# በኢጣሊያ በረሃዎች

ሻምበል አብዲሣ አጋ

በአርበኝነት ጀብዱ የሠራ ኢትዮጵያዊ ታሪክ

*The story of a Hero-Patriot of the*

*Italo-Ethiopian War*

t.me/OLDBOOKSPDF

## ምስጋና

በመጀመሪያ ቀን ይህችን መጽሐፍ ለማቀናበር ስጀምር በትርፍ ሰዓታቸው በታይፕ ሥራ ሴት ተቀን ለረዱኝ ም/፲

አለቃ አሁን ም/፻ አለቃ ዘሪሁን አታለልንና በሕትመትም ሆነ በሥራ ቅልጥፍና የረዱኝን የአዲስ ማተሚያ ቤት ሠራተኞችን ከልብ አመሰግናቸዋለሁ።

አብዲሣ አጋ ሻምበል

## መታሰቢያነቱ

ይህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ በዚያች በቀውጢ ቀን በአምስቱ ዓመት የኢጣሊያ ወረራ ዘመን ከጠላት ከኢጣሊያ ፋሺስት ጋር ስለ አገሩ ፍቅርና ስለወገኖቹ ኢትዮጵያውያኖች ክብር ከጠላት ጋር ተሰልፎ ሲዋጋ በጦር ሜዳ ለወደቁት ጀግኖች የተሰጠ ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF



ሻምበል አበዲሣ አጋ በአርበኝነት ጊዜ።

## መግቢያ

ያለሁበት ዘመን ልክ የ፪ኛው ዓለም ጦርነት ዋዜማ መሰለኝ። ቦምብ እንደ በረዶ ከሰማይ የሚወርድበት ቶጋዝ ጢስ የሚረጭበት የንጹሐን ሕዝቦች አስከሬን በየሜዳው የሚረፈረፍበት ያ የብስልና የጥሬ መለያ ወንፊት የሆነው ቀውጢ ቀን ከፊቱ ድቅን አለብኝ።

የሰውን ተፈጥሮ አደነቅሁ። በዚሁ ዓለም ስንት አጥፊዎችና ስንት አልሚዎች መሪዎች እንደ ተነሡ ተገነዘብሁ። ከላይ የወረዱ መቅሠፍቶች ናቸው አልሁ። ክቡሩ የሰው ልጆች ሕይወት በእኒህ ዕብሪተኞች መሪዎች በከንቱ ከ፟ገጸ ምድር መጥፋቱን ተመለከትሁ። የግል ፍላጎታቸውን ለመሙላት ያለዚያም የራሳቸውን ገናናነትና ኃያልነት ለማጉላት የሠሩትን ጥጋብ በአንክሮ አስታወስሁ። እንደኔ በጊዜው ሳልነበሩ ሕዝቦች የሂትለርንና የሙሶሊኒን እንዲሁም የተከታዮቻቸውን ዕብሪት ወደ ኋላ አዙሬ እንድመለከት ያደረገኝን የታሪክ ሐፍ አጠፍሁ። ‹‹ሰው እንዴት በሌላው ሰው ላይ እንዲህ ይጨክናል?›› ብዬ ተደነቅሁ።

ለ ፴ ክፍለ ዘመናት ከዚህም ለበለጠ በተራራዎቿ በልጆቿ ታፍራ የኖረችው ሀገሬ አንድ ጊዜ እንኳ መልክአ ምድሯን በቅኝ ገዥዎች ቀለም አለማስቀባቷን ሳስብ ራስ መውደዴንና ሥጋዊ ህልውናዬን በድሎት አርፎ የተቀመጠውን አንድ ጊዜም እንኳ የመበጥበጥና የመሸበር ዕድል ያልገጠመውን መንፈሴን አተኵሰው በዚያች ቀውጢ ቀን በአባቴ አብራክ በእናቴ ከረሥ ማኅፀን ውስጥ ሆኜ ተዋግቻለሁ። ተሰድጃለሁ ዱር ለዱር ተንከራትቻለሁ ብዬ ለልቤ ልብ ሰጠሁት።

t.me/OLDBOOKSPDF

የመኖር ልምምድ ያላቸው ሊቃውንት በተለይም የመጀመሪያውንና የ፪ ኛውን የዓለም ጦርነት በዐይናቸው ያዩት እንደሚተርኩት ያለዚያም እስከ ዛሬ ቁስሉ ያላዳነላቸው ጠባሳው ያልሻረላቸው አርበኞች እንደሚሉት የጦርነቱን ገፈት ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ ክፍለ ዓለም ውስጥ ከቀመሱት ኢትዮጵያ የመጀመሪያዩቱ ነች ይሉኛል በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ አርበኞች ለተተኰሰባቸው ጥይት መልሱን ሰጥተው በጠላታቸው አስክሬን ላይ ክንዳቸውን በመጫን ተጋደሉ። ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ባልዳሰሰው ሰይፍና ጕራዴ የጠላቶቻቸውን አንገት አንጠለጠሉ። በፋክራ በሽለላ የሚገባቸውን ፈጸሙ። ግን ዓለም ባወገዘው በጋዝ ጢስ ተደበደቡ። ከሰብአዊ ርኅራኄ ውጭ የሆነ በደል ተፈጸመባቸው። ግማሾች በመንፈስ ሳይሆን በአካል ድል ሆኑ የቀሩት በዱር በገደል ተሰደው ለጠላት የራስ ምታት ሆነው ከረሙ። የተረፉት ደግሞ በግዞት ወዳልተወለዱበት አገር ታፍሰው ተወሰዱ። በረኃብ በድብደባና በደዌ ፍዳቸውን አዩ። ብዙዎቹም ከነዚህ መቅሠፍቶች የተነሣ ሕይወታቸው እያለፈ ያ ክብር ኢትዮጵያዊ አካላቸው ለከባድ አገር አራዊት ታደለ። ታሪክ የትዝብት መነጽሩን ሲቀስር የእኒያን ግፈኞች መሪዎች ሐረግ ትውልድ ከአራዊት ወገን መሆኑን ደፍሮ መዘገበ።

በኢጣሊያ አገር ተሰደው ከወህኒ ቤት አምልጠው በታሪክ ለታሪክ የሠሩት ጅግንነት ለሀገራቸው ብቻ ሳይሆን ሌሎች ወንድ የሚያፈሩ አገሮችን ደስ የሚያሰኝ ሆነ። በሮም ከተማ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማና ክብር ሲዋረድ አይቶ በባዕድ አገር በጕራዴ ሽብር የፈጠረው ጀግናው ዘርዓይ እዚህ ላይ ይጠቀሳል። አዝናለሁ። ዘርዐይን በዐይኔ አላየሁትም። ታሪኩንም በሚገባ አላውቅም። ግን በኢትዮጵያዊነቱ እሁንም እኰራለሁ።እኔ ብቻ ሳልሆን መላው የሀገሬ ሕዝብ ይኰራበታል። እስከ ዛሬ ድረስ ያ ኢትዮጵያዊ ዓፅሙ የትኛው አፈር ጋር እንደተቀላቀለ ባይታወቅም የዘርዓይ ታሪክ ፋናውን ይዞ ሲጓዝ ብዙ መሥመር ያለው ጽሑፍ ይወጣዋል።

ወደ ዓላማዬ ልመለስ። «ከትሬያ ወህኒ ቤት አምልጩ የኢትዮጵያንና የዩጎዝላቪያን እንዲሁም የሌሎቹን አርበኞች አስከትዬ በኢጣልያ ተራራዎች ተዋጋሁ። ብዙ የፋሽስትና የናዚስት አስክሬን አስቆጠርሁ። ማረክሁ። ተሸለምሁ። ከበረሓ ወዳ ከተማ በድል አድራጊነት ስገባ «ኢትዮጵያ» የሚል ጹሑፍ ያለበት የሀገሬ ግርማ ሞገስ የሆነችውን ሰንደቅ ዓላማ በያንዳንዱ አርበኛ ክንድ እያሰርሁ አሰለፍሁ...» ይህን የነገሩኝ የዚህ መጽሐፍ ባለታሪክ ሻምበል አብዲሳ አጋ ናቸው «ሻምበሉ እንዴት ይህን የመሰለ ሥራ በሰው አገር ላይ ይሠራል»? ስላቸው የሚያቀርቡልኝ የጽሑፍ መረጃ ብቻ ሳይሆን ፎቶግራፍም የተባበሩት መንግሥታት የቃል ኪዳን ጓደኞችንም ማኅተምና ፊርማም ጭምር ሆነ። ለካ ሀገራችን እስከዚህ በደረጃ ጀግኖች የታጠረች ነች አልሁ።

የሻምበል አብዲሳን ታሪክ በሙሉ ያዘጋጀሁት እኔ ብቻ አይደለሁም በፊት የኢትዮጵያ ድምፅ ረዳት አዘጋጅ የነበሩት ሟቹ አቶ መንግሥቱ ገሠሠም ሞክረውት ሞት ቀደማቸው። «እሳቸው ትንሽ ጀምረውልኝ ነበር የአምላክ ፍቃድ ባለመሆኑ ቀረ። እባክዎ እርስዎ በተቻለዎ መጠን ያዘጋጁልኝ» ብለው ሐሳቡን ነድፈው አቀረቡልኝ። እኔም የዚህን የጀግና መጽሐፍ ባለኝ አቅም መልክ ባስይዘው በጥቂቱ እኔም በጦር ሜዳ እንደ ዋልሁ በጥቂቱ እንደ ቆሰልሁ በትንሹም እንደ ታሰርሁ እቆጥረዋለሁ ብዬ ተስማማሁ፤ ሆነ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ራሴ ጀግና አይደለሁም እንጅ የጀግኖችን ታሪክ ማንበብ እወዳለሁ፡፡ አንድ የዱር አውሬ ተኩሶ ባልገደለው እጄ የዚህን ጀግና ታሪክ ሳዘጋጅ በጣም ባልኰራም ደስ ይለኛል፡፡ በፖለቲካም ጦር ሜዶ ጀግና የነበሩትን የሰውን ተፈጥሮ በእኩልነት የሚመለከቱትን የኬኔዲን የአሟሟትና ሌላም ታሪክ ጽፌያለሁ፡፡ ይሁን እንጅ ተቀምጦ መሞነጫጨርና በረሓ ለበረሓ ተንከራትቶ መዋጋት የተለየ በመሆኑ ከዚህ ቀጭ ብዬ ጻፍሁት፡፡ አንድም ቀን አልተዋጋሁም፡፡ እንግዲህ ሻምበል ታሪካቸውን ይናገሩ፡፡ አንብበላቸው እኛም አንድ ቀን ይህን የመሰለ ጀግንነት እንሠራ ይሆናል፡፡ ዘላለም ድልወት አያዋጣም፡፡ የተዋጉና ታሪክ ያነበቡ ሰዎች ተመሳሳይ የጦርነት ፈለግ ይከተላሉ የሚል ጥቅስም አለ፡፡ እንግዲህ ሻምበል አብዲሳ እንዲህ ይላሉ፡፡

* * *



ሻምበል አብዲሳ አጋ በጋሻና በጦር ልብስ

t.me/OLDBOOKSPDF



ሻምበል አብዲሳ አጋን በጦር ልብስ የሚገልጽ ስዕል



ሻምበል አብዲሣ አጋ ንጉሰ ነገሥቱን በክብር አጅበው

t.me/OLDBOOKSPDF



ሻምበል አብዲሣ አጋ ከአክስታቸው ልጆች፣ከአጎታቸው እና ከአጎታቸው ልጆች ጋር በ1962 ዓ.ም.



አብዲሳ አጋ እባላለሁ። የተወለድኩት በ፲፱፻፲፮ ዓ.ም በወለጋ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ በነጆ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ቀበሌ ነው። በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ስመ ክርስትና ተሰጥቶኝ በመጠመቅ የኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ተከታይ ሆንኩ።

በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም በነጆ ቀበሌ ይገኝ በነበረው በአባ ገብረ ማርያም የግል ትምህርት ቤት ገብቼ የአማርኛ ጽሕፈትና ንባብ እንዲሁም የቅኔ ትምህርት ተማርሁ። ከዚያም ፡ በ፲፱፻፳ ዓ.ም ከአንድ የሚሲዮን ትምህርት ቤት ገባሁና የእንግሊዝኛ ትምህርቱን ቀጥዬ ሳለ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም አባቴ ወደ ነቀምቴ አውራጃ ይዘውኝ ሲሄዱ የጀመርኩት ትምህርት ተቋረጠብኝ።

ከዚህ በኋላ በለቀምት እንዳለሁ አንድ አጋጣሚ ተፈጠረ ይኸውም አጋጣሚ ከትውልድ አገሬ ለመውጣት ምክንያት ከመሆኑም በላይ ለኑሮ ዕድሌም በር ከፋች ሆኗል። በልጅነቴ የደረሰብኝ ድንገተኛ አጋጣሚ አሳዛኝ ነበር። ምናልባት በዚሁ ምክንያት እንደሆነም አላውቅም በተፈጥሮ ዕድሌ ሳማርር ለመኖር የተገደድሁት። ዋናው የሕይወት ታሪኬ እንዲህ ሲል ይጀምራል። ጊዜው በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ሲሆን ወሩንና ሰዓቱን ለይቼ አላስታውስም። በዚህ ወቅት እኔ የ12 ዓመት ልጅ ነበርኩ። አባቴ ከታላቅ ወንድማቸው ጋር በርስት ጉዳይ ጸብ ነበራቸው ይላሉ። በዚሁ ጸባቸው የተነሣ ወንድማቸውን በጦር ስለ ገደሉት ተይዘው ነቀምቴ ወህኒ ቤት እንዲታሠሩ ተደረገ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሩ እጀን በጆፎ እንደ ተባለው በመሆኑ በእኔም በእናቴም ላይ ከባድ ሁለት ኀዘን ወደቀብን፡፡ እንደተናገርኩት ዕድሜዬ የ12 ዓመት ነበር፡፡ ሆኖም የዕድሜዬ ማነስ የአባቴን ሕይወት ለማትረፍ ከመታገል ወደ ኋላ እንዳሸገሽግ አላስገደደኝም፡፡ ከዚህም የተነሣ ከሌሎች ዘመዶቼ ጋር የህገር ሽማግሌዎች ሰብስበን የሟቹን ቤተ ዘመዶች «ይቅረቡልን» በማለት ለአባቴ ይቅርታ እንዲያደርጉለት ልመናችንን አቀረብን፡፡ የአጎቴ ወገኖችም ምንም እንኳን በአሟሟቱ ቢጸጸቱ በድጋሚ የእኔን አባት አስገድለው መቅበር አልመረጡም፡፡ ስለዚህ ነገር ሳናበዛ «ይቅር ለእግዚአብሔር» ተባባልን፡፡

የሚቀጥለው እርምጃ በሟችና በገዳይ ቤተ ሰቦች መካከል ዕርቅ መውረዱን ለፍርድ ቤቱ አስረድቶ አባቴን ከእስር ማስፈታት ነበር፡፡ በዚህም መሠረት በመጀመሪያ የሟቹ ቤተ ሰብ«ምረናል» ሲሉ በማረጋገጥ ነቀምቴ ፍርድ ቤት ተገኝተው ቃላቸውን በጽሑፍ አስፈረው በፊርማቸው አጸኑት፡፡ ይህ ሲሆን ለእኔም ለእናቴም የተሰማን ደስታ የላቀ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ አባቴ ወደ አዲስ አበባ ተላልፈው ስለ ነበር ፍርድ ቤቱ ይህን የቤተ ሰቡን መተማመኛ ከሸኚ ደብዳቤ ጋር ወደ አዲስ አበባ የሚልክ መሆኑን ገለጸልን፡፡

ስለዚህ እኔና እናቴ ቀድመን አዲስ አበባ ለመገኘት አገር ጥለን ቁርበት ጠቅልለን ተነሣን፡፡ ጉዞአችን አድካሚ ቢሆንም አልተሰማንም ቀን በዕውኔ የማስበው ሌሊት በሕልሜ የማልመው አንድ ነገር ብቻ





ነበር፡፡ ያንን አባቴን...ያን የሚያፈቅረኝን አዎ ያንን ብለየው የሚከፋውን አባቴን ከእስር ለማስፈታትና አሁንም አባባ እያልኩ እንድከተለው የላቀ ምኞት አድሮብኛል፡፡ ቁመናው በዐይኔ ላይ ይሄዳል ፤ ጨዋታውና ፈገግታው ትዝ ሲለኝ እንባ ያንቀኛል፡፡ ማን ያውቃል የአምላክን ነገር ምናልባት አሁንም በነጻ ተለቅቆልኝ ካጠገቤ ቁሞ በዚያው ሁኔታ ያነጋግረኝ ይሆናል!! አሁንማ ጉዳዩ አልቋል ፤ ዳኞቹም ግድ የለም ብለውናል፡፡ ታዲያ ምን ያሠጋኛል እያልኩ ሳስብ ውዬ አድራለሁ፡፡

አዲስ አበባ ስንደርስ ግን ነገሩ ተለውጦ ብርሃኑ ጨለማ ሆነብኝ ፤ ያሰብኩት ቀርቶ ፍጹም ይደረጋል ያላልኩት ተፈጽሞ አገኘሁት፡፡ ከአዲስ አበባ ስደርስ የክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያምን እንደራሴን አገኘኋቸውና ከሟቹ ዘመዶች ጋር በነቀምቴ ፍርድ ቤት ቀርበን በዕርቅ መለያየታችንንና የዕርቁም ስምምነት በነቀምት ፍ/ቤት በኩል ወደ አዲስ አበባ መተላለፉን አስረዳኋቸው፡፡ ግን እኔ እንዳልኩት አልተፈጸመም፡፡ ለካስ በዚህ ፈንታ ፍ/ቤቱ የሟቹ ወገኖች እንታረቅም ብለዋል የሚል ደብዳቤ አስተላልፎ ኑሮ ይህንኑ ነገሩኝ፡፡ እንዴት? እኔው ራሴ ቀርቤ በተገኘሁበት የተፈጸመውን...እንዴት ይክዱኛል?...ፍላጎታቸው አባቴን ሊአስገድሉብኝ ነው? እያልኩ እንባዬ እየፈሰሰ ስጮህ የደጃዝማቹ እንደራሴ «ልጄ የአራት ቀናት ጊዜ ብቻ ስጠኝና እንደሚሆን አደርጋለሁ» አሉኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

አራት ቀናት በዚያን ጊዜ ለእኔ ሩቅ ነበር፤ ብቻ ምን ይደረግ? ሌላ ምርጫ አልነበረኝምና ለመታገስ ቆረጥኩ። በማግሥቱ ግን መርደዱን ተከናነብኳት። አባቴ መገደሉን ሰማሁ። ይኸው ነው ያ ሁሉ ሩጫ ያ ሁሉ ድካም ያ ሁሉ ምኞት ያ ሁሉ ተስፋ። ከዚህ ላይ አበቃ። የድካሜ ውጤት ሁሉ መጨረሻው ኀዘን እንደሚሆን ምናልባት ይህ የመጀመሪያው ምልክት ይሆን? እንጃ እስኪ ከዚህ በኋላ የቀጠለውን ታሪኬን ላውጋላችሁ። እዚህ ላይ ባለምባራስ ገብረየሱስ ካራ ዮና ባለቤታቸው በዚያ ጊዜ ከኔና ከናቴ ጋር የተቀበሉትን ፈተና ሳላስታውስ አላልፍም። ከአምላክ ብድር ይግባቸው።

ምንም እንኳ የአባቴ ኀዘን ከልቤ ባይጠፋ የወደፊት ሕይወቴን አቋም መሥመር ለማስያዝና ወደ ዕለት ተግባሬ ለመሠማራት በማለት በገነት በተቋቋመው የቀ. ኃ. ሥ. ጦር ት/ቤት ለመቀጠር ወሰንኩ። በወታደርነት ሀገሬን ለማገልገል የነበረኝ ቅን ምኞት ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለማመልከት ዕድል ስላጋጠመኝ ወደዚሁ ት/ቤት ገብቼ እንድማር ሲፈቀድልኝ በባሻ ኤፍሬም በየነ ባልደረብነት ለክቡር ኮሎኔል በላይ ኃይለ አብ ተነግሮልኝ ትምህርቴን ጀመርኩ።

ይሁን እንጂ ዕድሜዬ ገና 14 ዓመት ስለነበር ክቡር ኮሎኔል በላይ ጋር ለጥቂት ጊዜ አብሬ እንድቆይ ተደረገ። ክቡርነታቸው በዚያን ሰዓት የቦይ እስካውቶች ኃላፊ ሲሆኑ እኔም የተደለደልኩት በዚሁ





ክፍል ነበር የመጻፍና የማንበብ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የአግረኛ ሰልፍና የከባድ መሣሪያ ተኩስ ትምህርት ቢሰጠኝም የእኔ የተለየ ተሰጥዎ የከባድ መሣሪያ መፍታትና መገጣጠም እንዲሁም የልዩ ልዩ መሣሪያዎች ተኩስ ነበር።

ይህን ትምህርት እንዳጠናቀቅሁ የ፲ ዕልቅና ማዕርግ ተሰጠኝ፤ ወዲያው በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም በፋሺስት ኃይል ኢትዮጵያ ስትወረር በወሊጋ የገባውን ጠላት ለማጥቃት ሙሉ የገነት ጦር በኮሎኔል በላይ መሪነት ነቀምቴ ወደ ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ዘንድ ሲሄድ እኔም ከዘማቾቹ አንዱ ነበርኩ።

ከዚያ ለመድረስ ስንነሣ ጠላት በአውሮፕላኖች መጥቶ ቦነያ ላይ አረፈ። ሌሊት ጠላት ወደ አረፈበት ተጠግተን አደርን። ሲነጋ ጦርነት ገጠምንና አምስቶቹን የጠላት አይሮፕላኖች ስናቃጥል አንዱ ብቻ ሊያመልጥ ቻለ።

ጉዞው ቀጥሎ ነቀምቴ ገባን። እንደገናም ከነቀምቴ ወደ ግምቢ ከግምቢ ጮሊ ጌራ አምርተን ከዚህ ላይ ከልዑል ራስ እምሩ ጦር ጋር ተገናኘን። ሁለቱም ክፍለ ጦር በአንድነት እየተጓዙ ጉጅብ ስንደርስ ድልድዩ ፈርሶ ስላጋጠመን ለጊዜው ሠራዊቱ ከዚያ እንዲያርፍ ተደረገ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በአራተኛው ቀን ጠላት ዙሪያውን ኣበበን፡፡ ከ3 ሰዓት ያላነሰ ውጊያ ቀጥሎ ከሁለቱም ወገን ከፍ ያለ ጉዳት ከደረሰ በኋላ ጠላት ዙሪያውን ከመክበቡም በላይ የያዘው ሰፍራ ለማጥቃት ስላመቸው የእኛ ሠራዊት ተበታተነ፡፡ ዕድለኛ የሆነው ሲሰደድ ገሚሱም ከልዑል ራስ እምሩና ከኮሎኔል በላይ ጋር ተማረከ፡፡ እኔም በሁለት ጥይት ቆስዬ ስለነበር ከሌሎች ቁስለኞች ጋር በቃሬዛ ወደ ቦንጋ ተወሰድኩ፡፡ ከ3 ወር ሕክምና በኋላ ግን እኔንና አብረውኝ የነበሩትን ፴ ወታደሮች ጂማ ወህኒ ቤት አስገቡን፡፡ በዚህ ወህኒ ቤት አንድ ወር ተኩል እንደቆየን አዲስ አበባ አምጥተውን በመካከለኛው ወረዳ በተለይ ጾሮ ማንቂያ ከተባለው ሰፈር በነበረው ወህኒ ቤት ውስጥ ሁለት ወር አሥሩንና በኋላ በቁም እሥር ለቀቁን፡፡

ስድስት የምንሆነው በጉለሌ የእማሆይ ደስታ ቤት ተከራይተን ተቀምጠን ሳለ አንድ ቀን የተኩስ ድምፅ ሰማን፡፡ ዕለቱ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ሲሆን የተኩሱም መነሻ ምክንያት ያው የግራሲያኒ መቁሰል ነበር፡፡ ፫ ኢጣሊያኖችና ሌሎችም አድራሻችንን የሚያውቁ የሀገራችን ሰዎች መጥተው እየነዱ ከዚያው ፊት ከነበርንበት ወህኒ ቤት አስገብተውን መጀመሪያ የቃል ምርመራ አደረጉልን ፤ ቀጥለው እያንዳንዳችንን በየክፍሉ አሥረው ሲገርፉንና ሲደበድቡን አድረው በማግሥቱ የቀሩትን ፺፪ ወታደሮች እየሰበሰቡ አምጥተው የእኛኑ የመሰለ ዕድል እንዲያገኙ አደረጓቸው፡፡





የደረሰብን ድብደባና ግርፋት ሰው ያችለዋል የሚባል አልነበረም፡፡ እጃችን የፊጥኝ ወደ ኋላ ታሥሮ የዛፍ ፍልጥ እንጨት በላያችን ሲያልቅ ጥፊና ጡጫ ሲወርድብን ከቆየ በኋላ የአኮርማጅ ግርፋቱ ይቀጥል ነበር፡፡ ገራፊዎች ክንዳቸው ሲዝል እያረፉ ምርመራውን በዚሁ ዐይነት ለሁለት ቀናት ሲያከናውኑ ቆዩ፡፡ በአራተኛው ቀን በመኪና ጭነው ወደ ምፅዋ ወሰዱን፡፡ ከዚያም በመርከብ ተሳፍረን ሞቃዲሾ ስንደርስ ደናኔ ወህኒ ቤት ከተቱን፡፡

በደናኔ ወህኒ ቤት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሴትና ወንድ ኢትዮጵያውያን እስረኞች ነበሩ፡፡ ካየናቸው ይበልጥ ሌሎች ብዙዎች እንደ ነበሩ ብንሰማም በድብደባ ብዛት በጥይት በረሃብና በበሽታ ማለቃቸውን ተረዳን፡፡ እኛም ወደዚያው የተወሰድነው ለዚሁ መከራ ነበርና ዱላውና ግርፋቱ ይወርድብን ጀመር ፲፰ቱን የገነት ልጆች ግን ከመካከላችን መርጠው ረሃብና መጉሳቆል ባደከመው ጉልበታቸው የራሳቸውን መቀበሪያ ጉድጓድ ካስቆፈሩአቸው በኋላ ከዚያው ጉድጓድ ውስጥ እያቆሙ በጥይት ፈጅተው አፈር መለሱባቸው፡፡

ይህን ሁሉ ስቃይ የቻልነውና ከጥይት የተረፍነውን ፴ የገነት የጦር ወታደሮች ሌሎች ሴቶችና ወንዶች ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ከሌላ አገሮችም የመጡ እሥረኞችን ወደ ኢጣሊያ ለመውሰድ በመርከብ ጫኑን፡፡ የመርከቡ ጉዞ ከወህኒ ቤቱ ከነበርንበት ሁኔታ የተሻለ አልነበረም፡፡ በተለይም ስዊስ ካናል ስንደርስ የእንግሊዝ ፖሊሶች



t.me/OLDBOOKSPDF

ለምርመራ ወደ መርከቡ ሲወጡ እሥረኞቹን ከመርከቡ የከሰል ማኖሪያ ክፍል ውስጥ አግብተው ዘጉብን። የእሳቱ ግለት የፀሐዩ ሙቀት የአየሩ በጢስ መታፈን መፈጠርን የሚያስጠላ ነበር። ደግነቱ መርማሪዎቹ ሲወርዱ እኛም ከዚያች ክፍል እንድንወጣ ተደረገ።

ከ፫ ቀናት በኋላ ናፖሊ ስንደርስ ፀሙቹን የገነት ልጆች በአውቶቡስ ጭነው እኛና ከተባለ የእሥረኞች ሠፈር ከተቱን። ይህ ቦታ ለጊዜው ለእሥረኞች ማረፊያ እንዲሆን የተሠራ ቁመቱ ፫ ሜትር በሆነ የሽቦ አጥር የተከለለ ሲሆን እሥረኞቹም የሚኖሩት ከእንጨትና ከብረት ከተሠሩ ቤቶች ውስጥ ነበር። ወህኒ ቤት ብዬ ልጠራው ያልሞከርኩበትም ምክንያት ለጊዜው ለጦር እሥረኞች እንዲሆን ተጣድፎ የተሠራ በረት እንጂ ቋሚ ሆኖ እንዲያገለግል ታስቦ የታነጸ ባለመሆኑ ነው።

የወህኒ ቤቱን የሽቦ አጥር ቀርቦ ከእሥረኞቹ ጋር ለመነጋገር ማንም ተላላፊ አይሞክርም። አንዳንድ ደፋር ሲገኝም ወዮለት። ተላላፊ የውጭ ዜጋ ከሆነ ውጭ እሥር ቤት ይታሠራል። ከእሥረኞቹም አንዱ በመንገድ ከአጥር ውጭ የሚተላለፍ መንገደኛ ለማነጋገር ቢሞክር ለተወሰነ ጊዜ በተዘጋጀች ክፍል ውስጥ እንዲሰነብት ይገደዳል። የእሥሩ ሠፈር ቀን ቀን ይበርዳል ማታ ማታ ደግሞ ይሞቃል። የእኛም የእሥር ሠፈርና የናፖሊ ከተማ ትይዩ በሆነ አንጻር ላይ ናቸው። እሥር ቤቱ ከከተማዋ ወጣ ባለ ቦታ ላይ ሲገኝ





ከምሥራቅና ከምዕራብ በሁለት ትላልቅ ተራሮች የተከበበ እርሻ ይታያል። ከእሥር ቤቱ ወጥቶ የሚሄደው የመኪና መንገድ ይህንኑ እርሻ ሰንጥቆ ያልፋል። በስተምዕራብ ካለው የተፈጥሮ ፍል ውሃ አቅራቢያ አንድ ትምህርት ቤት ተሠርቷል። በስተሰሜን የሚታዩትን ግን በእሥር ቤቱ አቅራቢያ የሚገኘውን ባሕር በመከበብ የተሠሩ ታላላቅ ሕንጻዎችና አፈር እያቀለጠ ብረት የሚያወጣ ፋብሪካ ነው።

በእኛና እሥር ሠፈር እንዳለሁ ጣሊያንኛ መነጋገር ደህና አድርጌ ቻልኩ። አንድ ቀን የእንግሊዝ አይሮፕላን መጥቶ በአረብኛ በእንግሊዝኛና በፈረንሳዊኛ የተጻፈ ወረቀት ሲበትን ጥቂቶቹ ከእሥር ሠፈሩ ውስጥ አረፉ፤ እኔም አንዷቷን አገኘሁና ደበቅኋት። ለካስ ሌሎች እሥረኞች አይተውኝ ኑሮ ለሠፈሩ ዘበኛ ገለጹለት በመከራ ጊዜ ሰዎች ይተዛዘናሉ ሲባል እሰማ ነበር፤ ነገር ግን እንደሰማሁት አልሆነም በመከራ ላይ የወደቁ ሰዎች ቢተዛዘኑም ሁሉም የየራሱን ሕይወት አብልጦ እንደሚወዳት በዚያን ሰዓት መገንዘብ ቻልኩ። ሆኖም እኔን አሳልፎ በመስጠት ራሱን ነጻ ለማድረግ ያሰበው እሥረኛ እንደኔው መንገላታት እንጂ አስተያየት ሳይደረግለት ቀረ።

መልእክቱ የተነገረው ዘበኛ መጥቶ ከፊቴ ተገተረ። ያ ቀድሞ ኖራ የሚመስል መልኩ አሁን ሳምባ መሰሏል። የዐይኑና የግንባሩ ሁኔታ በእኔ ላይ ምን ያህል ጥላቻ እንዳደረበት ነገረኝ። ቢሆንለት ወዲያውኑ አንቆ ቢገድለኝ የሚከፋው አይመስልም። ‹‹ጽሑፉን



t.me/OLDBOOKSPDF

ጽሑፉን ቶሎ በል ጽሑፉን አምጣ›› አለኝ። ከኪሶ አውጥቼ ሰጠሁት ። አልበቃውም ይህቺን በግራ እጁ አዛወረና መዳፉን ዘርግቶ ጣቶቹን እጥፍ ዘርጋ በማድረግ ‹‹ቶሎ ቶሎ በል ሌላውንም አምጣ›› ሲለኝ ራሴን እያወዛወዝኩ ይኸው ብቻ ነው አልኩት።

ደርሶ ላይጠቅመው ንዴቱ ገንፍሎ በጫማው ረገጠኝ፤ እኔስ ማነኝ? ኢትዮጵያውያን ለክብራችን ክርሱ የበለጠ ስሜት እንዳለን ገና አልተገነዘበውምና እጆቼ ከሰንሰለት ነጻ ወጥተው ስለነበር ትምህርት እንድሰጠው ኢትዮጵያዊነቱ አስገደደኝ። በነበረኝ የጉልማሳ ኃይል ከጆሮ ግንዱ ስር ሁለት ጊዜ በጡጫ ብነጠርቀው ከእግሬ ስር ተፈጠፈጠ። የዘበኛውን አወዳደቅ እሥረኞቹ ሲመለከቱ ድፍረቴ በፍርሃት እንዲዋጡ አደረጋቸው። ሌሎች የፋሺስት ዘበኞችም እየሮጡ ሲመጡ ከቆምኩበት ሳልንቃንቅ ጠበቅኋቸው። በብዛት በላዩ ተረፈረፉብኝና እጆቼን በካቴና ውስጥ አስገብተው ከነበርኩበት ፎቅ ወደ ታች ቢለቅቁኝ በትከሻዬ ከመሬት አረፍኩ። ትከሻዬም ደቀቀ። ጉልበቶቼም ተላላጡ። በዚያን አደጋ የደረሰብኝን የቁስል ጠባሳ እስከ ዛሬ ስመለከት ሕሊናዬ በኀዘንና በትካዜ ሲመሰጥ በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያዊነቱ እኮራለሁ።

እንዴት ሰው በሰው እስከዚህ ይጨክናል? ምናልባት ለሀገሩ ባዳ ለሕዝቡ እንግዳ በመሆኔ ይሆን? ምናልባትም እኮ ጥቁረቴና ባይተዋርነቱ በእነሱ ዘንድ እንደ ዱር አውሬ አስቆጥሮኝ ይሆናል።





ይሁን እንጂ በአውሬውስ ቢሆን ኀስከዚህ የሚጨክን ሰብአዊ ፍጡር እንዴት ሊኖር ይችላል? አለ ወይም ነበር ከተባለ እርሱም ከአውሬ የተሻለ አይደለም ማለት ነው።

ይህን የመሰለ ጉዳት ከደረሰብኝ በኋላ ታዝኖልኝ ሕክምና የሚደረግልኝ መስሎኝ ነበር። ግን እንዲያውም ያለሁበት የእሥር ሠፈር እንዲለወጥና በጠበቀ እሥራት እንድቀጣ ስለተወሰነ ቀኑን በማላስታውሰው በ፲፱፻፴፩ ዓ.ም ወደ ናፖሊ ቦጆሪያሊ ወህኒ ቤት ተወሰድኩ።

በጆሪያሌ እሥር ቤት ውስጥ የነበረው የእሥረኛ ብዛት እጅግ የበረከተ ሲሆን የብዙ ሀገር ዜጎች ነበሩበት። የኢትዮጵያ የእንግሊዝ የዐረብ የፈረንሳይ የዩጎዝላቪያና የሌላ አገር እሥረኞችም ነበሩ። ከኢትዮጵያውያኑ መካከል ካሣዬ፣ አብጤ ፣አሰፋ ፣በለውና ካርሎ አባ መጋል ከተባሉት ጋር ዘወትር እንገናኝ ነበር በቦጆሪያሌ እሥር ቤት ከሁሉም የማይዘነጋኝ በየቀኑ የሚመጣው የእሥረኞች ሬሣ ብዛት ነበር። ምክንያቱ በሽታ ቢሆንም አስፈላጊው ሕክምና ስላልቀረበ በቀን ብቻ እስከ ፪፻ ያህል ሰው ይሞታል። ምናልባት ስንቅ ከማቅረብ በበሽታ ማለቃችን ተመርጦም እንደሆን አልገባኝም። ግን ምንም እንኳ እኔ ካለሁበት ክፍል ብቻ በቀን ፪ እና ፫ ሬሣ ቢወጣ ፈጣሪዬ ከልሎኝ እኔን ጉንፋን እንኳ አልያዘኝም ነበር። እንዲያውም በአምላክ ረድኤት ሰውነቱ እየፋፋ ሄደ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከዚህ እሥር ቤት እንዳለን ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተነሣ። ጦርነቱ እየተፋፋመ ሲሄድ በኢጣሊያ ወታደሮች መካከል መርበድበድ ሽብርና አለመተማመን መፈጠሩን በአቅራቢያችን ከነበሩት ዘበኞችና ሹማምንቶቻቸው ሁኔታ መረዳት ችለን ነበር።

ከዚህ ሁሉ በላይ እኛ የነበርንበት የእሥር ሠፈር አስጊ መስሎ ስለታያቸው ሌሊት በሚያልፍ ባቡር እሥረኞቹን በሙሉ በሰንሰለት እያቆራኙ ከናፖሊ ወደ መካከለኛ ኢጣሊያ ማጓጓዝ ጀመሩ። እሥር ቤቱ የሚገኘው በተለይ በሌቼ ወረዳ ትሬያ ቀበሌ ቪላ አስባዳ ከተባለው ቦታ ‹‹ካምቦ እንቴርናቴ›› የተባለ ነበር። ለጊዜው እሥረኛ በመሆኔ የሁኔታውን ፎቶ ባለማግኘቴ ይጸጽተኛል። በጠቅላላው ጉዞአችን አሳዛኝና አስቃቂ ነበር። መሬ-መድ የተሳነው አንዳንድ እሥረኛ እየወደቀና ወደ ፋርጎው ሲያመራ በግፊያው መካከል እየተረጋገጠ ሕይወቱን አጥቷል። ሌሎችም ለሕመማቸው ሳይታዘንላቸው የዘበኞች እርግጫና የሰደፍ ጉሽም የደረሰባቸው ብዙዎች ነበሩ። ያም ሁሉ ሆኖ በናፖሊ ከተማ ውስጥ የከበበን ስቪል ሕዝብ ገሚሱ ሲተፋብን ክንዳቸውን ወደ አየር እያወጡ በዛቻ የደነፉብንን ወጣት ፋሺስቶች አልዘነጋቸውም።

እኔም ዕድሜዬ ገና ፳፰ ዓመት ስለነበር ንጹት ፈጥኖ እየተሰማኝ አንድ ቀን ዕድል አጋጥሞኝ ከእሥራት ለማምለጥና ይህን





ሁሉ አመፅ የሚፈጽሙብኝን ፋሺስቶች በመፍጀት ብድሬን ለመመለስ መመኘት እንጂ ለዚህ ዓለም ኑሮ አምሮት አልነበረኝም።

እንደ ሰርዲን በየፋርጎው ታጭቀን በሩ ከተዘጋብን በኋላ ባቡሩ ጉዞውን ቀጠለና ትሬያ ከተባለው እሥር ሠፈር ደረስን። ከዚያም እንዲሁ ከልዩ ልዩ አገር የመጡ የፖለቲካ እሥረኞች ጋር እንድንቀላቀል ተደረገ። ውስን ስናድር አብረውኝ ከእሥር ቤቱ የሚገኙትን አንዳንድ ኢትዮጵያውያን እየፈለግሁ ከእነሱ ጋር ሐሳብ መለዋወጥ ስጀምር ጠባቂዎቹ ዘበኞች ከባድ ጥርጣሬ አደረባቸው። ጥብቅ ተከታታዮችም እንዳደረጉብኝ ተረዳሁ። ሆኖም ከሀገሬ ሰዎች ጋር የማደርገውን ግንኙነት አላቋረጥኩም። ከዚህ የተነሣ ለወደፊቱ ከማንም እሥረኛ እንዳልገናኝ በማለት አጃቢ እንዳይለየኝ ታዘዘ።

ይመስለኛል ብቸኝነት ለሐሳብና ለመመራመር ይረዳል። ብቻዬን ሆኜ ሐሳቤን ሳወጣና ሳወርድ አንድ መላ ፈጠርኩ። ከሰው ሳልነጋገር ከአንድ ክፍል ውስጥ ተዘግቶብኝ መዋል እጅግ አድርጎ አስመረረኝ።

ስለዚህ ዘበኞቹ ወደ ውጪ ሊያወጡኝ በመጡ ቁጥር ‹‹አሞኛል የሕመሜንም ዐይነት አላውቀውም›› እላቸውና ጥቅልል ብዬ እጋደማለሁ። ይህ በመጀመሪያ ጊዜ የወሰድኩት የለሰለሰ እርምጃ ነበር፤ ከሐሳቤ ጋር የምሟገትበት ሌላ ዓላማ ደግሞ አቅጃለሁ። እርሱን



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመፈጸምም ተቻልኩ ልቤ ሲጎትታ ይሰማኛል፡፡ «ጊዜው አሁን ነው ፣ ያልኩባት ሰዓት ደረሰች፡፡

ለመንፈሴ «ከዛሬ ጀምሮ ዕብድ ነኝ» ስል ራሴን በራሴ አታለልኩት፡፡ አዎ ዕብደት ባይሰማኝም ከዛሬ ጀምሮ እንደ ዕብድ ሆኜ ራሴን ከዚህች ጨለማ የሆነች ምድራዊ ገሃነም ውስጥ ማውጣት አሰብኩ፡፡ የክፍሏ መዝጊያና መስኮት በተላላፊ የብረት ዘንጎች የተጠፈሩ ቢሆኑም በተደራቢ ከውስጥ በኩል በመስተዋት ከውጭ በእንጨት የተዘጉ ነበሩ፡፡ የዕብደቱን ምልክት ለማሳየት ስል በእኩለ ሌሊት ላይ የመዝጊያውንና የመስኮቱን መስተዋት በእርግጫ እየደበደብኩ ከፍ ባለ ድምፅ እጮህ ጀመር፡፡ ሌሊቱንም እንዲሁ ስጮህና ስፎክር አደርኩ፡፡ አንዳንድ ጊዜም ነገሩ ወደ ብስጭት እየተለወጠብኝ ከብረቱ ጋር ሲያታግለኝ መቼም እንዳይነጋ የለም የብርሃን ወጋገን ታየ፡፡

በሦስት ሰዓት ገደማ ዘበኞቹ መጥተው እንደተለመደው እጆቼን በካቴና ካስገቡ በኋላ ትሬያ ወደተባለው ከተማ ከሚገኘው የአንጎል ሐኪም ቤት ወሰዱኝ፡፡ «እጆቹ ይፈቱ» ሲል ዶክተሩ አዘዘና እርሱ በመረጠልኝ ወፍራም ላስቲክ ክንዶቼን አስሮ ምርመራውን ቀጠለ ነገሩን ለማስተማመን ያንኑ ሁኔታዬን መቀጠል አሰብኝ በማለት እርሱ ሲስቅ እኔ አፍጥጬ እየዋለሁ፡፡ ሲቆጣ ደግሞ እየሳቅሁ አፈዝበታለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜም በሀገሬ ቋንቋ እየለፈለፍኩ ቀረርቶ በማሰማት እሞክራለሁ፡፡ የድካሜ ውጤት በከንቱ አልቀረም፡፡ «አንጎሉ





ተነክቷል» ሲል ዶክተሩ የምስክርነት ቃሉን ሰጥቶ አንድ መርፌ አዘዘልኝ፡፡ ይጉዳኛል ብዬ መስጋቴን እንጂ ይጠቅመኛል ብዬ ያላመንኩበትን መርፌ ከወሰድኩ በኋላ በመጣሁበት ሁኔታ ከነበርኩበት ከዚያች አስጸያፊ ክፍል ተመልሼ ተወሰድኩ፡፡

«እነዚህ ጨካኞች አላመኑኝም መሰል ገና አልለቀቁኝም፡፡ ደግሞ ሌላ ማስተማመኛ መንገድ ማግኘት አለብኝ፡፡ እኒህ አውሬዎች የዋዛ ሰው ያገኙ መስሎዋቸው» በማለት ሳመነታ ከሥፍራው ደረስን፡፡ ከዚያች እንደ ሞት በምትቀፍ እስር ቤት ስደርስ ወደ ውስጥ እንድገባ ዘበኞቹ እጄን ከካቴና ሲያላቅቁኝ ከመቅጽበት ካጠገቤ የነበረውን ዘበኛ በጡጫ ብዬው ወዲያው የመስተዋቱን ስብርባሪዎች እየለቀምኩ ወደ ሌላዎቹ ዘበኞች ስወረውር ሁለቱን አደማኋቸው፡፡

ማርሻሉ ቼስቴሲ ኤኔሪኮ የተባለው የዘብ አዛዥ ከእሥር የሚበልጡ ጭፍሮቹን አስከትሎ ወደ እኔ መሮጡን ስመለከት በገዛ እጄ ተዘርሬ ወደቅሁና እንከባለል ጀመር፡፡ እውነትም አሁን ዕብድቱን አወቁልኝ፡፡ ሁለት እግሮቼንና ሁለት እጆቼን ከታሠርኩ በኋላ ሁሉም በመሰላቸው ዐይነት ቁጭታቸውን ተወጡብኝ ከባድ የመቁሰልና የመፈንከት አደጋ አደረሱብኝ፡፡ ፊቱም ከመላላጡ ሌላ ከጭንቅላቱ በሚወርደው ደም ተሸፈነ፡፡ ቀጥሎ ማርሻሉ ወደ ትሬአ ካራቤኜር እሥር ቤት ተወስጄ ከዚያው እየተመላለስኩ ሕክምና እንድቀጥል አዘዘ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

‹‹አሁንስ በመርዝ መርፌ ወይም በጥይት ላይገድሉኝ አይቀሩም፤ ግን በማን ዕድሌ ከዚያች ምድራዊ ዝግ በሆነው መኪና ውስጥ እየተንገላታሁ እንደምንም ገሣነም ከተገላገልኩም አንድ ነገር ነው››። ዙሪያውን ከካራቤኜሩ እሥር ቤት አደረሱኝ የጣቢያው ሹም በጥላቻ መልክ ከፍና ዝቅ እያደረገ ተመለከተኝና ‹‹ለጊዜው ለወንጀለኛ ምርመራ በተዘጋጀው አንደኛው ክፍል ውስጥ አስገቡትና ሌሊት ምርመራው ይቀጥላል›› የሚል ትእዛዝ ሰጥቶ ሄደ። ወዲያው አንድ ወታደር በሰደፍ ሲገፋኝ ወደቅሁ። ተሸክመው ከአንድ አነስተኛ ክፍል ውስጥ ወረወሩኝ።

አበሳዬ ገና አላለቀም። እንዲያውም ገና የተጀመረም አይመስልም ለበል? ይህቹ ክፍል ደግሞ ከዚያች ቀድሞ ከነበርኩበት የባሰች ሆና አገኘኋት ፤ ሲወረውሩኝ የተፈጠፈጥኩበት የሲሚንቶ ጣውላ ውሃ ፈስሶበታል። ያም አነሰ ተብሎ ጣሪያው እየወረዛ ውሃ ያንጠባጥባል ብቆምም ብቀመጥም ብተኛም ቅዝቃዜው ልዩነት የለውም።

በግምት ከምሽቱ አራት ሰዓት ሲሆን ከላይ የተጠቀሰው መኮንን ሲቪል ልብስ ለብሶ በውፍረትም በቁመትም ከእኔ በጣም የሚበላልጡና እንደ ዱላ የተጠረቡ አለንጋዎች የያዙ ወታደሮች አስከትሎ የታሰርኩበትን ክፍል አስከፍቶ ሦስቱም ከውጭ እንደቆሙ አፍጥጠው ይመለከቱኝ ጀመር። ወገቡን በሁለት እጆቹ የጨበጠው





ማራቫሎ ገና ሲያየኝ ‹‹ይህ ጥቁር ገና አልሞተምና››? ኣል በመገረም መልክ ጠየቀ። ቀጥሎም በደም የተሸፈነ ፊቴን በጣቱ እያመለከተ በሰደፍ የተፈነከተውን ራሴን ሐኪሞች ዘንድ እንድታከመው ማለት እንዲጻፍልኝ አዘዘ። ከዚያች ክፍል ተወስጄ በትእዛዙ መሠረት ሕክምና ተደረገልኝ።

በዚህ ክፍል የሚገኘው ሐኪም ግን ቀደም ብሎ ፈጽሟል ተብሎ የተነገረው አድራጎቱ ሁሉ እርግጥ በዕብደት ምክንያት መሆኑን ስለተጠራጠረ አምኖ ሊቀበለኝ አልቻለም። ብዙ የተደጋገመ ምርመራ ካደረገልኝ በኋላም ወደ ነበርኩበት ተመለስኩ።

እስከዚህ ድረስ የእኔ ዕድል ከሌሎቹ እሥረኞች የተለየበትን ልረዳው አልቻልኩም። በጥይት እየተደበደቡ የሚሞቱ ብዙዎች እሥረኞች ነበሩ። ሆኖም በእኔ ብቻ ልዩ ልዩ አስተያየት የሚደረግበት ምክንያት አይገባኝም። የፈፀምኩት ድርጊት ሁሉ ማንንም እሥረኛ ለሞት የሚያበቃ ነበር በሽታውም ቢሆን አልደረሰብኝም። ይሁንና ነገሩ እንደ ልዩ ትንግርት ቢሆንብኝም ፈጣሪዬን ዘወትር ሳላመሰግነው አልቀረሁም። ለወደፊቱ ያስበልኝን አላውቅምና በእርሱ የመንፈስ ተስፋ መጽናናት ስለቻልኩ ሁልጊዜ ‹‹ተመስገን›› እለው ነበር።

ሕክምና በተደረገልኝ በማግሥቱ ጥዋት አራት ሰዓት ገደማ ላይ በአንድ ሹም በሚታዘዙ አራት ወታደሮች ታጅቤ ሌቼ አውራጃ ፍ/ቤት



t.me/OLDBOOKSPDF

ተወሰድኩ። ከችሎት ስቀርብ ያለምንም ጥያቄና መልሶ ዳኞቹ የቀረበላቸውን ጹሑፍ ተመልክተው ‹‹ሌቼ ዋና ወህኒ ቤት ገብቶ ከሁለት ቀናት በኋላ ለፍርድ ይቅረብ›› የሚል ትእዛዝ ሰጡ። ከሦስት ቀናት በኋላ ሁለት እጆቼን ታሥሬ እተባለው ፍርድ ቤት ቀረብኩ። አሁንም ምንም ጥያቄ ሳይደረግልኝ እኔም መልስ ሳልሰጥ እዚያው እነበረኩበት እሥር ቤት እንድመለስና ከሦስት ወር በኋላ እንድቀርብ ታዘዘ።

እንግዲህ ይህ የመጨረሻ ዕድሌ መሆኑን ተረዳሁት፤ እጆቼን ታሥሬ በጥይት ከምደበደብ ይልቅ ጠፍቼ ለመውጣት መሞከርን ወደድሁ። ‹‹እዎ ይህንን ለማድረግ ብዙ የሚያዳግተኝ ችግር ያለ አይመስለኝም። የቀጠሮው ጊዜ ፫ ወራት እንደመሆኑ አንድ የማያመች መላ መፍጠር እንዴት ያውከኛል ምናልባትም ይሆናል›› እያልኩ በሐሳብ ባሕር ተውጬ በወህኒ ቤት ውስጥ ጥቂት ቀናት ቆየሁ። በተጨማሪም በነዚህ ቀናት ውስጥ አብረውኝ ታሥረው ከነበሩት ብዙ ዩጎዝላቪያኖች እንግሊዞች መስኮቦች አሜሪካኖችና አረቦች ጋር መተዋወቅ ቻልኩ።

በዚህ ጊዜ ሁሉ የእንግሊዝ አይሮፕላን ቀን በቀን እየመጣ በወህኒ ቤት አቅረቢያ የሚገኘውን መንደር በቦምብና በመትረየስ ሲደበድብ ኢጣሊያኖች በየቤቱና በየቤተክርስቲያኑ ያኖሩት የጦር መሣሪያ ያለማቋረጥ ሲፈነዳና ሲጮህ ይውል ነበር። በወህኒ ቤቱም





ውስጥ ‹‹እሥረኞቹና በዘበኞቹ መካከል የሚታየው ሽብር ይህ ነው ተብሎ የሚነገር አልነበረም።

እንደ አጋጣሚ ሆኖ በተለይ ጁሴዎታቼክ ከተባሉ የዩጎዝላቪያ ተወላጅ ናቸው እርሳቸው እንዳጫወቱኝ በትውልድ ሀገራቸው ቤተሰብ ያላቸውና የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ ሲሆኑ ማዕርጋቸውም በዚያን ሰዓት የመቶ አልቅና ነበር። እንዲሁም 1.55 ቁመትና 40 ዓመት ዕድሜ ነበራቸው። በአርበኝነት ተግባራቸውም ላይ ስለ ቆራጥ ጀግንነታቸውና ስለ ፈጸሙት ጀብዱ ወደ ፊት በምንገልፀው ታሪካቸው እናስረዳለን።

እኔና ዩጎዝላቪያዊው ጁሴዎታቼክ ወዳጅነታችን ፈጥኖ እየተቃረበ መሄዱን ስገነዘብ አንድ ቀን በተለመደው ሰዓት ለነፋስ ወጥተን ስንመለስ ከወህኒ ቤቱ ጠፍቼ ለመሄድ የነበረኝን ቁርጥ ሐሳብ ገለጽኩላቸው። ጁሴዎታቼክ ንግግሬን በእርጋታ ካዳመጡኝ በኋላ በጉዳዩ እንዲያስቡበት ጠየቁኝ። በማግሥቱም እንዲሁ ከነፋስ ስንመለስ እንዲህ የሚል መልስ ሰጡኝ።

‹‹ከዚህ እሥር ቤት ቢቻልህ ለማምለጥ ባይቻልም በሙከራው ላይ ለመሞት ባቀረብከው ሐሳብ እስማማበታለሁ። አንተ ለመሞት የቆረጥክ ሰው ከሆንክ እኔም እንዳንተው ለሞት የተዘጋጀሁ ቆራጥ መሆኔን እንድታውቀው እፈልጋለሁ። ብቻ ዋናው ዓላማችን በሕይወት



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመጥፋት ስለሆነ ብዙ በቀደምት ልናስበበት የሚገባ ነገር አለ፡፡ ፩ኛ በዚህ ወህኒ ቤት የታሠሩ እንደኛው የመሰለ ሐሳብ ያላቸው ዩጎዝላቪያኖችና ሌሎችም የፖለቲካ እሥረኞች ስላሉ ዕቅዳችንን ለእነርሱም ብናማክራቸው አይከፋም፤ ጠፍተን ከወጣን በኋላ ቁጥራችን የበረከተ ቢሆን የተሻለ ይሆናል ለማለት ነው››፡፡

‹‹ሐሳብዎ መልካም ነው››፡፡ አልኳቸው፡፡ እኔም በበኩሌ ‹‹ሆኖም እርስዎ ያልተገነዘቡት አንድ ነገር አለ፡፡ ይኸውም የጊዜ ጉዳይ ነው አንደኛ እንደሚመለከቱት ጦርነቱ እየተፋፋመ በመሄድ ላይ ስለሚገኝ ኢጣሊያኖች ቀለብ በማቅረብና እኛን ከማንቆራጠጥ ፈንታ ፈጅተውን ወደ ጦር ሜዳ እንደሚሄዱ ይወቁ፡፡ ሁለተኛ በየቀኑ የሚሰጠን የቀለብ ራሽን እየተቀነሰ መሄዱን ያያሉ ታዲያ የምንጠባበቀው በችጋር የምናልቅበት ቀን እስኪመጣ ነውን? እንደኔ ከሆነ ለሚመስሉዎት እሥረኞች ጉዳዩን ያጫውቷቸውና በአስቸኳይ ከዚህ ወህኒ ቤት ጠፍተን እንውጣ››፡፡ የሚል አስተያየት ሰጠኋቸው፡፡

ከዚህ በኋላ እየተገናኘን በጉዳዩ ስንመክር ቆይተን ሳለ የእንግሊዝ አይሮፕላኖች መጥተው ቦምብ መጣል በሚጀምሩበት ውድቅት ከዘቦቹ መሣሪያ ዘርፈን ለምለጥና እስከዚያው ሁሉም የመሹለኪያውን ዘዴ ለየራሱ እንዲያስብበት ተስማምተን ተለያየን፡፡ ሁለታችን ግን ተከሉና ሽብሩ እንደ ጀመረ ከክፍላችን ወጥተን የምንገናኝበትን ሥፍራ ለይተን ወስነን ነበር፡፡





አንድ ቀን በ፮ ሰዓት ላይ እንዲሁ በወህኒ ቤቱ ግቢ ውስጥ ስንዘዋወር አንዲት የእንግሊዝ አይሮፕላን በከፍተኛ ርቀት እየተገለባበጠች ስትበርር ባየን ጊዜ የእንግሊዝ ጦር ወደ ኢጣሊያ መግባቱን ያለጥርጥር ተረዳን፡፡ ምክር የተከፋፈልነው ሁሉ ዛሬ ነገር እንዳለ አወቅነው፡፡ በዚያን ዕለት እስከ ቀኑ ፲ ሰዓት ድረስ የአደጋ ምልክት ሲነፋ ስለዋለ በሽብርና በዋካታ ምድረ ግቢው ተናወፀ፡፡ በሁለተኛው ቀን እኩለ ሌሊት ላይ የእንግሊዝ አይሮፕላኖች ሳን ቤሮ የተባለውን የጀርመን ጦር ወታደር ያሰበትን ሠፈር መደብደብ ጀምረው 30 ደቂቃዎች ያህል እንደቆዩ እኛ ባለንበት ወህኒ ቤት ላይ ቦምብ መጣልና መትረየስ መተኮስ ቀጠሉ፡፡ በመትረየስ ለመምታት ያመችም ዘንድ የሌሊት መብራቶችን አከታትለው ጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከወህኒ ቤቱ ዘበኞች በኩል አንድም የተኩስ መልስ ሲሰጥ አይሰማም፡፡ እንደመሰለኝ ብዙዎቹ ሲሸሹ የቀሩት ደግሞ በየመጠጊያው ተከልለዋል፡፡

በዚህ ነፍስና ሥጋ በሚሟገቱበት ወቅት አንድ ሐሳብ መጣልኝ፡፡ ያለሁበት የፎቅ ክፍል እሥር ቤት መስኮት ከውስጥ ተከፋች ሆኖ ብረት የለውም እሥረኞችም ጥዋት ማታ የሚጠበቁት ከማማ ላይ ቆመው መትረየስና ባውዛ መብራት ብቻ በደገኑ ዘበኞች ነበር፡፡ ባልተፈቀደ ሰዓት ከእሥር ቤቱ ወጥቶ የተገኘ እሥረኛ መገደል ብቻ ነበረበት፡፡ ይሁንና አሁን ጊዜው ተለውጧል፡፡ ዘበኞቹም ራሳቸውን



t.me/OLDBOOKSPDF

ለማዳን መከላከልን ትተው እሥረኞችን እንደማይጠባበቁ እምነት አደረብኝ፡፡

ስለዚህ የለበስሁትን ብርድልብስ እየተለተልኩ በቁጥር ካገኘሁት በኋላ አንዱን ጫፍ በመስኮቱ ላይ አስሬ ቁልቁል ወርውሬ በዚያ እየተሳብኩ ወረድኩ፡፡ መሬት እንደ ደረስኩ የቤቱን ግድግዳ ተደግፌ ግራና ቀኝ ባስተውል ጨለማው ምንም የሰው ምልክት ሊያሳየኝ አልቻለም፡፡ አጐንብሼ በፍጥነት በመሮጥ ጁሌዎታቺክ ጋር ለመገናኘት ወደ ዩጎዝላቭ እሥረኞች ሠፈር ደረስኩ፡፡ ጥቂት አድፍጬ እንደቆየሁ በአነስተኛ ድምፅ ‹‹ጁሊ ጁሊ›› ብዬ ስጣራ እርሱም እኔን በመጠበቅ ላይ ነበር በዳበሳ ወደ እኔ ቀርቦ ተገናኘን፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

[illegible]/A147-[illegible]

Head Quart[illegible] Allied Commission
[illegible] 1941

Displaced persons and repatriation sub-commission DPRK/10-11-6/
[illegible]/[illegible] Tel. 480031 EXT. 239-240-241.

20th, February 1947.

To His Ethiopian Majesty's Minister,
Cairo - Addis Ababa.

1. The bearer of this letter Major Abdiasa Aga an ex-pupil of the Ovalletta Military School has been a political prisoner in Italy and Ethiopia since the attempt on Graziani's life in 1937 A.D.

2. On Fascism's fall and when Italy sued for an armistice, Major Abdiasa Aga escaped from the concentration camp at Treia and joined a Partisan Band of British-Yugoslavs, South Africans and others to fight in the best tradition of those Ethiopian Patriots who kept their flag flying during the darker days of the Italian occupation of their country. He is in possession of laudatory certificates from the officer commanding the patriot unit and of a "Patriots Certificate" issued by Field-Marshal Sir Harold Alexander, supreme Allied Commander in the Mediterranean theater of operations.

3. I feel that Major Abdiasa's outstanding services to the Allied cause under difficult condition deserve to be brought to the notice of His Majesty the Emperor and would be personally grateful if you would so recommend to the appropriate Ethiopian Government Department.

Yours sincerely,

[signature]

Col.

Copy to:

Major Abdiasa Aga

Italy.

t.me/OLDBOOKSPDF

እሱ እጄን ይዞ እየሳበኝ በደረታችን ስንጐተት ሄደን እ'ስቱን ዩጎዝላቪያውያን እሥረኞችና  እንዲሁም ካሣዬ አብጤ ካርሎ አባ መጋል የተባሉትን ኢትዮጵያውያን እሥረኞች ካሉበት ክፍል አውጥተን በወሕኒ ቤቱ አጥር ሽቦ ላይ እየተንጠላጠልን ስንወርድ ዘበኞቹ ነቅተው ተኩስ ከፈቱብን፡፡ በዚህም ጊዜ ብዙዎቻችን ከአጥሩ ዘልለን መሬት መድረስ ብንችልም የመትረየሱ እሩምታ ተኩስ አንዱን የዩጎዝላቪያ እሥረኛ ገና በመውረድ ላይ እነበረበት አጥር ላይ ገንጥሎ ሲያወርደው እንዲሁም አቶ አሰፋ በለው የተባለው ኢትዮጵያዊ በጥይት ተመትቶ ወዲያውኑ ሕይወቱ አለፈች፡፡ የተረፈው ግን መሬት ለመሬት በመሳብና አንዳንድ ጊዜም እየተነሣን በመሮጥ ወደ ሳንብችና አቅጣጫ ስንጓዝ አድረን በማግሥቱ ጥዋት በግምት ፱ ሰዓት ላይ ከአንድ ምድረ በዳ የሆነ ሥፍራ ደረስን፡፡

ይህ ክፍለ ሀገር በረሃማ እንደመሆኑ መጠን ከረሃብ ይልቅ የውሃ ጥማት ሊሰማን ጀመረ፡፡ ሆኖም ጉዞአችንን ቀጥለን ወደፊት እንዳመራን በአምላክ ፍቃድ አንድ ትልቅ ጅረት አጋጠመን፡፡ ሁሉም እያጐነበሰ የጥሙን ያህል ጠጥቶ ከረካ በኋላ እንደፍላጎቱ በመታጠብ ሰውነቱን አቀዘቀዘ፡፡

ጥቂት እፎይ ብለን ግራ ቀኝ ስንመለከት ከጅረቱ አቅራቢያ ከሚገኝ የሣር ሜዳ ላይ የሚግጥ የከብት መንጋ አየን፡፡ ወደዚያው እየተጠጋን ስንቃረብ የመንጋው ጠባቂዎች የሆኑ አንድ በፈረስ





የተቀመጠ ሽማግሌና አንድ ልጅ እግር እረኞች አገኘን፡፡ ሁ'ቱም አንዳንድ የአውሬ ማደኛ ረሽ ከበረከት ጥይት ጋር ይዘው ነበር፡፡ በመጀመሪያ ወደ ሽማግሌው ሰው ቀረብንና የሚበላ እህል እንዳለቸው ቢሰጡን ብለን ጠየቅናቸው ሽማግሌው ሰው ብዙ አሳመነታም ያለ ብዙ ችግርና ቅሬታ ከፈረሱ ወርዶ የምግባቸውን ቅርጫት ረሽ ጠብ መንጃቸውንና ጥይታቸውን ወዳኖሩበት ቦታ እልፍ ሲል እኛም ተከተልነው፡፡ ወዲያው ቅርጫቱን ከፍቶ ለስንቅ የያዙትን አራት ኪሎ ዳቦና ሁለት ጠርሙስ የወይን ጠጅ ሰጥቶን ተከፋፍለን እንድንመገበው አዘዘ፡፡ በዚህ ጊዜ የተመለከትኩት የሽማግሌው ሁኔታ አሁንም ይታወሰኛል፡፡ ከመካከል ቆሜ የደረሰኝን የዳቦ ቁራሽ ስገምጥ በድንገት የእኔና የሽማግሌው ዐይን ገጠመ፡፡ ግንባሩን ኮስተር ዐይኑን ትክ አድርጎ በመገረም አፍጥጦ ይመለከተኛል፡፡

እኒያ ትልቁ ደራሲ አቶ ከበደ ሚካኤል ‹‹ቹሌ›› ስለተባለው የፋሺስት ተወላጅ በጻፉት ልብ ወለድ ታሪክ ውስጥ ‹‹ከእሥረኞች ጋር ሁሉም ዳቦ ጉርሰው ሲበሉ አየኋቸው ጥቁሮችም እንደሰው››፡፡ የሚለውን ቃል ሀገሬ ተመልሼ ከመጣሁ በኋላ ስመለከተው ታሪኩ እርግጥ ልብ ወለድ መሆኑ አጠራጠረኝ፡፡

ዳቦአችንን ጐርሰን የወይን ጠጃችንን በተራ በማፈራረቅ ደርሶን በመጎንጨት ዕቃዎቹ ሲጋቡ የእረኞቹን መሣሪያዎችና ፈረሶቻቸውን

ቢቻል በልጥና ካልሆነ በግዴታ ለመንጠቅ ስንወ ክር ሽማግሌው ሰው ጥያቄ አቀረበልን፡፡

‹‹ስመለከታችሁ ከሩቅ አገር የመጣችሁ ይመስለኛል መልካችሁም ቀለም የተለያየ ነው ከየት ነው የመጣችሁት?

‹‹እንዳልከው ከሩቅ አገር የመጣን መንገደኞች ነን፡፡ ቀለማችን ቢለያይም ሁላችንም የአንድ አገር ዜጋ የሆንን የጦር ስደተኞች ነን፡፡ ይልቅ አሁን የምንሄድበት አገር ገና የብዙ ቀናት ጉዳና የቀረው ስለሆነ ፈረሶቻችሁንና ረሻችሁን ብትሰጡን? የማለት ልመናችንን ልናቀርብላችሁ አስበናል፡፡ ጥያቄያችንን ብትቀበሉን ከልብ እናመሰግናለን›› በማለት ሐሳባችንን ለሽማግሌው እረኛ ስንገልጽለት በንዴት እንደ መብረቅ እየጮኸ ይንጒራደድ ጀመር መዳፉን ጨብጦ ዐይኖቹን አፍጥጦ አንገቱን ደፋ ቀና በማድረግ

‹‹የተራባችሁና የተጠማችሁ መንገደኞች ናችሁ በማለት የያዝነውን ስንቅ ሰጥተን ባስተናገድን እንደገና ፈረስና መሳሪያ አምጡ ትሉኛላችሁ? ለመሆኑ ለራሳችን ከአውሬ የምንከላከልበትን መሳሪያ አሳልፈን እንድንሰጣችሁ ትፈልጋለችሁ? እንዴት ኃፍረት የላችሁም? እንዲያውም ወንበዴዎች ትመስሉኛላችሁ››፡፡ እያለ ሲጮኽ ከመካከላችን አንዱ ‹‹እኛ ይህን ልመና ያቀረብንልዎ መቼም እርስዎ ያሉት በአገርዎ በወንዝዎ ስለሆነ ለእኛ ለመንገደኞቹ ፈረሶቹም ሆነ





መሣሪያዎች የበለጠ ይጠቅሙናልና ቢረዱን ብለን ነው›› የሚል ምልስ ሰጠው፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም ያንኑ ዘለፋውንና ጩኸቱን ስለ ቀጠለ ጥያቄያችንን ፈቅደው የማይፈጽሙ ከሆነ በማስገደድ ኃይል የምንጠቀም መሆናችንን ስንነግረው ረሹን ለማንሣት ሮጠ፡፡ በዚህም ጊዜ ከእርሱ ይልቅ እኔና ጁሌዎታቼክ ለመሣሪያው ቀርበን ቁመን ስለ ነበር ሁለታችንም አንዳንዱን አንስተን ፈንጠር እያልን ስንቆም ሁለቱም ለማምለጥ ፈረሶቻቸው ላይ ወጥተው ግልቢያ ሲጀምሩ ወጣቱ ከነድንጉላው ፈረስ ሲገደል እንዲሁም ሽማግሌው በጥይት ከፈረሱ ላይ ወርዶ ሲሞት ፈረሱን ሳያመልጥ ያዝነው፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ ጉዞአችንን ቀጠልን፡፡ የፀሐዩ ንዳድ እየወረደብን መንገዳችንን ስናመራ ከቀትር በኋላ በግምት ፲ ሰዓት ላይ የሞተውን ሽማግሌና ልጁን ለመጠየቅ ረሹንና የስንቁን ቦርሳ አንግቶ በፈረስ እየጋለበ መጣ እንደደረሰ የሚሄድበትን አድራሻ ብንጠይቀው ፊት ወደተገደሉት እረኞች ዘንድ መሆኑን አስረድቶን በመንገድ ስናልፍ ተገናኝተን እንደሆነ በማለት ጠየቀን ሆኖም ፈረሱን ሲያይ ጥርጣሬ ተሰማው፡፡

‹‹አይዞህ አትደንግጥ›› አለው አንዱ ባልደረባችን ‹‹ሰዎቹ በሰላም ከብቶቻቸውን በመጠበቅ ላይ ናቸው፡፡ እንዲያውም በሁኔታችን ተጸጽተውልን መሣሪያዎቻቸውንና ይህን ፈረሳቸውን ሰጥተውናል›› ፡፡ ካልነው በኋላ ወደ ሳንቢችኖ ተራራ የሚያደርሰውን አቋራጭ መንገድ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲመራን ጠየቅነው። እሥር ቤት ውስጥ በነበርን ጊዜ ብዙ የፋሺስት ተቃዋሚ አርበኞች በዚህ ተራራ ላይ መኖራቸውን ስምተን ስለነበር ከነርሱ ጋር ለመቀላቀል አሳብ ነበረን። ቢወድም ባይወድም እሺ ከማለት በቀር ሌላ መንገድ እንደሌለው ስለተገነዘበ መሣሪያውንና ፈረሱን አስረክቦን ቀደመ።

በእርሱ መሪነት ሌሊቱን ስንገሥግሥ አድረን ከእሥር ቤት አምልጠን በወጣን በ፫ኛው ቀን ጨለማው ለቅቆ ብርሃን ወጋገን ሲታይ ከሳንሺችኖ ተራራ ከመድረሳችን በፊት ኪኛኖ ከተባለው መንደር ዳርቻ ተቃርበን ጥቂት እረፍት አደረግን። የስንቅ ችግርና ድካም ተሰምቶን ስለነበር ገሚሱ ወደዚህች መንደር እንግባ ሲል ሌሎቹ ደግሞ ለሕይወታችን ያሰጋል እና አልፈን ወደ ተራራው መውጣቱ የተሻለ ይሆናል በማለት በመመካከር ላይ እንዳለን አንድ የከተማ ተላላፊ ሰው አገኘንና አቆምነው።

ሰውየው መካከለኛ ዓመት ዕድሜ ያለው የገጹ ደም የጠራ ቁመናውና አለባበሱ ያማረ በጠቅላላው ሙሉ ጀግና ቢመስልም ገና ሲያየን ደንግጦና አፉን ከፍቶ ዐይኖቹን አጉርጦ ይመለከተን ጀመር። በኋላ እንዳስረዳን ለዚህ ድንጋጤ ያበቃው ከተራራው ላይ ወርደን ከተማዋን ለመያዝና ለመዝረፍ የመጣን አርበኞች መስለነው ነበር።





ንግግር ጀምረንለት ድንጋጤው ካሸሸ በኋላ ስለመንደሪ ነዋሪዎችና በተራራው ላይ ስለሚኖሩ አርበኞች ሁኔታ እንዲያስረዳን ጠየቅነው። እርሱ እንደገለጸልን በዚህች መንደር ውስጥ ጥቂት የፋሺስት ወታደሮች እንደሚገኙና በተራራውም ላይ ብዙዎች የእንግሊዝ የፈረንሳይ የአሜሪካ እንዲሁም የኢጣሊያ የፖለቲካ ስደተኞች ጭምር መኖራቸውን ለማረጋገጥ ቻልን። ወደ አርበኞቹ ዘንድ መርቶ እንዲያደርሰን ብንጠይቀው ግን አድራሻቸው በምንም ዐይነት እንደማይታወቅና እንዲያውም ወደዚያ ደፍሮ ከመጠጋት ሞቱን የሚመርጥ መሆኑን እየተንቀጠቀጠ ሲናገር እርሱን በማስገደድ ይዘን ጉዞአችንን ቀጠልን።

የብዙ ሰዓቶች መንገድ ሳንሄድ ደረቱን ገልብጦ የሚመለከተንን የሳንሚቼኖ ተራራ ደፋ ቀና እያልን ተጋጠምነው፤ ተራራው ድንጋያማ ቢሆንም በዛፎችና በቁጥቋጦ የተሸፈነ ነው። የሚያስገርመው ይህን ተራራ አጋምሰን ሳንወጣ ከየት እንደ መጡ ልናውቅ ያልቻልነው የአርበኞች ቃፊሮች ዙሪያችንን በመከበብ ካለንበት እንዳንንቀሳቀስ ማስጠንቀቂያ ሰጡንና መሣሪያችንንም አስቀምጠን እጃችንን እንድናነሣ ጠየቁን። እንደ ጥያቄያቸው ፈጸምን፤ ወዲያው ሁለቱን የረሸ ጠብመንጃችንን እያነሱ እንያንዳንዳችንን ፈተሹን፤ ቀጥሎ መንገድ እንድንቀጥል ታዘዝንና ከቃፊሮቹ አዛዥ እንግሊዛዊው ሜጀር ፋይል ዘንድ ቀረብን።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሜጀሩም ከየትኛው አውራጃ ጦር ቤት እንዳመለጥን ከእሥር ቤቱ ከወጣን ስንት ቀን እንደሆነን እያንዳንዳችን የታሠርንበትን ጊዜ ብዛት የእያንዳንዳችንን ዜግነት የያዝነውን የረሽ መሣሪያዎችና ፈረሶች ከየት እንዳገኘናቸው ሌላ ሌላ ጥያቄዎች አቅርበውልን ትክክለኛውን መልስ ከሰጠናቸው በኋላ በበኩላችን ጥያቄ እንዳለን ማቅረብ እንደምንችል ገለጹልን፡፡ ሁሉም በየበኩሉ የተቸገረበትን ቢጠይቅም ለጊዜው የማስታውሰውን በበኩሌ ስንዝሬ ያገኘሁት መልስ እንዲህ የሚል ነበር፡፡

ጥ: «ከእሥር ቤት ጠፍተን ለመውጣት ያነሳሳን ዋናው ምክንያት በሕይወት እስካለን ድረስ በኅብረት ሆነን የፋሺስትን ኃይል በአለን ኃይል ለማድከም ነው ስለዚህ አሁን እንደሚያዩን እኛ ባዶ እጃችንን ስለሆነ መሣሪያዎች እንዳለዎ አከፋፍለውን ከእናንተ ጋር በአርበኝነት እንድንሠራ አይፈቀድልምን?

መ: አንተ እንደጠየቅኸን የጦር መሣሪያዎቹ ቢኖሩንና ለእያንዳንዳችሁ እንዲዳረሱ ብናደርግ ደስ ባለን ነበር፡፡ ነገር ግን እኛም እንደናንተው ከእሥር ቤቱ አምልጠን ከወጣን ገና አንድ ወር ጊዜ ብቻ ያላለፈን ሲሆን ያሉን መሣሪያዎች ከአንድ ፋሽስት ወታደር የነጠቅነው አንድ የአልቢን ጠብመንጃ ከ፲፪ ጥይት ጋር አንድ ፊሻሌ ሽጉጥ ከ፮ ጥይት





ጋር እንዲሁም በገንዘብ የተገዙ ፫ የእጅ ቦምቦች ብቻ ናቸው፡፡ እንግዲህ እኛ ፴ ሰዎች ስንሆን ለጊዜው የቆጠርኩልህ መሣሪያዎች በእጃችን ይገኛሉ ታዲያ በምን ዐይነት ልንረዳችሁ የምንችል ይመስላችኋል?



አብዲሳ በጦር ሜዳ በዚህ ዓይነት ልብስ ይጠቀም ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥ፡ በዚህ ተራራ ላይ ያሉት አርበኞች ብዙዎች ናቸው ማለትን ሰምተን ነበር?

መ፡ እርሱስ ነበር፡፡ ግን እኛ ስንደርስ እንደሰማነው ይህንን ተራራ ለቅቀው ወደ ሌላ ስፍራ ተዛውረዋል፡፡ እነርሱማ ቢኖሩ ምንም ችግር ባልገጠመን ነበር፡፡

ጥ፡ ይህ እንዲህ ከሆነ መሣሪያ ወደሚገኝበት ሄደን ዘርፈን እንድናመጣ ከርስዎ ሰዎች ጥቂቶቹን አይሰጡንምን?

መ፡ አሁን እናንተም ሆናችሁ እኛ ገና ድካማችን ያልለቀቀን እሥረኞች ነን፡፡ ስለዚህ ለማናቸውም የዛሬን እረፍት አድርገን በጉዳዩ ነገ እንነጋገር ብለውን ወደማረፊያቸው ዋሻ ወሰዱን፡፡ አዳር ተደረገና በማግሥቱ ጠቅላላ ስብሰባ አድርገን መመካከር ተጀመረ፡፡ በበኩሌ ባቀረብኩት ሐሳብ ለጊዜው የምንገኘው በባዕድ አገር ላይ ሲሆንና ፋሺስቶችም አርበኛ የተባለውን ሁሉ ለማጥፋት ዱካችንን ለማግኘት በሚጣደፉበት ወቅት በተአምር የጦር መሣሪያ እስክናገኝ እጃችንን አጣምረን መቀመጥ የለብንም፡፡ ይልቁንም ፋሺስቶች እስካለንበት መጥተው ቢማርኩን በተለይ እኔን ጥቁር በመሆኔ ከመማረክ ይልቅ በሰከንድ ውስጥ እንደሚገድሉኝ እርግጠኛ ነኝና ፍቃደኛ የሆኑት ተከትለውኝ





የጦር መሳሪያ ማግኘትና ሕይወታችን ለሳካለፈ ድረስ የጠላትን ኃይል ማድከም አለብን የሚል አስተያየቴን ሰጠሁ፡፡

ሐሳቤ የሜጀር ፋይልንና የአብዛኛውን አርበኞች ድጋፍ ከማግኘቱም በላይ ፳፮ የዩጎዝላቪያና ፱ የእንግሊዝ ወታደሮች አብረውኝ ሊሄዱ ቆርጠው ተነሡ፡፡ እጃችንም ባዶ እንዳይሆን በማለት ከቦምብ ከረሽ ከጠብመንጃና ከሽጉጥ አንስቶ እስከ ወይን ጠጅ ጠርሙስና ድንጋይ ድረስ ሁሉም ያገኘውን ይዞ ነበር፡፡ ከሜጀር ፋይል ጋር ወደ ኋላ ለቀሩት ግን አንድ ረሽ ከ፴ ጥይት ጋር አንድ ቦምብና አንድ ሳንጃ ትተንላቸው ሳን ሎሬንሶ ወደ ተባለው የእሥር ሠፈር ከምሽቱ ፩ ሰዓት ሲሆን አገሩን ቀደም ብለው በሚያውቁት ሰዎች መሪነት ጉዞ ተጀመረ፡፡

ያለንበት የሳንሎሬንሶ ተራራ እኛ ከምንሄድበት አድራሻ በግምት የ ፲፭ ኪሎ ሜትር ርቀት የሚቀረው ስለነበር የተዋጊዎቹ ቅደም ተከተል እንዲዘጋጁ ተደረገና ዋና አዛገችን ጁሊዮ ሆኖ እኔ ከ፲፭ ሰውና መሣሪያ ጋር ግምባር ቀደምትነቱን ይዤ ጉዞው ቀጠለ፡፡ ለማጥቃት ያሰብነው ምሽግ እኔ ከዚያ በፊት ታሥሬበት የነበረ የእሥረኞች ሠፈር ነው፡፡ ከዚህ እሥር ሠፈር ለመድረስ በግምት የ2 ኪሎ ሜትር ተኩል ርቀት ሲቀር የመብራቱና የስልኩን መሥመሮች



t.me/OLDBOOKSPDF

በጉጠት በጣጥሰን ከግቢዉ ዋና በር በስተጀርባ በኩል ለመግባት ዋናውን መንገድ መልቀቅ ስንጀምር ያልታሰበ በረዶ መጣል ጀመረ፡፡

ይህ ሲሆን እግዚአብሔር እኛን ሊረዳን መፍቀዱን ሲያስገነዝበኝ ቻለ፡፡ ስለዚህ በግቢው መግቢያ በር በስተጀርባ በኩል ለመግባት የጀመርነውን መንገድ ትተን በዋናው በር ለመግባት በማለት ወደኋላ ተመለስን፡፡ የግቢው ዘብ ወደቆመበት ሥፍራ አካሄዳችን በሆዳችን ተኝተን እንደ ነብር በመሳብ ነበር፡፡ ከበሩ ስንጠጋ እንገቴን ቀና አድርጌ ብመለከት አንደኛው ዘብ ብቻ ቆሞ ሲጠብቅ ሌሎች ጥቂት ዘበኞች ደግሞ እልፍ ብሎ በሚገኝ ዛኒጋባ ውስጥ መተኛታቸውን ተመለከትኩ፡፡ ነቅቶ የሚጠባበቀው ዘብ ብረቱን በጀርባው ተሸክሞ እጆቹን በካፖርቱ ኪሶች ውስጥ በመክተት በዘብ መቆሚያው ውስጥ እንደቆመ ሳያስበው ጥልቅ ብዬ ስይዘው የእንቅልፍ ሽውታ ይዞት ነሮ በድንጋጤ ሲባንን ተክትለውኝ የነበሩት ሳጂን ሜጀር ዱግላስ የተባሉ እንግሊዛዊ ጉሮሮውን አነቁት፡፡ በዚህም ጊዜ ብረቱን ነጥቄው ሁለቱን እግሮቹን በመያዝ ከሳጂኑ ጋር ተጋግዘን ወደ አንድ ጉድባ ወስደን አንገቱን በመጠምዘዝ ገደልነው፡፡ መሞቱን ለማረጋገጥም ያህል ሆዱን በሳንጃ ሽረክትነው ሳጂን ሜጀሩ የሟቹን ዘብ ልብስ አውልቀው ለብሰው ከዘብ መቆሚያው ሥፍራ ስንደርስ እርሳቸው ዘብ በመምሰል ሳንጃ የተሰካበትን ብረት ይዘው ቆሙ፡፡ በዚያ ሰዓት የነበረው የበረዶ





ው?ነፍር መዓት ነው፡፡ ነፋሱ ያፏጫል የመስኮት መዝጊያዎች ይንቀጠቀጣሉ፡፡ የእሥር ቤቱም በአርበኞች ተወረረ፡፡

የዘቦቹ አለቃ በመጠራጠር ይመስለኛል የእሥር ዕልቅና ማዕርጉን እንዳዳረገ ሲጠጋቸው አንገትን ሲያንቁት እኔም ካደፈጥኩበት ደረስኩና ተረዳድተን በማፈን ገደልነው፡፡ ሌሎቹ ተከታዮቻችን ደግሞ እኛን አልፈው ሄደው ነሮ የቀሩት ዘበኞች እንደ ተኙ ደርሰውባቸው ሁሉንም በሳንጃ ጭጭ አድርገዋቸው አንዱን ብቻ ለመረጃነት እንዲረዳ በሕይወት ማርከው ቆዩን፡፡ የተገኘውንም መሣሪያ ሁሉ እያማረጥን በእጃችን ስናገባ እኔ አንድ ድግን ቀላል መትረየስ ደረሰኝ፡፡

* * *

የተማረከው ዘበኛ ወደ ዋናው አዛዡ መኖሪያ እንዲወስደን ተነገረውና ከአንድ ፎቅ ቤት ደረስን፡፡ ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲጠራው አዘዝነው፡፡ ምርኮኛውም እንዳይቃወመን ሕይወቱን ወዲያውኑ እንደሚያጣት ያውቀዋልና በፍርሃት እየተንቀጠቀጠ ‹‹ማርሻሎ ማርሻሎ›› ሲል ተጣራ፡፡ ዋና አዛዡ እንዲሁ በተመሳሳይ ድምፅ ‹‹ምን ሁነሃል? ›› በማለት ቢጠይቅ ከካምፑ ግርጌ የብዙ ሰው



t.me/OLDBOOKSPDF

ኦምፅ ስለምሰማ ይህንኑ እንድነግር ከእሳቃዬ ታዝገፔ ነው የሚል መልስ ሰጠው።

ዋና አዛዡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የአልጋ ልብስ ለብሶ ከፎቁ በረንዳ ላይ ወጣ ፤ መብራቱ አስቀድሞ ስለ ተቆረጠበት በእጁ የባትሪ መብራት ይዟል። ይህንንም መብራት በእኛ ላይ ሲያበራ በያዝኩት መትረየስ ውስጥ የነበሩትን ፳ ጥይቶች በደረቱ ላይ ሳራግፍበት በጀርባው ተንጋለለና ከዚያው ከቆመበት በረንዳ ላይ ወደቀ።

የጥይት ድምፅ የሰሙት ፫ ሴቶችና ፬ ሕፃናት ከመኝታ ቤታቸው እየተሯሯጡ ወጥተው ሬሳውን በመከበብ ይጯጯሁ ጀመር። በኋላ እንደሰማሁትና ልረዳ እንደቻልኩት ሁለቱ የሚቼ እኅቶች ሲሆኑ አንዲቷ ሚስቱ ሕፃናት ደግሞ ልጆቹ ነበሩ። የቀሩትም በግቢው ውስጥ በየክፍሎቻቸው ተገኝተው የነበሩትን ወታደሮች በሙቶ አለቃ ጁሊዮ ኢታቺክ የሚመሩት ተከታዮቻችን እየተደናበሩ ሲሯሯጡ በጥይት አለቁ።

ይህን ሁሉ ተአምራት ስመለከት አዲስ አበባ ውስጥ በፋሺስቶች የተፈጸመውን ግፍ አስታወስኩ። አዎ ብዙዎች ጀግኖች ሳያስቡት በሰላም ከተቀመጡበት ቤታቸው ውስጥ በጥይት ተፈጅተዋል። በሰደፍ በአካፋና በዶማ ድብደባ ሕይወታቸውን አጥተዋል። እልቂቱ ሴት ወንድ ልጅ ሽማግሌን አላማረጠም። ወላጆችና ቤተ ዘመዶች የሟች





ቤተሰቦቻቸውን ሬሣ ለማንሣት እንኳ ሳይቻላቸው የቀረበት ክፉ ቀን ነበር። ይሁን እንጂ እኔ ደግሞ በፈጣሪ ትእዛዝ ወደማላውቀው አገር ተልኬ የወገኖቼን ደም ለመበቀል በመቻሌ የአምላክን ፍርድ አደነቅሁ።

በእሥር ቤት ቅጽር ግቢ ውስጥ ከእኛ በኩል አንድም ሰው ሳይነካ ሙሉ ባለሥልጣንነት ከተቀዳጀን በኋላ ለመሪነት ያስቀረነውን ዘብ በፍርድ የሞት ቅጣቱን እንዲቀበል ተወስኖ በሙቶ አለቃ ጁሊዮ ኢታቺክ እጅ በጥይት ተደበደበ። የቀጠለው ተግባራችን ደግሞ ግምጃ ቤቶቹን ከፋፍተን የተገኘውን ልብስ ምግብ መሣሪያና ጥይት ሁሉ ካወጣን በኋላ ከእሥር ቤቱ ውስጥ በተገኘው አንዲት ፊያት ትሬንታኳትሮ መኪና ላይ መጫንና ወደመጣንበት ምሽግ መላክ ነበር በዚያን ዕለት የተገኘውን ምርኮ በያዝነው ማስታወሻ መሠረት እንደሚቀጥለው ሆኖ አግኝተነዋል።

ይህ ተከናውኖ እንዳለቀ እሥረኞች ታሥረው ሲጯጯሁ የነበሩበትን ክፍሎች እየከፈትን እሥረኞቹን በነጻ ለቀቅናቸው።

* * *

እሥረኞቹ ተለቅቀው ሲወጡ ፈጥነው በመሄድ ፈንታ በደስታ ስሜት እየተቃቀፉ ዘፈን በመዝፈን ይፈነጭሩ ጀመር። አዛዦቹና ታዛዦ ጠፍቶ



t.me/OLDBOOKSPDF

በደኅታ መንፈስ የተዋጠው እሥረኛ ገሚሱ ሲሯሯጥ ገሚሱ ወጥቶ የሚሄድበትን ቆሞ ሲያሰላስልና ሲመካከር የቀረውም የወደቀ መሣሪያና ዕቃዎችን ለማንሣት ጉድ ጉድ ሲል ያልታሰበ የመትረየስ እሩምታ ተኩስ ከአንዲት ሰብቻዋ ከቆመች ክፍል ቤት መስኮት ላይ ወረደበት። በዚህም ጊዜ በጥይት የተመታው ደህናውም ሰጥ ብሎ ከመሬት ላይ ተኛ።

እኔና ጁሴዎታች እንዲሁም ሌሎች አራት ወታደሮች ተጠቃቅስን በደረታችን እየተሳብን ከኋላ በኩል ዙረን ተኩስ ከፈትን። በዚህም ጊዜ አንድ ሰው በጥሩ አውቶማቲክ መሳሪያ በመስኮት ብቅ እያለ በኃይለኛ ተኩስ በሚሰጠን መልስ ችግር ፈጠረብን። ሆኖም የእርሱን ተኩስ ውጋገን እነጻጸርን በመትረየሳችን የእሩምታ ተኩስ ስለተኮስንበት ድምፁ በመጥፋቱ መሞቱን አረጋገጥን። መሬት ለመሬት እየተሳብን ወደ መስኮቱ ከተጠጋን በኋላ ትክክለኛውን ለማወቅ ካልሞተ መልስ ይሰጠናል በማለት ብንተኩስ መልስ ጠፋ። በመስኮት እየዘለልን ገብተን ብንመለከት አንድ ሴትና አንድ ወንድ ተዘርረው ከወለሉ ላይ ወድቀዋል።

የሟቹን ኪሶችና ቤቱን ፈትሸን በተገኘው መረጃ የፋሺስቶች የአየር ኃይል ባልደረባ የነበረ ካፒቴን ካሎ የተባለ ሰው ነው። ለጊዜው በፍቃድ ላይ መሆኑን ብንረዳም ወደ እሥር ሠፈሩ ምን ምክንያት እንዳመጣው ለማወቅ አልቻልንም። ሟቹ ካፒቴን የሰጠንን





ማስጠንቀቂያ ተቀብለን በእሥር ሠፈሩ በሚገኙት ቤቶች ላይ ቤንዚን ካርከፈከፍን በኋላ እሳት ለቀቀንበትና ወደመጣንበት ምሽጋችን ለመመለስ ጉዞአችንን ቀጠልን።

ካልተጠነቀቁት እሥረኞች መካከል ብዙዎቹ በካፒቴኑ የመትረየስ ጥይት እዚያው ቀርተዋል። እኔ በተለይ የማስታውሳቸው በመልክ ይመሳሰሉኝ የነበሩትን ሶማሌዎች ሲሆን ይልቁንም የግምጃ ቤቱን ጠቁሞ ያሳየንን ሞሐመድ ራጌ የተባለው ሶማሌያዊና የሶማሌ ተወላጅ የሆኑ ሴቶች እሥረኞችን ነበር። ከተረፉት እሥረኞች መካከል እንዳንዶች ብቻ ተነጥለው ሲቀሩ ሌሎች የአርበኞቹ አባሎች ነበሩ። የቀሩትም አቅም በማጣት በሀገሩ ብርድና በሽታ ካልሆነ የእሥር ቤቱን መከራ ደስታ በማድረግ አይደለም።

ከምሽጋችን ክሳን ሎሬንሶ ተራራ ላይ ለመድረስ እየተጣደፍን ሰባት ኪሎ ሜትር ያህል እንደተጓዝን አንድ የገጠር ባለሀጋ ቤት ስላጋጠመን ጥቂቶቻችን በሩን መትተን አስከፍትን። ባለቤቱ የሌሊት ልብሱን እንደለበሰ ሲወጣ የተራብን መንገደኞች መሆናችንን ገልጸንለት በሚቻለው ሁሉ ዕርዳታውን እንዲያደርግልን ጠየቅነው።

ባለሀጋው ሰው ከቁመቱ አጠር ያለና ትከሻው ሰፋ ብሎ ደንዳና ሰውነት ያለው ነበር በአንድ እጁ የተከናነበውን ፎጣ ጨብጦ በአንድ እጁ ደግሞ ሆዱን አቅፎ የብርዱ ኃይል ያስመረረው የሚመስለው



t.me/OLDBOOKSPDF

ሽማግሌ ዐይኖቹን እያጉረጠረጠ አተኩሮ ከተመለከተን ኋላ «ግቡ...ግቡ» አለንና እንድንከተለው ምልክት እያሳየን ወደ ውስጥ ገባ። እኛም ተከተልነው። እኛን ከሳሎን ውስጥ ጥሎን ወጥቶ አንዲት አሮጊት ሴት አስከትሎ ተመልሶ መጣና ከወጥ ቤት ውስጥ ዳቦ እየቆራረሱ አምጥተው አከፋፈሉን። የወይን ጠጅንም በብርጭቆ እየቀዱ ሰጡንና ጥማችንን ከአረካን በኋላ ከወጥ ቤቱ ውስጥ ገብተን እጆቻችንን አሙቀን ከብርድ አላቀቅናቸው ሽማግሌውን ሰውና ሴቲቱን አመስግነን መንገዳችንን ቀጠልን።

ጥዋት ሊነጋጋ ሲል በ12 ሰዓት ከሳን ሎሬንሶ ተራራ ጫፍ ደረስን። አልፈውን የሄዱት ጓደኞቻችን ግን ከእኛ ቀደም ብለው በመግባት እረፍት አድርገዋል። ከአርበኞቹ ጋር ከመቀላቀላችን በፊት ቆም ብለን ወደኋላችን ብንመለከት አንድ የሻለቃ የፋሺስት ጦር ከተራራ ተነስቶ ከለላ በማድረግ ወደ እኛ ሲገሰግስ አየን።

ወደ ምሽጋችን ገብተን ይህንኑ ስላስታወቅን ቀላል መትረየሶችን የያዙ 15 ሰዎች ቀደም ብለው ከተራራው ቁልቁል በመውረድ ምቹ ሥፍራ ይዘው ደጀን እንዲሆኑ ተወሰነ። የቀረው አርበኛ ግን በሙሉ የተማረኩት መሣሪያዎች ታድለውት ለእርዳታ ፈጥኖ እንዲደርስ ትእዛዝ ተሰጥቶ ሁሉም በክፍል በክፍሉ ወደ ፊት አመራ።





ለደጀን ጠባቂነት የተላኩት ወታደሮችና የፋሺስት ጦር ተኩስ መለዋወጥ እንደጀመሩ የኋለኛው እርዳታው ከሁለቱም ወገን የተኩስ ኃይል ተጋጋለ ፋሺስቶች ለጊዜው የመደናገጥ ስሜት እንዳደረባቸው ሊያስገነዝበን የቻለው ተኩስ ከእኛ በኩል እየተፋፋመ ሲሄድ የእነርሱ በኩል መቀዝቀዝ ነበር። ምናልባት የማረክናቸው መትረየሶች ብዛት ኃይላችንን እንደገመቱት ሳይሆን አስቀርቶ ይሆናል። የያዝነው ሥፍራ ምቹትም ሳይረዳን አልቀረም።

* * *



ሻምበል አብዲሳ አጋ በጦር መስመር ከሠራዊቱ ጋር ግንኙነት ሲያደርግ



t.me/OLDBOOKSPDF

አርበኞቹ ምን ጊዜም ለጦ ት የተዘጋጁ እንደመሆናቸው መጠን ልበ ደፋሮች ነበሩ። ከዚህ ቆራጥነት ጋር ማለፊያ የጦር መሣሪያ ስለያዙ ጠላትን ተጠግተው ለማጥቃት እየተጠጉት ሲሄዱ የጠላት ጦር የነበረውን ኃይል በሙሉ ወደ ኋላ እንዲመለስ ትእዛዝ ሰጠ። ፊቱን አዙሮ ሲሮጥ አርበኞቹ እየተከታተሉ ቁልቁል የተቻላቸውን ያህል ጥቃት አደረሱበት። በዚህ ዓይነት ከተሰናዳ ትጥቅ ጋር የመጣብንን ጠላት ለማባረር እግዚአብሔር ድጋፍ ሰጥቶን ውጊያው ያደረሰውን ጉዳት ለማወቅ ቁጥጥር ሲደረግ የመጣብን ጠላት ብዙ ሳይዋጋ ገና ከአፍላው ስለሸሸ ከእኛ በኩል አንድም የሞተ ወይም የመቁሰል አደጋ የደረሰበት አልተገኘም። ሆኖም አርበኞቹ ከአፋፍ ላይ ሆነው ቁልቁል የሚሸሸውን የፋሺስት ኃይል ለመጉዳት አመችቷቸው ስለነበር የ፲፫ ፋሺስቶችን ሬሳ ለመቁጠር ችለናል። ከዚህ በኋላ ወደ ሠፈራችን መልስ ሆነና የአርበኞቹ ጦር መሪዎች ባደረጉት ምክር እረፍት ከማድረግ ይልቅ ጠላት •እንደገና በሌላ መንገድ ተመልሶ እንዳያጠቃን የተሻለ ዋሻ መርጦ ሠፈር ማድረግ ተገቢ መሆኑ ተገልጾ ስምምነት ተደረገበት።

ስለዚህ በሚቀጥለው ቀን ያለው የወታደር ብዛት ታውቆና ሁሉም በየክፍሉ ተደልድሎ አሲቃና ሥራውን ካወቀ በኋላ ለውጊያ የተሻለ ምቹነት ያለውን ሥፍራ ቀደም ብለው ከእሥር ቤት በማምለጥ የወጡት አርበኞች ያውቁት ስለነበር ኡ...ያኖ ከተባለው





ተራራማ ፃ ሶሌ ስራልዳ በሚል ስም ከሚጠራው ምሽግ ሠፈር አደረግን።

ከተራራው ግርጌ የምትገኘው የኡያኖ መንደር ደማቅና ብዙ ሕዝብ የሚኖርባት ነበረች። በከተማዋ ውስጥም የፋሺስት ኃይል ሳይሆን የነበሩት ጥቂት ፖሊሶች ብቻ ነበሩ። ይህ በሰላዮቻችን መረጃ ተገልጾ እንደታወቀው አንዳንድ አርበኞች በሲቪል ልብስ እየሆኑ ወደመንደሯ እንዲወርዱና ሕዝቡን እንዲሰበኩ ሆኑ የአርበኞቹ ስምና የፋሺስት ኃይል እየተዳከመ መሄድ በይፋ ታወቀ። ከዚህም የተነሣ ምግብና ጠብመንጃ የምንጠቀመው የጠላትን ነበር።

* * *



t.me/OLDBOOKSPDF



አብዲሣ በኢጣሊያ በረሃ በአርበኝነት ጆብዱ የሠራው በዚህ በረዶ ውስጥ ነበር።





ምሽጋችንን እያደረጀን የጦር ስልቶቻችንን እያጠናን ጥሩ መሣሪያዎችንም ሲገኝ በገንዘብ በመግዛት እያከማቸን ሳለን ፋሺስቶች ካለንበት ምሽግ ድረሽ መጥተው ሊገጥሙን ማሰባቸውን ሰማን ስለዚህም በክፍል በክፍላችን ደንበኛ ምሽግ ይዘን ስንጠባበቅ እንደተወራው በሠራዊቱ ብዛትና በመሳሪው ኃይል የተማመነው የፋሺስት ኃይል ከሩቅ ሲታይ የሚያስጋ መልክ ነበረው። በጥድፊያ እየተጓዘ እኛ ከመሸግንቢት ቀበሌ ሲደርስ ሲቃረብ ልክ በሯ ሰዓት ያልታሰበ ተኩስ ከፍተን ሽብር ፈጠርንበት ከጠላት በኩልም የተኩስ አጸፋ መስጠቱ ተጀምሮ ከሁለቱም ወገን በሚሰማው የተኩስ መለዋወጥ አየራው ሲጨስ የአርበኞቹ ጥይት ተገን ለመያዝ የሚጣደፈውን የጠላት ወታደር ይለቅመው ጀመር። ከጠላታችን በኩል የቀጠለውን የተኩስ ድምፅ ስሰማ በዚን ዕለት የሁላችንም የዕልቂት ፍጻት ነው ብዬ ግምት ሰጥቼው ነበር። ብቻ ምን ያደርጋል አምላክ ያለው ሳይቀር ሰው በከንቱ ይጨነቃል እንደሚባለው ሁሉ ፍጻሜው እንደአጀማመሩ ሊያምርለት አልቻለም። የእኛ ዋናው ተዋጊያችንና ተከላያችን ያዘጋጀነው ምሽግ ነበር። ጠላት ከኋላ ለመዞር ሲሞክር ተጠባባቂ ደጀን አስቀርተን በሩን ዘግተንበት ስለነበር የአርበኞቻችን መትረየሶች እሩምታ በጆሮው ቢያፏጭበት እንደተለመደው ቁልቁል ወደመጣበት ተመለሰ። ግንባር ቀደም ሆኖ የመጣውም የጥይትና የዕጅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቦምብ ናዳ ስለፈላበት እስከ ፲ ሰዓት ድረስ ታግሎ እርሱም ፊቱን አዞረና ሽሽቱን ቀጠለ፡፡

በዚህ ቀን ከእኛ በኩል ሰባት ሰው ቆስሎ ፲፫ ሰዎች ሲሞቱብን ከጠላት ወገን የ፶፪ ወታደሮች ሬሳ ቆጥረናል፡፡ ቁስለኞቹን ግን በቃሬዛ ይዘዋቸው ሽሹ፤ ብዛታቸውን ሳንደርስበት ቀረን፡፡ ከዚህ ከጦርነት ምሽጋችን ጠላት እንደገና መመለሱን የሚጠባባቅ አንዳንድ ተጠባባቂዎች አስቀርተን ከዋናው ሠፈራችን መልስ ተደረገና የሞቱትን አርበኞች ስንቀብር ጨለማ ሆነ፡፡ ቁስለኞም ከዋሻው ውስጥ አርፈው ለጊዜው በተገኘው መድኀኒት ዶክተር ያላየው ሕክም ተደረገላቸው፡፡

* * *

ከዚህ ጊዜ አንስቶ የቀጠሉት ፲ ቀናት የኀዘን የትካዜና የብስጭት ነበሩ፡፡ ከእሥር ቤት ውስጥ አብረውት ሲንገላታ የኖረ እስረኛ በጀግንነት ከእሥራቱ አምልጦ ከጠላቱ ጋር በቆራጥነት ሲዋጋ በየትም በረሃ ወድቆ መቅረቱ ሲታሰብ ወይም በጥይት ቆስሎ የስቃይ ጩኸቱ ሲሰማ እርግጥ በሕይወት ለተገኙት አርበኞች አሳዛኝ ሳይሆንባቸው አልቀረም፡፡ የነዚያን ሁኔታ ከራስ የወደፊት ዕድል ጋር ሲያመዛዝነው ደግሞ ስሜቱ ወደ ትካዜ ይለወጥበታል፡፡ ከኀዘንና ከትካዜ በኋላ የሚፈጠር ሦስተኛ ስሜት ቢኖር ብስጭት ነው፡፡ ሰላምና





ነጻነት እንደ ውሃ የጠማው ቤተሰብና ሀገሩ የናፈቀው የጦርነትና የሰው ደም ማየት ያንገሸገሸው ወታደር ቢተክዝና ቢበሳጭ የወታደርነት ግዴታውን ረስቷል ሊያሰኘው እንዴት ይችላል? ማር እንኳን ሲበዛ ይመርራል የተባለው እኮ ከማር የበለጠ ጣፋጭ ነገር አለመኖሩ እየታወቀ ነው መራሩ ጦርነት ደግሞ ሲበዛ መጐምዘዙ አይቀርም ጕምዛዛ ጣዕም እንደሚያንገሸግሽ ሁሉ ጦርነትም ሲበዛ ለተዋጊው ወታደር የሚሰጠው ስሜት እንዲሁ ነው፡፡

በዚህ ዐይነት አሥር ቀናት በዚያ ምሽጋችን አሳልፈንና በአሥራ አንደኛው ቀን በገንዘብ ተገዝቶልን በስለላ ተግባር ሲያገለግለን የነበረ ቲቶ ቢአንኮ የተባለ የሀገሩ ተወላጅ ትኩስ ወሬ ይዞልን ደረሰ፡፡ « በፋሩንታሌ ሜዳ ላይ» ሳለን በሩጫ አመጣጡ ምክንያት የሚያቃስተው ቲቶ ቢአንኮ «የጀርመን ወታደሮችን የያዘች አይሮፕላን አረፈች» በማለት ሲዘረዝር ከወታደሮቹ ጋር አንድ ሻለቃ እንደሚገኝ ገለጸልን እርግጥ ጥቂት ቀደም ብሎ አንዲት አይሮፕላን ምሽጋችንን እንደዞረች ስታንዣብብ ቆይታ አልፋ ስትሄድ ተመልክተን ነበር፡፡ መረጃውን ካገኘን በኋላ ሁኔታውን ለማጣራት እኔና ጁሊዮ ኤታቼክ ከ ፳፫ ወታደሮች ጋር ወደ ፋሩንታሌ ሜዳ አመራን ፡፡ ከተባለው ቦታ ስንደርስም ጀርመኖቹ ካርታ ዘርግተው የቦታውን አቀማመጥ ሲያጠኑ ተመለከትን ወዲያው ከመካከላቸው አንዱ አይቶን ኖሮ ምልክት ሲሰጣቸው ተኩስ ከፈቱብን፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ፕሮቶኮል ቁጥር 98092.

[illegible] / ሐምሌ [illegible] 1946 ዓ.ም. /

የአርበኝነት የምስክር ወረቀት ፡፡

[illegible] መንግሥታት ሹም ሆነን የሻለቃ አብዲሳ አጋ [illegible] ኢትዮጵያዊ [illegible] እንፈልጋለን፡፡

የሻለቃ አብዲሳ አጋ [illegible] መንግሥታት ወታደሮች ጋ ሆነው ስለዓለም ነጻነትና [illegible] በጀግና አርበኝነት ተግባር ለተግባር በመሆን [illegible] አገልግሎታቸውን አስገኝተዋል፡፡ [illegible] በ1940 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1943 ዓ.ም. [illegible] ነበር፡፡

በዚህም ላይ [illegible] በአርበኝነት ስላስገኙት [illegible] እናመሰግናቸዋለን፡፡ የአሁኑን የምስክር ወረቀት [illegible] ሰዎች ሁሉ ስለዓለም ነጻነት ክብር [illegible] ፡፡

ፊርማ፡
1/ [illegible] ጄኔራል [illegible]
[illegible] መንግሥታት [illegible] ፡፡

2/ [illegible] ፡፡
3/ [illegible] ፊርማ ፡፡
ሻለቃ ፡፡

ግልባጭ፡ [illegible] መንግሥታት ፡፡



ተኩስ መለዋወጥ እንደ ጀመርን የአይሮፕላኑ ነጂ አልወረደም ነበርና አይሮፕላኗን አስነስቶ አመለጠ ። ከእኛ ወገን መጋል አባ ካርሎ የተባለው ኢትዮጵያዊ በጥይት ተመትቶ ሞተ ። ከጀርመኖች በኩልም አንድ የመቶ አለቃ መኰንንና ሦስት ወታደሮች ተገድለው የተረፉት እንደማያመልጡን ልቦናቸው ስለተገነዘበው እጃቸውን ሰጡን ። ምርኮኞቹንና የኢትዮጵያዊውን ወታደር ሬሳ ይዘን ኡያና የጦር ሠፈራችን ተመለስን።

የማረክናቸው የናዚ ወታደሮች በማረፊያ ቤት አድረው በማግሥቱ ጥዋት በተደረገው የፍርድ ስብሰባ ሁሉም የሞት ቅጣት እንዲቀበሉ ሲወሰንባቸው ሻለቃው ጀርመናዊ በካፒቴን ጁሊዮ ኢታሎ አስተርጓሚነት ፈቃድ ጠይቀው ቀጥሎ የተመለከተውን ተናገሩ፡፡‹‹ እናንተ የዩጎዝላቪያና የሌሎች አገሮችም አዳምጡኝና እውነተኛውን ላስረዳችሁ›› የፋሺስት ኃይል የእናንተን ቆራጥነት ስለተገነዘበውና ኃይላችሁንም ከፍ አድርጎ ስለሚገምተው ሥጋት አድሮበታል ይህንንም እኛ ከሰማነው ቆይቷል፡፡ ይልቁንም አቢሲኒያዊው (ኢትዮጵያዊ) ጀግና የአንቶንዮ (አብዲሳ) ታሪክ ተጋንኖ ይወራለታል፡፡ የሃበሻዎች ከመካከላችሁ መገኘት በፋሺስት ወታደሮች መካከል ፍርሃትን ፈጥሯል፡፡ ስለዚህ አሁን የምጠይቃችሁ ይህንኑ ቁርጠኛነታችሁን ከመሞቴ በፊት ለጦር አዛዤ እንዳስታውቅ እንድትፈቅዱልኝ ብቻ ነው›› ሲሉ ልመና አቀረቡ፡፡ ለፍርድ

የተመረጡት የአርበኞች ሹማምንትም ነገሩን አመዛዝነው ለማግለጽ የሚፈልጉት ሐሳብ በካፒቴን ጁሊዮ ኢታቹክ አስተርጓሚነት በሬዲዮ እንዲተላለፍ ተፈቀደላቸው።

ይህ ተፈጽሞ እንዳበቃ ሞት ትእዛዙ ይፈጸም ዘንድ ተማረኪዎቹ ወደ አስፈላጊው ሥፍራ ተወሰዱ። በዚህም ደንቡ በሚያዝዘው መሠረት እጃቸው በገመድ ሊታሠር ዐይኖቻቸው ደግሞ በጥቁር ጨርቅ ሊሸፈን ይገባ ነበር። ሆኖም እዚህ ላይ ሻለቃው ሌላ የትሕትና ጥያቄ አቀረቡ። ‹‹ እኔና እናንተን ከዚህ ቦታ ያገናኘን ግዳጃችን ነው። (የሐበሾችን) ጀግንነት በትምህርት ቤት በነበርኩ ጊዜ በመጽሐፍ አንብቤዋለሁ። ጀርመኖችም እንዲሁ ጀግንነታቸው የተመሰከረ ነው። ስለዚህ አሁን የምጠይቀው ሳንታሠር የሞት ፍርድ እንዲፈጸምብንና በጀግንነት መልክ እንድንሞት ነው።›› ብለው ለእኔ መታሰቢያ ይሁንህ ሲሉ የወገባቸውን ሽጉጥ የሱሪያቸውን ቀበቶ የእጃቸውን ሰዓትና የጣታቸውን ቀለበት አውልቀው ሰጡኝ መታሰቢያውም እስካሁን በእጄ ይገኛል። ምርኮኞቹ ከዚህ በኋላ ‹‹ሃይ ሂትለር›› ማለት (ሂትለር ይኑር) የሚለውን ቃል እጃቸውን እየዘረጉ ሲያሰሙ ፍርዱ ተፈጸመባቸው።

* * *







ሻምበል አብዲሣ አጋ በሩቅ የጠላትን ሰፈር ሲመለከቱ።



t.me/OLDBOOKSPDF



አብዲሣ በኢጣሊያ በረሃ በአርበኝነት ጀብዱ የሠራው በዚህ በረዶ ውስጥ ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ ገና ለተወሰኑ ቀናት እረፍ ብለን በሰላም ከርመን ነበር። ግን ፋሺስቶች እኛን ለማጥፋት የነበራቸው ምኞት የጠነከረ እንደመሆኑ በሌላ ጊዜ አድፍጠው ሳንቤሮ ከተባለው አደገኛ ተራራ ላይ ውጊያ ገጠሙን። ፍጻሜው ግን ካለፈው ጋር ሲተያይ ሌላ ለውጥ አልነበረውም። እንደተለመደው የፋሺስት ወታደሮች ገና የአርበኞቹ የተኩስ እሩምታ ሲከፈት ሽብር እየተሰማቸው ወደ ኋላ መፈርጠጥ ሆነ ። ገሚሱ ከአፍሪካ ገሚሱ ከእንግሊዝ ገሚሱ ከፈረንሳይ ገሚሱ ከዩጎዝላቪያ የመጡና እንዲሁም ደግሞ ሌሎች ብዙዎች ዜግነታቸውና ቀለማቸው የተለያዩ አርበኞች በየቋንቋቸው እየፎከሩ ተባራሪውን ጠላት በሳንጃ እየወጉ ወደ ገደል ሲጥሉት መመልከት መፈጠርን የሚያስጠላ ነበር።

ጠላታችንን እንዲህ እያስመረርን አስወጥተን የሞቱብንን በክብር ቀብርን ቁስለኞችን ከሠፈር አደረስን። ከዚህ በኋላ ግን እስካሁን የነበርንበትን የመከላከል ተግባር ትተን የማጥቃት ኃይል መውሰድ አስፈለገ። በዚህም መሠረት በማግሥቱ ማታ ጀግናው ካፒቴን ጁሊዮ ኢታቺክ በአቅራቢያችን ከምትገኝ አንዲት ቤተ ክርስቲያን የሰበሰቡትን የቀሳውስት ልብስ ለ፲ የተመረጡ አርበኞችና ለራሱም እንዲለብሱ አደረጉና እያንዳንዳቸው በካባቸው ውስጥ ቀላል መትረየስ የእጅ ቦምቦችን እንደያዙ ሳንሳ ባሪኖ ዴሌ ማርኬ ከተባለው ከተማ ውስጥ ገቡ። ከዚያም የከተማዋ የፀጥታ ጠባቂ ፖሊሶች ካሉበት ሠፈር





በመጠጋት አደጋ ጥለው ፶ኙ ወታደሮችን ፈጅተዋል፡፤ ከተማቸም ተሸብራ ስለ ነበር በተደናገጠው ሕዝብ መኖሪያ ቤት ውስጥ እየገቡ ምርኮ ይዘው መመለስ ቻሉ። የተማረኩትም መሣሪያዎች ቀላልና ከባድ 110፡4779 ጥይቶችን አንድ ፊያት ትሬንታኳትሮ ፬ ሴትና ወንድ የሬዲዮ ሠራተኞችና ፪ ሬዲዮ ናቸው።

* * *

በዚህ ዐይነት በ፫ ታላላቅ የአፈርና የድንጋይ መጫኛ ፊያት መኪናዎች ላይ ተጭኖ ሠፈር የደረሰውን እራግፈን የሚቀጥለውን የማጥቃት ተግባር በተከታዩ ሐሙስ ቀን ለመውሰድ ተወሰነ። በዚህ ቀን በከተማዋ ውስጥ የፋሩንታሌ ገበያ የሚውልበት ነበር።ስለዚህም በተባለው ዕለት ወደ ገበያው በሚያመራው በቪያኑራ መንገድ ላይ ባለው የኪጃና ወንዝ ድልድይ ላይ እኔና ካፒቴን ጁሊዮ ኢታቺክ ቁመን ከመንገደኛው ገበያተኛ ላይ በነፍስ ወከፍ ያገኘነውን የአሣማ ሥጋ እንቁላልና ጨው ስንቀርጥ ዋልንና ማታ ወደ ሠፈር ስንመለስ ጠላት ወሬ ሰምቶ እንዳይከታተለን በማለት ድልድዩን በፈንጂ ኃይል አፈራረስነው። እንዲሁም በሚቀጥለው ቅዳሜ ቀን ትሬያ በተባለችው ቀበሌ የገበያ ቀን ስለነበር አራት አርበኞቹን አስከትዬ ከጥዋቱ ሁለት ሰዓት ገበያው ሲደራ ገባን። ከመግባታችን በፊት አስቀድመን



t.me/OLDBOOKSPDF

የኤሌክትሪክና ስልክ መሥመሮች ቆራርጠናቸው ነበር። እንደደረስንም ከሕዝቡ ጋር የተደባለቁ ሁለት ካራቢኔሬዎች አግኝተን ስንገድላቸው ገበያተኛው ተደናገጠ። ይልቁንም የእኔን የጥቁር መልክ ያየ ሁሉ ወሬውን በፍርሃት ተቀባብሎ አራብቶት ነበር። በዚህም ምክንያት ለጊዜው የተገኙትን የጦር መሣሪያዎች እየገፈፍን ስንሄድ እንኳን ሊተኩሱብን መቃጣት ቀርቶ ያሰፍንበትን መንገድ ተከትሎ ለማየት ብቅ የሚል አልነበረም ።የተማረኩትም መሣሪያዎች 1761 ከባድና ቀላል መሣሪያ የእጅ ቦምብና እንዲሁም ጩቤዎች 3,836,231 ጥይቶች 4,003,213 ሊሬ ነው፡

* * *

ይህን እኛችን ካደረግን በኋላ ከከተማው በስተምዕራብ ወጣ ብለን የተማረኩትን አራቱንም የእጅ ቦምቦች ወደ ገደል ስንወረውረው በገበያው ላይ የነበረው የከተማና የባላገር ሕዝብ ገሚሱ ወደ ገጠር ገሚስ ወደ ከተማ መባረር ያዘ። ዘረፋና ሽብርም ተፈጠረ። ለከተማዋ ጥበቃ የታዘዙት ፖሊሶች ነፍሳቸውን ለማትረፍ ከሲቪሉ ቀድመው ሸሽት ቀጠሉ። ይህ ሲሆን እኛ በእግዚአብሔር እርዳታ አንድም ችግር ሳያጋጥመን ገድለንና ማርከን ለመመለስ ችለናል፤ የተማረኩትም 6 አቶማቲክ መሣሪያዎች 9 የእጅ ቦምቦች 658 ጥይቶች ናቸው።







ጄሌ ታኪች ዩጎዝላቪያን አርበኛ መሪ በዚህ ዐይነት ጠላትን ያጠቃ ነበር።

በየጊዜው ከጦር ሠፈራችን እየወረድን በአካባቢው የፈጸምነውን የወረራ ተግባር ሁሉ የፋሺስት ከፍተኛ ጦር አዛገሮች እየሰሙ መበሳጨታቸው ባይቀርም በሌላው በኩል የሚገሰግሰው የጦር ኀዶች ኃይል ያጣድፋቸው ነበርና ወደ እኛ ዘንድ ለመምጣት ጊዜ አላገኙም:: ሆኖም የአርበኞቹ ምሽግ ካለበት 102 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ የነበረው አንድ የጠላት ጦር ሲያዝ የነበረውና በጨካኝነቱ የታወቀው ኮሎኔል ቱሩንቤት ልዩ ስሙ ኤስ ኤስ የተባለ እግረኛ ጦር ተፈቅዶለት በማስከተል ለሦስት ሳምንት ያህል በተለይ የእኔን ዱካ በስላይ እያጠያየቀ ይከታተለኝ ጀመር::

የሚከታተለኝ ጦር ኃይለኛ መሆኑን ብገነዘበውም በየቀኑ ምሽግ ከማቀያየር በቀር የነበርንበት ተራራ ትቼ አልራቅሁም ነበር:: ለዚህም ምክንያት ከሆነን አንዱ ተራረው ለመደበቂያ ያለው ምቹት ነው:: በአንድ የገበያ ቀን ከሁለት የአርበኝነት ጓደኞቼ ጋር ከተራራው ወርደን ቢያኑራ ከተባለ መንገድ አቅራቢያ አድፍጠን እንጠባበቅ ጀመር:: ተላላፊ ሕዝብ ብዙ አይታይም ነበር:: ወታደሮችም ሳናይ ሁለት ሰዓት ያህል እንደቆየን የመኪና ድምፅ ሰማን:: አንገቴን አቅንቼ ብመለከት ወደ ገበያው የምታልፍ አንዲት ወታደር አብሪያሌያ ባለሽራ መኪና ናት:: ተጠንቅቀን ጠብቀናት ካጠገባችን ስትደርስ ያልታሰበ ተኩስ ከፍተን አቆምናት ጥቂት ተጠባብቀን መልስ ስናጣ ወደ መኪናዋ ተጠግተን ሁኔታውን ብናጣራ ነጂውና ካጠገቡ ተቀምጦ የነበረው





ኮሎኔል ትሩንቤንተ እንዲሁም ከኋላው ተቀምጠው የነበሩት ሁለት ወታደሮች መሞታቸውን አረጋገጥን::

የሟቾቹን ፋሺስቶች ሬሳዎች አውርደን ከጣልን በኋላ እኔና ጓደኞቼ በአብሪሊያዋ መኪና ተሳፍረን ወደመጣንበት ተራራማ ስፍራ ሸሸት ቀጠልን:: በዚህም ጊዜ ብዙ መሣሪያዎች ማግኘት ችለናል::

ከኮሎኔል ቱሩንቤቲ የተማረኩት ፫ ቀላል አቶማቲክ መሣሪያዎች 328 ጥይቶች ፫ ቦምብ ልዩ ልዩ ደኩሜንት ናቸው::

* * *

የዚህ ኮሎኔል መሞት ሲሰማ ሌላ የጠላት ኃይል ይበልጥ በደረጃ ጦር ሲወጋን ወደ እኛ ምሽግ በመምጣት ላይ መሆኑን ሰማን ዜናው ደርሶን እኛም በንቃት ስንጠባበቅ የተባለው ጦር ከሳንቤችኖ ተራራ ደርሶ የተጀመረው ውጊያ በልዩ ልዩ አቅጣጫ ከብቦን እያረፈ በመቀጠል አራት ቀን ቆየ:: በዚህ ጊዜ የመከላከል ተግባራችንን ሳናቋርጥ በምሽጋችን እየተረዳን ስናጠቃ ለጠላት ያልታሰበ የጀርመን ኃይል ተተክቶ ድል ሊመቱን ጥቂት ሲቀራቸው የእንግሊዝና የአሜሪካ ወታደሮች ደረሱልን:: ፋክራ አይሁንብኝና እውነቱን ለመናገር ያህል እንደተለመደው በካፕቴን ጁሊዮ ኢታቺክና በእኔ የሚመሩት አርበኞች የመጀመሪያውን ድል ለማግኘት በቁ::



t.me/OLDBOOKSPDF

በእኛ በኩል አስቀድሞ በጥናት በተደረገው ውሳኔ መሠረት የቦታው አቀማመጥ ለሚሸሹት እንጂ ለሚያጠቁት ስለማይመች ብዙውን ጊዜ የሠራንበት ታክቲክ እየሸሸን ማጥቃት ነበር።

ይህን እርምጃ እየተከታተልን የሞተው ሞተ። ጥቂቱ የተረፈው ጠላት ሲሸሽ ጠቅላላው ድል ለአርበኞች ሆነ።

* * *

ከሀገሬ ከኢትዮጵያ ወጥቼ በማላውቃቸው አርበኞችና ያችን ባዕድ የሆነችውን ምሽጋችንን ተገን በማድረግ ይህን ሁሉ ድልና ገዞና ለማትረፍ መብቃቱን እስከ ዛሬ ሳስበው ይደንቀኛል። ተራራዋ ለብዙዎቹ አርበኞች ባዕድ ብትሆንም ከመካከላችን የሚሞቱትን ሬሳዎች ተቀብላ ለማስተናገድ እምቢተኛ አልሆነችም፤ ዛሬም ቢሆን የሟቾቹ አጽምና ማርከን የቀበርናቸው መሣሪያዎች ቅሪት ከዚያች ተራራ ሥር እንደማይጠፉ እተማመናለሁ።

ሰው የራሱን ሕይወት ለማትረፍ ‹‹፣ አልሞት ባይ ተጋዳይ›› በሚለው አባባል መጠቀም ግዴታ ይሆንበታል። እኔን የመሰለው ቀን የጐደለበት ሰው በሰላም ከሚኖርበት ትውልድ ሀገሩ እንደ አውሬ ታሥሮ ወደ ጠላቱ አገር ከተወሰደ በኋላ እንደገና የግዳይ ሙከራ ቢቃጣበት ጠላቶቹን ደምስሶ ሕይወቱን ማዳን አለበት። አድራጎቱን





ስለሚፈጽምበት ሁኔታ ወይም የገጠሙት ጠላቶቹ እነማን እንደሆኑ ምርጫ አያደርግም። በሳንቢርኖ ተራራ ላይ እንዲሁ በአርበኝነት ስንኖር ከዕለታት አንድ ቀን የምግብ አውሬ ለመፈለግ ወደ አደን ሄጄ ነበር። በዚሁ ጊዜ የአንድ ቋጥኝ ጥጋት ይገፔ ለጥቂት ደቂቃዎች እረፍት እንደተቀመጥኩ የእንቅልፍ ሽልብታ ይዞኝ ቆይቼ ብነቃ አንድ የቀበሮ ውሻ ካቅራቢያዬ ተጋድሞ ተመለከትኩ፤ፈጥኜ ብድግ ብዬ ልሄድ ስል የቁጣ ድምፅ አሰማኝ ለዚህ አውሬ የሰጠሁት መልስ በመትረየስ ቃታ ስለነበር ሲገድለኝ ከተነሣው አውሬ አፍ መዳን ቻልኩ።

* * *

በሳንቢችኖ ተራራ ላይ ከተደረገው ከባድ ውጊያ በኋላ ለአንድ ሳምንት ያህል በእረፍት ላይ ቆይተን ከተራራው አጋማሽ ላይ ይገኝ በነበረው ሜዳ ላይ አንድ ቀን ጠቅላላ ስብሰባ ተደረገ። አርበኞቹ ዙሪያውን ተሰልፈው እንደቆሙ ለዕልቅና የተመረጡት ሹማምንት ሲመካከሩና ሐሳብ ለሐሳብ ሲለዋወጡ ቆይተው አዲስ ድልድል ተደርጎ ወታደሮቹ በስንደቅ ዓላማ እየተለዩ በአራት እንዲመደቡ ተወሰነ።



t.me/OLDBOOKSPDF

በአንደኛው ክፍል የተመደቡት ፪፻፶ አሜሪካውያን ኔ:ርበኞች ሲሆኑ የሚመሩትም በአንድ ሙሉ የሙቶ አለቃ ነበር። ይህ ሰው ከአሜሪካኖች ጋር ቢደለደልም ዜግነቱን እየለዋወጠ ሲናገር ይሰማ ነበር። ቁመቱ በግምት 185 ይደርሳል። አቋሙ ቀጥ ያለ ቀጭን ሆኖ ዐይኑ ነጫጭ ፀጉሩ ቀይ ነው። የጦር ዘዴ አሳምሮ ያውቃል፤ ብዙውን ጊዜ ከአርበኞቹ ለየት ያለ አለባበስ እንዲኖረው ይፈቅድ ነበር። በመጨረሻ ጊዜ በኃይለኛ ጦርነት ላይ ጠፍቷል። ተገድሏል የሚሉ አሉ። በእርግጥ ያየ ሰው ግን ከመካከላችን አልተገኘም።

በ፪ ኛው ክፍል ደግሞ የእንግሊዝን ሰንደቅ ዓላማ የያዙ ፻፶ ወታደሮች ሲገኙ 1.60 ቁመት ያላቸው ሜጀር ፋይል በኋላ በጦር ሜዳ ሌ/ኮሎኔል ማዕርግ አግኝተው የወርቅ ሜዳይ የተሸለሙት ጀግና ነበሩ። እኒህ ሰው አስቀድሞ በአፍሪካ ምድር በሊቢያ ውስጥ በ፲ኛው እግረኛ ክፍለ ጦር በአየር ወለድ የፓራሹት ክፍል አዛዥ ነበሩ። ከዚያም ወደ ቺቺሊያ ለጦር ስለላ ተልከው አይሮፕላናቸው በድንገት በመትረየስ ስለተመታ በፓራሹት ወርደው በፋሺስት ወታደሮች ተማረኩ። ከእሥር ቤት ካመለጡም በኋላ ከአርበኞች ጋር ተቀላቅለው በአዛዥነት ሲዋጉና ሲያዋጉ ቆይተዋል። ብዙውን ጊዜ በአሜሪካና ከእንግሊዝ የጦር ጓዶች በአይሮፕላን የሚላኩልንን ምግቦችና መድኃኒቶች በእርሳቸው ትእዛዝ በሚተላለፈው የሬዲዮ መልእክት አማካይነት ነበር።







የሻምበል አብዲሣ አጋ በሩቅ የጠላትን ስፈር በመነጽር እየተመለከተ በሁለት መትረየስ ግራና ቀኝ ሲያስመታ



t.me/OLDBOOKSPDF

፫ኛው ክፍል ከ፱፻ ያላነሰ የዩጎዝላቪያና የኢጣሊያ አርበኞችን የሚመሩት ካፕቴን ጁሴ ኤታቺክ ነበሩ። ካፕቴኑ በአርበኝነት ጊዜያችን እንዳጫወቱኝ ሁሉ ትውልዳቸው በዩጎዝላቪያና ሉቪያና ባቪቶሪኦ መንገድ ቁጥር ፶፮ ነው። ሃይማኖታቸው ኦርቶዶክሳዊ ሲሆን በዚያን ሰዓት ዕድሜያቸው ፵ ዓመት ነበር። ካፕቴኑ ቆራጥ ጀግና ሞትን እንደ ሠርግ የሚቆጥሩ በተከታዮቻቸው ዘንድ የተወደዱ ለጠላቶቻቸው ደግሞ የጭካኔያቸው ሙያ የሚያስፈራ ነበሩ። የዩጎዝላቪያውያኑ አርበኞች ጀግንነትና ቆራጥነት ለማረጋገጥ ካበቁኝ ምክንያቶች አንዱ ከመካከላቸው የነበሩት ከ፪፻ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ሲሆኑ እስከመጨረሻው ድረስ ሳይታወቁ እንደ ወንድ ሲጋደሉ መቆየታቸው ሆኗል።

በ፬ኛው ክፍል የተመደቡት ፫፻፹ አርበኞች ደግሞ ዜግነታቸው የተለያየ ሲሆን የሚመሩት በእኔ ሜጀር አንቶኒዮ አብዲሳ ነበር ። ስለራሴ ሁኔታ አስቀድሜ እኔነቴን ያስተዋወቅሁ ይመስለኛል ሆኖም ምንም እንኳ ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ ከጦርነት መካከል ለመግባት የተፈጥሮ ወኔዬ የሚገፋፋኝ መሆኔን ብገልጽም ከዚህ ድልድል ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይገፔ ወታደሮቼን እንድመራ ስደረግ የሀገሬና የንጉሠ ነገሥቴ ፍቅር ግለቱ እየተፋፋመ ይሰማኝ እንደነበር ማረጋገጥ እወዳለሁ። በዚያን ጊዜ የነበረኝ ሰንደቅ ዓላማ ባለአንበሳ ስትሆን ዛሬም በድኃ ጉጀዬ ትገኛለች ። ልብሴን ከማጥን





ለማውጣት በከፈትኩት ቁና ር የሞትሁላትን ዓላማዬን በተስፋ ጌን እንዳታለልሁ ነኝ።

በአርበኝነት የተጠቀምሁበትም የአርበኞቹ ልዩ ምልክት አሁን በእጄ ይገኛል። ጦሩ በዚህ ዐይነት ተከፋፍሎ ሳለ የእንግሊዝና የአሜሪካ አይሮፕላኖች በሜጀር ፋይል አማካይነት በሚተላለፍላቸው መልእክት የምንጠይቀውን ሁሉ በፓራሹት ያወርዱልን ነበር። ይህንንም የፋሺስትና የጀርመን ወታደሮች ሲመለከቱ አርበኞቹን ፈጽመው ለመደምሰስ ሙሉ ሐሳብ አደረጉ ዋናው ምክንያታቸውም የእነርሱ ኃይል እየደከመ ሲሄድ ከእኛ ጋር የሚቀላቀሉት ስደተኞች መበርከትና የአቅማችን መጠንከር ነበር።



[illegible]



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመከላከል የሚያመቸንን ቦታ መርጠን ፀእኔ በኩል ያሉትና በካፕቴን ጁሴኤታቺክ የሚመሩት አርበኞች ንቅናቄ ስናደርግ እንግሊዞችና አሜሪካኖቹ ወደ ኋላ ቀሩብን ፡፡ ሞንታራለሴ ከተባለው ስፍራ ስንደርስ ሳናስበው በጀርመን ጦር ሠራዊት ተከበብን ፡፡ ሁለት ቀን ስንደበደብ ቆይተን ከብዙ ስቃይ በኋላ ሌሊት ለማምለጥ ቻልን፡፡ ይህ በሆነ በሁለተኛው ቀን ዋናው የጀርመን ጦር ድል ሆኖ የጦር ጓደኞቹ ሠራዊት ሮም ገብቶ ኑሮ ወደ ምሥራቅ አውሮፓ የሚሸሹትን ጀርመኖች የእኛ አርበኞች ጦር ከመንገድ እየተጠባበቁ መድረሻ ያሳጣው ጀመር ፡፡ ከዚህም በቀር መተላለፊያ መንገዶችንና ድልድዮችን በድናሚት እያፈራረስን ስለ ተጠባበቅነው እኛን ለማጥቃት በኅብረት ገፍቶ የሚመጣ ጦር ሊያገኘን አልተቻለውም፡፡

የኢጣሊያ ጦር መሪዎች አስቀድመው በመርበድበድ መሪዎቹም የጦር መሣሪያዎቻቸውን እየጣሉ መሄድ ጀመሩ፡፡ ይሁን እንጂ ከፍራታቸው ፍራታቸውን እንዳይገልጥባቸው ሜጀር (አንቶኒዮ) አብዲሳ ካፕቴን ጁሊዮኤታቺክ ሜጀር ማርዮንና ሌ/ኮሎኒል ፋይልን እነዚህን አራቱን የአርበኞች ጦር መሪዎች ይዞ ላመጣልኝ ወይም አንገታቸውን ቆርጦ ለሚያሳየኝ የወርቅ ኒሻንና ፩፻ ሺ ሊሬ እሸልመዋለሁ ብሎ መንግሥቱ በማስታወቂያ አውጥቶ ባወጀ ጊዜ ቀደምት ሽልማት የፈለገው ማርሻል ባሎምባሪኒ አስፈትዶ ወዳለንበት ቦታ ድረስ መጣ ፡፡ እኛን በመፈለግ ብዙ ከደከመ በኋላ በአምላክ





ፈቃድ ወደኛው ክፍል ሲያ..ራ በአርበኞቹ እጅ ተይዞ የመጣ..ን ምክንያት አንድ ባንድ ከዘረዘረ በኋላ በጥይት ተደበደበ፡፡ የማቹ ቤተሰቦች ትሬያ ከምትባል ደጋግሞ የፋሺስት ደም ከፈሰሰበት አነስተኛ ከተማ አሁንም ይገኛሉ፡፡

ከዚህ አስቀድሞ ግን ማርሻሉ የሚረገርም ነገር ተናገረ ፡፡ የሚገርም ስላችሁ የሚያስደንቅና የፋሺስት አርቆ አለማየት የሚያሳይ ነው ማለቱ ነው፡፡ ማርሻሉ ባሎምባሪኒ በዐይኑ ማየት በሚጠላው ጥቁር እጅ ተይዞ ሲደበደብ እጁን ወደ አንዲት ቤተ ክርሲቲያን በማንሣት ‹‹ ተመልከቱ ጥቁሮች በሀገሬ ላይ መጥተው ያስፍርዱ ይገድሉኛል›› ማለቱ ነው፡፡

ይህ በጣም የሚያስገርም አስተያየት ነው፡፡ ፋሽስቶች ስንት ባሕር አቋርጠው መጥተው በውዷ ሀገሬ በኢትዮጵያ ላይ ይህን ያህል ግፍ የሠሩ በእሥር ቤት ተወስኜ ጊዜ አጋጥሞኝ ከጠላቶቼ አንዱን ብገድል ምን የሚያሳጣ ነገር ነበር?፡ ፋሺስቶች የደጉን ወገኔን ደም ያለምክንያት ሲያፈሱ ምን ሐሳብ ኖሯቸዋል? ከሥልጣኔ ቆጥረውት ይሆን?፡፡

ማርሻሉ ተቀበረ አለ፡፡ ከዚያ በኋላ ከፋሺስት በኩል አንድ ካፕቴንና ሁለት ሰዎች እኔን ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር ለማስታረቅ ሳንሎሬንሶ ከተባለው ተራራ ጫፍ ደርሰው ሳለ ጓደኞቼ የዩጎዝላቪያ



t.me/OLDBOOKSPDF

አርበኞች አስቀድመው አገኟቸውና በቂ ምርመራ ካደረጉላቸው በኋላ ገድለው ከጉድጓድ መጣላቸውን የወሬ ጭምጭምታ ሰማሁ ። ወዲያው ሰባት አርበኞች አስከትዬ ዩጎዝላቪያኖቹ ካሉበት ደረስኩና በካንቴን ጁሴኤታቺክ አማካይነት የተገደሉትን ፋሺስቶች ሬሳ እንዳይ ከመሞታቸውም በፊት የሰጡትን ቃል እንድመለከት ጥያቄዬ ከተፈጸመልኝ በኋላ ወደ ቦታዬ ተመለስኩና በኔ የሚመራው ጦር በድንገት የሚመጣውን ጦር እንዲከላከል አሁን ያለንበትንም ቦታ ወደሌላ አዛውር እንዲዘጋጅ አደረግሁ። በማግሥቱ የተገደሉትን ሰዎች እስከሬን እንዲሰቀል አደረግሁ። ከነሱም ፲፰ ኦቶማቲክ ጠብመንጃ ሽጉጥና ቦንብ ፫፻፳፬ ጥይት እኛ እንድን ገደል የታዘዘበት በማርሻል ሩዶልፎ ባዶሊዮ የተፈረመ ሦስት ካርታ ማረክን እንዲሁም የተማረኩት ኢጣሊያኖች የሚሊታሪ ልብሳቸውን እንደለበሱ የሚገባቸውን ዋጋ አገኙ።

* * *

የምርኮ ዕድል ባጋጠመን በዚህ ቀበሌ የኢጣሊያ ጉረምሳዎች ሌላ ዘዴ ይፈለስፋ ጀመር ።ይኸውም ፊታቸውን ጥቁር ቀለም እየቀቡ ፤ መሣሪያ እየያዙ ጨለማ በመልበስ በገጠርና በከተማ « እኛ ሜጀር (አንቶኒዮ) አብዲሳ» ነኝ እያሉ ማታለላቸው ነበር። ይህ ብቻ ሳይሆን አንዱ ጉረምሳ ፊቱን ካትረሜ ሳይቀባ « እኔ ካፒቴን ጁሴኤታቺክ ነኝ» እያለ አገሩን ለመውረር የእኛን ስም ያጠፋ ነበር። እኔ ራሴ





ምግብ ፍለጋ ስሄድ ወይም ስልክ ስደውል ምነው ትናንት ማታ መጥታችሁ አልነበረም? ዛሬ መቼ አዘጋጀን ይሉኝ ጀመር ። እነዚህን አታላዮች መያዝ አለብኝ ብዬ ወሰንኩ፤ አንድ ቀን በስንት ድካም ፲፭ የሚሆኑ ጉረምሳዎች ፊታቸውን ካትራሜ ቀብተው ሌሎች ደግሞ ፳ የሚሆኑ አቶማቲክ መሣሪያ የያዙ በድምር ፴ ሰው ከአንድ ባለጠጋ ቤት ሄደው ቤት በማስከፈት ገንዘብ ልብስና ጥይት ሲቀበሉ በግል ሰላይ ደረስኩ። ወዲያው እንዲያዙ አደረግሁና 7240 ጥይት ሽጉጥ ተላል መትረየስ የእጅ ቦምብ ለነጭና ለጥቁር ሰው የሚሆን የፊት መሸፈኛ (ማስካራ) ማረክሁ። እንዲሁም 89749 የኢጣሊያ ኖት(ሊሬ) ሲገኝበት የተመነዘረው በጀንያ ስለሆነ አልተቆጠረም ከዚህም በስተቀር ፶፬ ጆንያ የምግብ ዕቃዎች የያዙ እነዚህን ዝርዝር ጉዳዮች የሚጭኑ ፵፭ በቅሎዎች ምርጥ ሆኑ የከርቻ ፈረሶች እንዲማረኩ አደረግሁ። በዘመኑ ለነበረ ሥራ ክንውን በሚገባ በተገኘው ገንዘብ እንደልባችን ተጠቀምንበት።

* * *



t.me/OLDBOOKSPDF

## የኪሻኖ ድልድይ።

ይህ ድልድይ ርቀት አለው። የተማረኩትን ንብረቶች ከተረከቡኩ በኋላ ተማራኪዎቹ ሰዎች እያንዳንዳቸው ቀርበው ቃላቸውን ሰጡ። የሠሩት የማታስል ተግባር ወንጀል ስለሆነ ሁሉም በጥይት እንዲገደሉ አደረግሁና ኪሻኖ ከተባለው ድልድይ ውስጥ እንዲጣሉ ተደረገ፤ ይህ ድልድይ ርቀት አለው አልኩ እንጂ ታሪካዊነቱ በርቀቱ ብቻ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ከፋሺስት ጋር ጦርነት ገጥመን ዕድል ከድታን ስንሸሽ ብዙ ጓደኞቻችን ከዚህ ገደል ውስጥ እየገቡ ከመሞታቸው በላይ የሚማረኩትንም አርበኞች የኢጣሊያ ፋሺስቶች ከነነፍሳቸው እጃቸውን እየያዙ ከዚህ ገደል ውስጥ ይጨምሯቸው ስለነበር ያንን በቀል ለመመለስ ያልነው ነው።

በየጊዜው ከኢጣሊያኖች ጋር ጦርነት ስናደርግ ኖርን። የናዚስትና የፋሺስት ጦር ኃይል በጦር ጓደኞቹ ድል ተነሥቶ ወደ ምሥራቅ አውሮፓ ሸሽቱን ቀጠለ። የጦር ጓደኞች ድል ነሥተው ሮም ከተማ በገባበት ወቅት የተባበሩት መንግሥታት የጦር ጓደኞች ዋና አዝማች ፊልድ ማርሻል ባውካንት አሌክሳንደር ለአርበኞች ቴሌግራም አስተላለፉ። እኛም የጠላት ጦር ሸሽቶ እንዳያመልጥ በሮማና በአንኮና በሚገኘው ጕዳና በመኪና መንገድና በባቡር ሐዲድ ዲናሚትና መትረየስ ጠምደን ስንከላከል የጠላት ጦር ገፍቶ መጣ። እኛም እየሸሸን ስንከላከል የእንግሊዝ ፣የአሜሪካና ፣የዩጎዝላቭ ጦር አርበኞች





ኣእርዳታ ስለደረሱልን ድልድዮችና መንገዶች ፈራረሱ። ጠላት የማለፊያ መንገድ ስላጣ በቀላል ለመማረክ ቻለ።

ከተባበሩት መንግሥታት ጦር ሠራዊቶች ዋና አዛዥ ለጦር አርበኞች ዋና አዛዥ ለሌ/ኮሎኔል ፋይል ለካፕቴን ጁሌኤታዮቼክ ለሜጀር አንቶኒዮ (አብዲሳ)ና ለሜጀር ማሪዮ ኢታሊኦ ‹‹ የጠላት ጦር ከሮም ወደ አንኮና ስለሚሸሽ ቆራጡን ጦር ይዛችሁ የሚሸሽበትን መንገድና ድልድይ እንድታፈርሱ የባቡር ሐዲዶችንም እንድታሰናክሉ ይሁን›› የሚል ነው።

የጠላት ጦር ድል ሆነ ። ሮማ ነጻ ሆና በጦር ጓደኞች ተያዘች ። በጦርነቱ ጊዜ ተጋድለው ከሞት የተረፉት አርበኞች በቀጥታ አንኮና እንዲገቡ ታዘዙ። እኛም ከዚህ በታች ባለው ትእዛዝ ገባን።

በመጀመሪያ የእንግሊዝና የአሜሪካ አርበኞች ገቡ፤ ቀጥሎም የዩጎዝላቪያ አርበኞች ወደ አንኮና መሄዳቸው ቀርቶ ባሪ ብርዲል በተባለው ቦታ ካምፕ ተዘጋጀላቸውና ገቡ።

እኔም አርበኞቼን አስከትዬ ሮማ ስገባ ጥቁር ሆነ ነጭ የሀገሬን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በግራ ክንዱ የእንግሊዝን በቀኝ ክንዱ እንዲያስር አደረግሁ። ከዚህም በላይ የኢትዮጵያን የአሜሪካን የዩጎዝላቪያና ሰንደቅ ዓላማዎች አርበኞች በየመኪናዎቻቸው እንዲያውለበልቡ አድርጌ ስገባ ፊልድ ማርሻል ባንካውንት በደስታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ተቀበሉኝ። ለእኔ የእጃቸውን የወርቅ ሰዓትና የፓንዱ ኒሻኖች ለሌሎችም አርበኞቹ እንደየአገልግሎታቸው ሽልማት አደረጉልን። ወዲያውኑ ሌሊቱን ወደ ሳንሳባሪና አውራጃ እንድንሄድ ታዘዝን። ከጥቂት ቀን እረፍት በኋላ ደግሞ የዩጎዝላቪያ አርበኞች ወዳሉበት ወደ ባሪ እንድንሄድ ታዘዝን። እኔ ከዚህ በታች ያለውን የጦር መሣሪያ ቆጥሬ አስረከብኩ።

140 ከጀርመን የተማረኩ ድግን መትረየሶች 302,890 ጥይት 4,500 የእጅ ቦምብ ። 250 መውዜር ጠብመንጃ ከ 10,000 ጥይት 10 ኦቶማቲክ ሽጉጥ 2 ካሜራ 90 ኮምባስ 15 ጅፕ መኪናዎች 2 ብረት ለበስ ቢልንዳ ባለመትረየስ 50 ቀላል መትረየሶች።

ከኢጣሊያ የተማረኩ 23,930 ጥይት 2,320 አልቢን ጠብመንጃ ከ 33,550 ጥይት 5 ከባድ ባለውሃ መትረየስ ከ፲፭ ሺ. ጥይት ፹፫ ድግን ባለወንፊት መትረየስ 00 የረሽ ጠብመንጃ ከ 33 ጥይት 4580 የእጅ ቦምብ 104 ጩቤ 7 የሚሊቴር ሬዲዮ 3 የቴሌግራም ሬዲዮ 790,740 ፊያት መትረየስ ከነዝናሩ 30 ከባድ መኪናዎች 73 ቀላል የሚሊቴር መኪና 17,731 የብረት ባርኔጣ ከእንግሊዝና ከአሜሪካን በአየር የተላከልኝ 40 መትረየስ ከ 9,883 ጥይት 400 የእጅ ቦምብ 350 ዲናሚትና 2 ሬዲዮ 4 የኢጣሊያ አገር ካርታ 350 ኮምፓስ 20 የጦር ሜዳ መነጽር አነስተኛ ሞተር ባለ 60 ኤም ኤም 6,471





ጥይ ሲሆን ልብስ ንብረትና ል ልዩ ዐይነት ትጥቅ አልተቆጠረም።

ከርክክቡ በኋላ የታላቋን ብሪታንያ የወታደር ልብስ ለብሼ ከነጭፍ ደ ጀርመን እንድዘምት ትእዛዝ ደረሰኝ። በሜጀርነት ማዕርግ የተቀላቀሉ ሚሊቴር ፖሊስ አዛዥ ሆኜ ወደታዘዝሁበት ቦታ ብዘምት ቀኑ የኛ ሆኖ ዋለ ። ሰባት ወር ከአሥር ቀን ጀርመን ሰነበትኩ። ከጀርመን ባሪ ትራንሲት ካምፕ ቁጥር 1 እንደ ተቀመጥኩ ከባሪ ካምፕ ወደ ሳንታ ማሪያ የስደተኞች ካምፕ ተዛውሬ ሁለት ዓመት እንደሠራሁ ወደ ካናዳ ሄጄ አገር እንዳይ ተደረገ። ካናዳ ሦስት ሳምንት ያህል እንደቆየሁ ስመለስ ናፖሊ ከሚገኘው ፌሬስካታ ወደተባለው ካምፕ በድንገት ትእዛዝ ደረሰኝ።

ከዚያም ያላሰብኩት ዱብ ዕዳ ገጠመኝ ። እንድዛወር ያደረገው ሜጀር ሳንስዎ የተባለው እንግሊዛዊ የሚከተለውን ጥያቄ አደረገልኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF

[illegible]/Fr

[illegible]

5 February 1946

To: His Ethiopian Majesty's Minister,
[illegible] — [illegible]

1. The bearer of this letter, [illegible], [illegible] pupil at the [illegible] Military School, was been a political prisoner in Italy and Ethiopia since the attempt on GRAZIANI's life in 1937.

2. On Mussolini's fall and when Italy sued for an armistice, [illegible] escaped from the concentration Camp at [illegible] and joined a Partisan band of British, Yugoslav, South African and others to fight the Germans. His services to the Common Cause were outstanding and were in the best tradition of those Ethiopian patriots who kept their flag flying during the darker days of the [illegible] occupation of their country. He is in possession of [illegible] very [illegible] certificates from the Officer Commanding the Patriot Unit and of a Patriot's Certificate issued by Field-Marshal Sir Harold ALEXANDER, Supreme Allied Commander in the Mediterranean Theater of Operations.

3. I feel that [illegible]'s outstanding services to the Allied [illegible] under difficult conditions deserve to be brought to the notice of His Majesty the Emperor and would be personally grateful if you would do [illegible] to the appropriate Ethiopian Government Department.

Yours sincerely,

[illegible]

ከተባበሩት ፡ የጦር ፡ ኃይሎች ፡ ለሰ ፡ አብዲሳ ፡ ሞገ ፡ የተሰጣቸው ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ።





ጥያቄና መልሱም ይኸውላችሁ፡፡

ጥ) ዜግነትዎን ለእንግሊዝ ወይም ለአሜሪካ መንግሥት ለማዛወር አይፈቅዱምን ?

መ) ፈጽሞ አልችልም፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ክዳትና ፍርሃት አናውቅም፡፡

ጥ) ሺ፱ ሺሊንግ ሰጡኝና እስኪ ከልብዎ ጋር ይምከሩና ይምጡ አሉኝ፡፡

በማግሥቱም ፈጽሞ አይሞከርም አልሁ፡፡

ጥ) ከዛሬ ጀምሮ ከእንግሊዝ ጦር ሠራዊት ተሰናብተዋልና ልብስዎን ያስቀምጡ፡፡

መ) አደሰታለሁ፡ ብቻ ወደ ሀገሬ እንድመለስ ያስፈቅዱልኝ፡ በድጋሚ የምስክር ወረቀት ይስጡኝ አልኩ የምስክር ወረቀቱን በሚገባ ከአንድ ከፍተኛ ኒሻን ጋር ከተቀበልኩ በኋላ በስደተኞች ካምፕ ሳለሁ እኒሁ እንግሊዛዊ መኰንን ከኢጣሊያኖች ጋር ተግባብተው «ሜጀር አብዲሳ በአንኮና አውራጃ በሳንባሪኖ ወረዳ በአርበኝነት ሲኖሩ ፴፪ ባለባቶች ገድለዋል ፡፡ ሀገሩንም ዘርፈዋል » ተብሎ እንድከሰስ አደረጉኝ፡፡

RH/fr

HEADQUARTERS ALLIED COMMISSION
APO 394
DISPLACED PERSONS AND REPATRIATION SUB-COMMISSION

[illegible]/1.1/38 Tel. [illegible] Ext. 239 5 February 1946

To: His Ethiopian Majesty's Minister,
CAIRO. — [illegible]

1. The bearer of this letter, Ato ABDISSA Agga, an ex-pupil at the HOLETA Military School, has been a political prisoner in Italy and Ethiopia since the attempt on GRAZIANI's life in 1937.

2. On Fascism's fall and when Italy sued for an Armistice, Ato ABDISSA escaped from the concentration Camp at TREIA and joined a Partisan band of British, Yugoslavs, South Africans and others to fight the Germans. His services to the Common Cause were outstanding and were in the best tradition of those Ethiopian patriots who kept their flag flying during the darker days of the Italian occupation of their country. He is in possession of laudatory certificates from the Officer Commanding the Patriot Unit and of a "Patriot's Certificate" issued by Field-Marshal Sir Harold ALEXANDER, Supreme Allied Commander in the Mediterranean Theater of Operations.

3. I feel that Ato ABDISSA's outstanding services to the Allied Cause under difficult conditions deserve to be brought to the notice of His Majesty the Emperor and would be personally grateful if you would so recommend to the appropriate Ethiopian Government Department.

Yours sincerely,

[illegible]

Copy to:
[illegible]

ከተባበሩት ፡ የጦር ፡ ጓደኞች ፡ ስለ፡ አብዲሳ፡ ዓጋ፡ የተሰጣቸው፡ የምስክር፡ ወረቀት ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

በኒሁ ሜጀር ትእዛዝ ሁለት እጆቼ በእግር ብረት ተወጥረው በካራቢኒሪዎች ታጅቤ በባቡር ወደሊቼ እሥር ቤት ተወሰድኩ ፡፡ ዘበኞቹ ከፋርጎ ውስጥ አስቀመጡኝ፡፡ የበረዶው ቅዝቃዜ ከሰንሰለቱ ጋር ሲገናኝ የነበረው ሥቃይ በጣም አሰቃቂ ነበር፡፡ ወደ ሊቼ ለመድረስ የባቡሩን ሐዲድ በረዶ ስለዘጋው መቆም ግድ ሆነ፡፡

ባቡሩ ከቆመበት ጣቢያ ተረኛው ፖሊስ ሁሉንም ክፍል ከመረመረ በኋላ እኔ ያለሁበትን ፋርጎ አስከፍቶ እንዳገኘኝ፡፡

ጥ) ማን ትባላለህ? ከወዴትስ ነው የመጣኸው አለኝ

መ) ሜጀር አብዲሳ እባላለሁ አገሬ ኢትዮጵያ ዕድሜዬ ፳፱ ዓመት ይሆናል፡፡ ካልኩት በኋላ ብርዱ ለመናገር ከለከለኝና ዝም አልኩ፡፡

ፖሊሱ ከባቡር ወርጄ ወደ አንድ ታዛ ቤት ተጠግቼ እሳት እንድሞቅ ቁርስ በዚያው እንድበላ አደረገልኝ፡፡ ሁሉም ትእዛዝ ተፈጸመልኝ፡፡

እሳት እየሞቅሁ ሳለሁ አንድ ሌላ ከፍተኛ ባለሥልጣን ከአቶሞቢል ወረደና፡፡

ጥ) ከየት ይመጣሉ? ማንስ ይባላሉ? እባክዎ ይንገሩኝ አለ፡፡





መ) አመጣጤ ከናፖሊ ነው፡፡ ሜጀር አብዲሳ ኢትዮጵያዊ እባላለሁ አልኩት፡፡

ከዚህ በታች ያለው እኔና እሱ የተመላለስነው መልስና ጥያቄ ነው፡፡

ጥ) ይቅርታዎን በሰንሲችና ተራራ የአርበኞች መሪ የነበሩት እርስዎ ነዎትን?

መ) ነኝ፡፡

ጥ) ወሬውን ሰምቼ ነበር አሁን ለፍርድ ጉዳይ መሄድዎ ነው?

መ) የምሄድበትን ምክንያት ከፍ/ቤት ስደርስ ብቻ ነው የማውቀው፡፡

ጥ) የቀሩት የጦር ጓደኞችዎ በሙሉ ጤና ናቸው?

መ) በጣም ደህና ናቸው፡፡

ጥ) ይቅርታ ያድርጉልኝና የት ይገኛሉ?

መ) ‹‹ ሁሉም በየተሰጠው ሥራ ላይ››፡፡

ጥ) እኔ የሰማሁት እንዲከሰሱ የተባሉት ኢትዮጵያ ፡ አሜሪካ እንግሊዝና ፡ ፈረንሳይ ናቸው ተብሎ ነበር ለምን ብቻዎን መጡ?



t.me/OLDBOOKSPDF

መ) በዚያ ሰዓት እኔ የሁሉም መሪ ነበርኩና ለሞቱት ሰዎች ለተቃጠሉት ንብረቶችና የፖስታ ቤቶች ኃላፊው እኔ ነኝ ስላልኩ ብቻዬን መጣሁ፡፡

ጥ) እኔ ለስደተኞች የተመደብኩ የጋዜጣ ወኪል ነኝና እባክዎ ፎቶግራፍ ላንሳዎ?

መ) አሁን ባለሁበት ሁኔታ ለመነሣት አልፈቅድም ቢሆንም ባይሆንም የምሄድበት ካወቁ በዚያ ይምጡ፡፡

ጥ) ምን የሚያሰጋዎ አለ ?

መ) የስጋት ጊዜ አለፈ እኔ አልሰጋም በዚህ ጉዳይ የሚያሰጋቸው ባለሥልጣኖች አሉ፡፡

ጥ) ሜጀር ሳንሶምን ያውቋቸዋልን?

መ) ስለማውቃቸውማ እነሆ እንድታሠር አደረጉኝ፡፡

ጥ) ባለጋራዎ ማን እንደሆነ ይገልጡልኛል?

መ) በፍርድ አደባባይ የምንሰለፍ ስለሆነ አሁን አስቀድሜ ብነግርዎ ዋጋ የለውም፡፡





ጥ)እንግሊዞች እጅዎን አሳልፈው የሰጡበትን ምክንያት ይነግሩኛልን?

መ) እንግሊዞች የግል ጥቅማቸውን መከታተል ስለሚወዱ ምክንያቱን ማወቅ አልፈልግም፡፡ ልማዳቸው ነው፡፡

ጥ) በአነጋገርዎ በእንግሊዞች የተቀየሙ ይመስላሉ?

መ) ስለ እንግሊዞችም ሆኑ ስለሌሎች ቅያሜ ፍርዱ ውሳኔ እስኪያገኝ ምንም የምነግልጥልዎ ነገር የለም፡፡

ጥ) አሁን ባሉበት ምንም አልሰጋም አሉ፤ ምክንያቱ ምንድን ነው?

መ) ኢጣልያኖች ከመልኬ ይልቅ ታሪኬን አጥንተው ያውቃሉ፣ ዛሬ አገሩ በጦር ጓደኞቼ ስለተያዘ የሚያሰጋኝ ነገር የለም፡፡

ጥ) ችሎት ከመቅረብዎ በፊት ጠበቃ አዘጋጅተዋልን?

መ) ፖለቲካው እንዳይበላሽ ማዘጋጀት ያለበት የጦር ጓዶች መ/ቤት ነው፡፡ እሱ ባይሠራ እራሴ አስብበታለሁ፡፡

ጥ) የአርበኞች መሪ ስለነበርኩ ኃላፊነቱን ወስጄኩ አሉ፣ ፍርድ ቢከብድዎ እነዚያን መጥራት ግድ አይሆንብዎትምን?



t.me/OLDBOOKSPDF

መ) እኛ ኢትዮጵያውያን ሁለት ቃል አንወድም ለወ?ጅነት ይፈልጉኝ እፈልጋቸዋለሁ፡፡ ክሱን እንዲያቃልሉልኝ ግን በፍጹም አልፈልጋቸውም፡፡

ጥ) ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከጦርነቱ በፊት ያውቁዎ ነበርን?

መ) እኔ አውቃቸዋለሁ፣ እሳቸው ግን አያውቁኝም፡፡

ጥ) በፊት በሀገርዎ በምን ዐይነት ሥልጣን ላይ ነበሩ?

መ) በ ፲፱፻፴፯8 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) የ፲፰ ዓመት ልጅ ስለነበርኩ ምንም ሥልጣን የለኝም ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ ባለሥልጣኑ በግል መኪናቸው ወደሊቼ ከተማ ሲጓዙ እኛም በባቡር ከተባለው ከተማ እንደደረስን የሊቼ ከተማ ወህኒ ቤት ሹም እኔን ተረክቦኝ ለመሄድ ስንጠባበቅ ሁለት የእንግሊዝ ካፕቴኖች ሁለት የደቡብ አፍሪካ መቶ አለቃዎች መጥተው በጦር ሠፈር ሁለት ቀን አሳድረውኝ በሦስተኛው ቀን ፍ/ቤቱ ከዚህ በታች ያለውን ጥያቄ ሲያቀርብልኝ እኔ መልሱን ሰጠሁ፡፡







የሻምበል አብዲሣ አጋ የኢትዮጵያን ድንበር ሲያስከብር የሚያሳይ

<u>ጥያቄና መልስ፡፡</u>

ጥ) ስም ከነአባት?

መ) አብዲሳ አጋ፡፡

ጥ) የትውልድ አገርዎ?

መ)ኢትዮጵያዊ ወሊጋ ጠ/ግዛት፡፡

ጥ) የተወለዱበት ዘመን?

መ) ፲፱፻፲፩ ዓ.ም (እ.ኢትዮጵያ አቆጣጠር)፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥ) ወላጆችዎ በሕይወት አሉ?

ጥ) አባቴ ሞተዋል፣ እናቴ አሉ።

ጥ) የማዕርግ ስምዎ?

መ) በዚህ አገር የእንግሊዝ መንግሥት በአርበኝነት የሰጠኝ ሜጀር እባላለሁ።

ጥ) በአርበኝነት በኢጣሊያ አገር ስንት ዓመት ሠሩ?

መ) ከ 42 - 45 ዓ.ም

ጥ) ወዲህ ፍርድ ቤት ሲመጡ በምን ሥራ ላይ ነበሩ?

መ) ወደ ሀገሬ ለመመለስ ትራንስፖርት እጠባበቅ ነበር። ከዚያ በፊት ግን በእንግሊዞች ጦር ሠራዊት በ ፰ኛ ክፍለ ጦር የሚሊታሪ ፖሊስ አዛዥ ነበርኩ።

ጥ) ደመወዝዎ ስንት ነበር?

መ) የሜጀር ደመወዝ የታወቀ ነውና መዘርዘር አያሻም፡ ምክንያቱም በገንዘብ ማጉደል አልተከሰስኩም።

ጥ) ሕግን ተከትለው ለፍ/ቤት መልስ ለመስጠት አይፈቅዱምን?





መ) እስካሁንም የሰጠሁት ሕግን በማክበር እንጂ በመገደድ አልነበረም ። አሁንም ከዚህ ሌላ ለሚቀርብልኝ ጥያቄ የጦር ጓደኞች ማለት የእንግሊዝ የፈረንሳይ የመስኮብና የአሜሪካ ተመልካቾችና ታዛቢዎች በሌሉበት ቃሌን ለመስጠት አልፈቅድም።

ጥ) ይህን ያሉበትን ሊገልጡልን ይወዳሉ?

መ) ዋናውን ምክንያት በዚያው ሰዓት እገልጥላችኋለሁ።

ከመልሱ በኋላ ላልተወሰነ ቀጠሮ ከነበርኩበት ከሊቼ ከተማ ወህኒ ቤት አሥራ አምስት ቀን ታሠርኩ። የወህኒ ቤቱ ሥቃይ ለትንግርት ነበር።

ከአሥራ አምስት ቀን በኋላ ጊዜውና ሰው አስገድዶኝ ወደ ፍርድ ቤት ቀረብኩ። አምስት የፍርድ ሰዎች ተሰየሙ። ይህም ማለት የኢጣልያ ተወላጅ ፕሬዚዳንት የእንግሊዝ የቀኝ አባል የአሜሪካው የግራ አባል የሞስኮ ተመልካች የፈረንሳዩ ሕግ አስከባሪ ሆነው በየመንግሥታቸው ስም ተሰይመው የ፴፪ ዓመት እሥራት አከናነቡኝና ተነሡ። ለእኔ የሕግ ጠበቃ እንዲሆኑኝ ከእንግሊዝ መንግሥት የታዘዙ ሜጀር ጄኔራል ሐርትመን ይባላሉ።ከዚህም ሌላ ጉዳዩ በግፍ የሚሠራ መሆኑን ተመልክተው በፈቃዳቸው እንዲከላከሉልኝ የቆሙት ሚስተር ኬቮርኪአን ኤድዋርድ ይባላሉ።

እሳቸውም አዲስ አበባ ከተማ ተወልደው ያደጉ ባጠላት ዘመን ተሰደው በ፪ ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ከጦር ጓደኞች ጋር የተቀላቀሉ ነበሩ፡፡

ሁለቱም ተከላካዮቹ ሊያድኑኝ አልቻሉም ፡፡ምክንያቱም የፍርድ ጉዳይ በፍጹም አልቆ ነበርና እንዚህ ሰዎች አንድ ዘዴ ተፈጠረላቸው፡፡ ይኸውም ለንደን ለሚገኙት ለፊልድ ማርሻል ቫውካውንት አሌግዛር የይግባኝ ቴሌግራም አስተላለፉ፡፡ ማርሻሉ ስለ ጀግንነቱ በቅርብ ያውቁኝ ነበር ፡፡በፊትም ለሥራ ጉዳይ ከኢጣልያ ወደ እንግሊዝ ሲሄዱ ከዚህ ለሚገኙት ስደተኞችና ጦር ሠራዊት ምግብ ልብስና ትጥቅ ዋና ግምጃ ቤት ዲሬክተር ሆኜ እንድሠራ አደራ ብለውኝ ሄደው ነበር፡፡ እሳቸውም ጀብዱዬን ስለሚያውቁ ከዚህ በታች ያለውን ቴሌግራም አስተላለፉ፡፡

‹‹ ከፊልድ ማርሻል ቫውካውንት አሌክሳንድር የተላከ፡፡››

ይድረስ ሮም ከተማ ለሚገኘው ለጦር ጓደኞች የጦር ሜዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሜጀር አብዲሳ አጋ ( አንቶኒዮ) የተባለ ኢትዮጵያዊ መኰንን በናዚስትና በፋሽስት እጅ ታሥሮ በነበረ ጊዜ ከጠላት እጅ አምልጦ ተሰደደ፡፡ በአርበኝነትም ሲኖር በአገሩና በንጉሡ ነገሥቱ ላይ የደረሰውን ግፍ ተመልክቶ ፋሺስትና ናዚስት





የሚሠሩትን ተቃውሞ ለዓላም ነፃነትና ለኢትዮጵያ ክብር ተጋደለ፡፡

‹‹ በአምስቱ ዓመታት በሀገራቸው ጠላትን በአርገበገቡት ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ይህ ወጣት መኰንን አብሮ የሚቆጠር ነው፡፡ መኰንኑ የሠራው ሥራ የሚያኰራው አገሩን ብቻ ሳይሆን ለእኛም ጭምር ሆኖ ሳለ የኢጣሊያ አገር ተቃጠለ ተዘረፈ ተብሎ የመኰንኑ መሠቃየት ለእኛም ሆነ ለዓለም መንግሥታት የሚያሳማ ጥልቅ ነገር ነው፡፡ ስለዚህ የ ፴፱ ዓመት የእሥራት ፍርድ በገንዘብ ተለውጦ የእንግሊዝ መንግሥት ጦር አዛዥ በብድር ስም ገንዘቡን ለኢጣልያኖች እንዲከፍል ሳስታውቅ መልሱን እጠባበቃለሁ››፡፡

‹‹... ይህ ቴሌግራም መተላለፋንም ለሜጀር ሳንሰምና ለሜጀር አብዲሳ አጋ እንዲነገራቸው››፡፡

‹‹ ፊልድ ማርሻል ቫውካውንት አሌክሳንደር››፡፡(ከእንግሊዝኛ የተተረጎመ)

ቴሌግራሙ እንደደረሰ ወዲያው ወደ ፍርድ ቤት ተጠርቼ $ 18,000 እንድከፍል ተነገ ረኝ፤ በትእዛዙ መሠረት እንግሊዞች ገንዘቡን አምጥተው ሲከፍሉና እኔ ስፈታ የተሰበሰበው ሕዝብ እልልታውን አቀለጡት ከጻኞቹ ውስጥ ብዙዎቹ በፊታቸው ላይ ኀዘን ይታይ ነበር፡፡ የገንዘብ አከፋፈሉም እንደሚከተለው ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

፭ኛ የእንግሊዝ መንግሥት እርዳታ $5,727.15

፮ኛ በእንግሊዝ ሚሊቴር ባንክ ከወር ደመወዜ ተጠራቅሞ የተከፈለ $5,911.75

፫ኛ በእንግሊዝ ዋስትና አገሬ ገብቼ እንድከፍል ከተደረገ በኃላ ወደ ሀገሬ መጥቼ የከፈልኩት ከሀገሬ መንግሥት ከወገኖቼ የተሰጠኝ እርዳታ ........................$ 7, 363.10

፬ኛ በዚህ ምክንያት ፍ/ቤት ቀርቤ ብዙ መጉላላት ከደረሰብኝ በኋላ አገልግሎቴ ዋጋ ያለው መሆኑ ታውቆልኝ በድጋሚ $ 890 እርዳታ አገኘሁ፡፡ የወጣልኝ ገንዘብ ጠቅላላ ድምር $19,890 ለዕዳ ከነወለዱ $ 18,975 ስከፍል የቀረው ለእኔ ቀርቷል ፡፡ የዕዳው ጉዳይ አለቀ፡፡ እንግዲህ ከጥቂት ዓመታት በኋላ የሀገሬን መሬት ለመርገጥ አሰብሁ፡፤ መጣሁ፤ የአመጣጤም ሁኔታ እንዲህ ነበር፡፡

* * *

## ከወህኒ ቤት ወደ ሀገሬ መመለስ፡፡

ከወህኒ ቤት ወጥቼ ወደ ሀገሬ እንድመለስ ጠየቅሁ፡፤ የመጣሁትም ከሮም ናፖሊ ከናፖሊ ካይሮ ከካርቱም ጅቡቲ አድርጌ ነው፡፡





በዚህም ጊዜ አንድ እንግሊዛዊ ዜግነቴን እንድለውጥ ጠይቆኝ ነበር፡፡ የሀገር ፍቅርና የራስ ጥቅም ምን እንደሆነ ስለማውቅ ጥያቄውን አልተቀበልኩም፡፡ በቀጥታ ሀገሬ እገባለሁ አልኩ፡፡

ቢአሳ ችንኩኤ ቺንቶ በተባለው ቦታ ልሳፈር ስል ፴ ዓመት በዚህ ቦታ የኖረ ኢትዮጵያዊ አገኘሁና ዘርዓይ ደረስ በወህኒ ቤት አለ የሚረዳው በማጣቱ ሳይሞት አይቀርም አለኝ፡፡ በሮም የሚተላለፉትም መልእክተኞቻችን ምንም ስላልጠየቁት ከችግሩ ንደቱ ሳይገድለው አይቀርም አለና እቅፏን ነገረኝ፡፡

ከጦር ጓደኞቼ ተለይቼ ወደ ናፖሊ ከመሄዴ በፊት የዚያን ስመ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ውጤት ማየት አለብኝ ብዬ እንደገና አንድ ወር ተቀመጥኩ፡፡ ከወር በኋላ መሞቱን ከእርግጠኛ ምንጭ ተረዳሁ፡፡በጎዘን ተቆራምጄ ካይሮ እንደደረስኩ የእንግሊዝ መንግሥት ኤምባሲ ሠራተኞች ቀደም ብሎ ቴሌግራም ተልኮላቸው ኖሮ አንድ ሙሉ ኮሎኔል ልከው ተቀበሉኝ፡፡

በቀጥታም ወደ እንግሊዝ ኤምባሲ ተወሰድኩና ብዙ ውይይት ካደረግሁ በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት እስኪረከበኝ ድረስ በዚያው ቆየሁ፡፤ ማንኛውንም ወጪ የእንግሊዝ መንግሥት ችሎ ሰባት ወር ካይሮ ከረምኩ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ቂጥሎም ካናዳ ሂጄ ተምሬ ዜግነቴን ለውጬ እንድኖር ተለመንኩ፡፡ ወደ ተባለው አገር ሂጄ ልማር‹‹ ዜግነት›› የሚባለውን ቃል አልቀበልም አልኳቸው፡፡ ውድ አገሬና ንጉሠ ነገሥቴ በዐይኔ ይዞሩብኝ ነበር፡፡ ከብዙ ትግል በኋላ እንደገና ወደ ካይሮ መጥቼ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሲረክበኝ ለጊዜው በእጄ ገንዘብ የለኝም ነበርና ለ፰ ቀን ችግር ደርሶብኝ ነበር፡፡ ከ፫ ወር በኋላ ወዴት እንደምሄድ ጠየቁኝ፡፡ እኔም በስጨት አልኩና የመጣሁበት ዶክሜንት ጠፍቶ እንደሆነ የጦር ኪዳን ጓደኞቼ ዋና መ/ቤት ይጠየቅ የሚል ጥያቄ አቀረብኩ፡፡ ከዚህ በኋላ ነቁና ሊያመሰግኑኝ እንደጀመሩ ሊስቱም ገና ከነፖስታው እንደታሸገ መዝገብ ቤት ተገኘና ተገረሙ፡፡

የገንዘብ ስጦታም አደረጉልኝ፡፡ አንዱ ችግር ሲገባበድ ሌላው ችግር ተፈጠረ፡፡ በማግሥቱ በመርከብ ተሳፍሬ ወደ አገሬ እንድገባ ሲደረግ ለአገሩ ባለሥልጣን የተጻፈውን ደብዳቤ የሚፈርምልኝ ባለሥልጣን ጠፋ፡፡ በዚህ ምክንያት እንደገና ሰባት ቀን ቆየሁ፡፡ ከኔ ጋር ለሦስት ሰው ልከፍለው የማይገባ ገንዘብም ከፈልኩና ከሞላ ጐደል አስፈላጊው ተፈጽሞልኝ በመርከብ ለመሳፈር ካናሊ ዴ ሱዊዝ ስደርስ የአሜሪካ የጦር መርከብ አመለጠኝ፡፡ ከ ፴፮ ሰዓቶች በኋላ ያለንዳች ሥጋት በዚሁ መርከብ ተሳፍሬ ፖርት ሱዳን ከተማ ስገባ የእንግሊዝ ጦር ወታደሮችና ሹማምንት ጥቂርና ነፁ ሳይሉ ተቀብለውኝ ፈንጠዝያ ሆነ፡፡





ምክንያቱም ጴ ዲ አፕሪሊ በተባለው የጦር ሜዳ ላይ አብረን ውለናልና፡፡

ሁለት ቀን የእንግሊዙ አገረ ገዥ ለኔና ለአሜሪካኖችም የጦር ሰዎች ግብዣ አደረጉልን፤ አሰብ ወደብ እስክንደርስ ድረስ የተደረገልኝ ግብዣ በጣም ግሩም ነበር፡፡ ጅቡቲ ስደርስ ባላምባራስ መንበረ ያየህይራድ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሹም በልዩ አቶሞቢል ተቀበሉኝና ታላቅ አቀባበል አደርገውልኝ ሰነበቱ፡፤ እስከ ምሽቱ ፫ ሰዓት በመልካም ግብዣ ላይ አመሸሁ በአምስት ሰዓት ወደ ማረፊያ ቤት ለመኝታ ሄድኩ፡፡ በዚያች ምሽት ሌላ ሥቃይ ተፈጠረ፡፡ ይኸውም በኢጣሊያ ወህኒ ቤት ያላየሁት ተባይ ክፍሉን ስለወረሰው ነው፡፡

ተባዮችን ስከላከል አድሬ ጧት በባቡር ድሬዳዋ መሄድ ሲገባኝ ተጓጉዬ በሁለተኛው ቀን ወደ ድሬዳዋ ተጓዝኩ፡፡ በሦስተኛው ቀን በአቶቡስ ጉዞዬን ወደ ሐረር ቀጠልኩ፡፡ የሄድኩበትም ምክንያት የቅርብ ጓደኛዬና መልካም መካሪዬ የነበረው ልጅ አሰፋ በሰው የተባለው ሰው በኢጣልያኖች ስለተገደለ የሱም ቤተ ዘመዶች ከተባለው ቦታ ስለነበሩ ልብሶቼንና ፎቶግራፎቹን ለማስረከብ ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

አባቱ ባለምባራስ በለውና ወሳጅ እናቱ የሚኖሩት ቀርሳ ነው ስለተባልኩ ወደ ድሬዳዋ በማግሥቱ ተመልሼ ከዚያው ሆቴል እንዳረፍኩ ሚቹ ክቡር ደጃዝማች ለጥያቄ ገብሬን አገኘኋቸው። ምንም ጥንት ባንተዋወቅ ስለኔ ጠይቀው ተረድተው ኖሮ ልዑል መኮንን መስፍን ሐረር ሐረር ውስጥ መኖራቸውንና እኔም ተገናኝቼ እጅ የምነሣ መሆኑን ገለጡልኝ። ተገቢውን መስተንግዶ ከዚያው ሆቴል አዘዙልኝ።

በማግሥቱ ጧት በሁለት ሰዓት ልዑልነታቸው የረር ጐታ ለመሄድ የሚመጡ መሆኑ ለደጃዝማች ስልክ ተደወለላቸው። ‹‹ እኛ ነገ ጧት ወደ የረር ጐታ እንሄዳለን ከነገ ወዲያ አንተ በባቡር ወደ አዲስ አበባ ስታልፍ የረር ጐታ ሲደርስ ባቡሩ መቆሙ ስለማይቀር በዚያ ሰዓት እኔ ራሴ አቅርቤ እጅ አስነሣሃለሁ። ከዚያም ከደጉ ልዑል ጌታዬ ሙሉ ተስፋና እርዳታ ታገኛለህ›› አሉኝ።

ይህን በሰማሁ ማግሥት በባቡር ወደ አዲስ አበባ ስጓዝ ክቡርነታቸው ‹‹ ሰው አስጠብቀውኝ ኖሮ ባቡሩ ጥሎኝ እንዳይሄድ ትእዛዝ ተሰጥቶት ከልዑል ነታቸው ፊት ቀረብኩ። እጅ ስነሣና ጫማ ስስም ዋ!! ያን ፊገግታና ርኅራኄ ሞት ቀሰፈው ያንድ ልዑል ሰው ግርማ ብቻ ሳይሆን የአባትነት አቀባበል አደረጉልኝ።የሀገሬን ዐፈር ስረግጥ ለመጀመሪያ ከኒህ ቅዱስ ልዑል ፊት በመቅረቤ ፈጣሪዬን አመሰገንሁ። ችግሬን ዘርዝሬ ነገርኳቸው። ‹‹ አሁን ባቡሩ ይቸኩላልና ሂድ እስከ ፫ ቀን አዲስ አበባ እመጣለሁና በዚያ ሰዓት ከግርማዊ አባቱ ዘንድ አቀርብሃለሁ አሁን ለስንቅህ $ 1000 ብር እንካ›› ብለው ሰጡኝ።


t.me/OLDBOOKSPDF



አባ ጅግሣ ከውጊያ በኋላ በጦር መስመር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ስተደረገልኝ ትሮታና ስተሰጠኝ ተስፋ ፈጣሪዬን አመስግኜ እጅ ነሥቼ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ቀጠልኩ። ልዑልነታቸው የሰጡኝ ባልደረባ ክቡር ደጃዝማች ለጥ ይበሉን ነበር።

ቀን ስንጓዝ ውለን ሌሊቱን በማግስቱ መጋቢት ፳፮ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ.ም አዲስ አበባ ገባን ባቡር ጣቢያ ወጣ ብዬ ብመለከት የኢትዮጵያ አንበሳ ሐውልት አለ መኖሩን በፋሺስት ተነቅሎ ሄዶ ሮም ከተማ ቢአሳቸንኪዬ ቸንቶ ላይ መኖሩን አስታውሼ ዕንባ አነቀኝ።

‹‹ በየትም ዓለም ጦርነት ይደረጋል በጦርነቱም ሜዳ ሁሉም ይሰለፋል ቀን የሰጠው ያሸንፋል። ድል ሁልጊዜ የአንድ ወገን ብቻ መሆን አለበት ። ግን ሰው ከተሸነፈ አገር ከተወረረ ሐውልት እያፈረሱ መታሰቢያን ማውደም በዓለም በተወገዘ መርዝ ጢስ ሰውን አቃጥሎ ድል ማግኘት ጀግንነት አይባልም። በወንድ ወንድ አለበት›› የጨካኙን ፋሺስት ቅስ.ም ለመስበር ፍቱን መድኃኒት ሆነው የተፈጠሩ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በእግዚአብሔር እርዳታ ድል ማድረጋቸውን የፋሺስት ጦር መጫር ስራሱ መሆኑን አምኜ የተሠራውንና የተገኘውን ውጤት ተገንዝቤ ተጽናናሁ።

እንደገና ቀና ብዬ የዳግማዊ ምኒልክን ግቢና አራዳ ጊዮርጊስን ተመለከትኩ። የኢትዮጵያ ዋና ከተማ በጠላት ኃይል ተወሮ ለጊዜው አሳዛኝ ነገር ቢፈጸምም በዚሁ ሰዓት የኢጣልያም ዋና ከተማ ሮም





እንዳልነበረች ሆና ሐውልቶቿ ታላቅ ሕንፃዎቿ ተሰባብረው ያን ሳመዛዝን ደግሞ ተደነቅሁ። ከ፲፱፻፳፰-፴፫ ዓ.ም ድረስ ሮማውያን ምግብ አጥተው አንድ ኪሎ ዳቦ ለመስመን እኛ እስካለንበት ወታደር ሠፈር ድረስ እየመጡ ሲጉላሉ ማደሪያ አጥተው ቤታቸው ተቃጥሎ በየካቡ ሥር ሲከርሙ ቀን ሐሩር የሌሊት ቁር ሲጫወትባቸው አይቻለሁ።

ጀግናው የሀገሬ ሕዝብ ለጠላት አልገዛም ብሎ ቢሰደድና አንዳንድ ግፍ ሲደርስበት ከዚያ ጋር ሳመዛዝነው የኢጣልያውያን የሞራልም የኢኮኖሚም ውድቀት አግኝቷቸው ነበር እላለሁ።

* * *

ቀኑ ወደ መምሽቱ ተቃረበ ። ሦስት ራሴን ሆኜ ዱክ ሆቴል ከተባለው ሆቴል አረፍን ። በማግሥቱ ክቡር ብላታ ዲሬሳ አመንቴ ‹‹ እንኳን ደህና መጣህ›› አሉኝና በፍጥነት ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት እንድቀርብ የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ ለነበሩት ለክቡር ሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ነገሩልኝ። ከጃንሆይ ዙፋን ፊት ቀረብኩ ። የጀግንነቴንና የአገልግሎቴን ሁኔታ የሚያስረዳውን ከተባበሩት ቃል ኪዳን ጓደኞች መንግሥታት የሰጡኝን የምስክር ወረቀት አቀረብኩ።

የሰውን ድካምና ውለታ የማይዘነጉት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከሰፊ ንግግርና ምስጋና በኋላ ሰፊ የገንዘብ ትሮታ አደረጉልኝ። ተስፋ

ያለው ምክርም ሰጡኝ። ጀኔራል ሙሉጌታን ባልደረባዬ እንዲሆኑ በወርቅ ትንፋሻቸው አዘዙልኝ። ከመጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፴፰-፴፱ ዓ.ም በግቢ ሚኒስቴር በክቡር ፊታውራሪ አስፋው ከበደ በኩል በቂ ደመወዝ እየተከፈለኝ ኖርኩ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በሰጡኝ ሙሉ ተስፋ መሠረት ከነሐሴ ፳፱ ቀን ፴፱ ዓ.ም እንሥቶ የንጉሠ ነገሥቱ የጦር ሠራዊት ባልደረባ እንድሆን የጦር ሚኒስትር የነበሩት ክቡር ራስ አበበ ጠርተው ነገሩኝ።

የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዋና እልፍኝ አስከልካይ ክቡር ሌ/ጀኔራል መርዕድ መንገሻ (የሀገር መከላከያ ሚኒስትር ሆነው በድንገት የሞቱት) ባልደረባዬ ስለሆኑ በሳቸው በኩል ሁሉም ነገር አልቆ ኅዳር ፪ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጦር ት/ቤት ገነት እንድሄድ ለጽሕፈት ሚኒስቴር ተላለፈልኝ።

፩፻፵ እጩ መኰንኖች በእንግሊዝና በኢትዮጵያውያን መምህራን ትምህርታችንን ስንከታተል የእንግሊዝ ጦር ሚሲዮን መኰንኖች የጦር ሜዳ ጀብዱዬን ስለሚያውቁ በፊትም በታላቋ ብሪታንያ የጦር ሠራዊት ውስጥ በሻለቃ ማዕርግ ስላገለገልኩ ስለኔ በጣም ያዝኑ ነበር። ከንዘናቸውም የተነሣ ሲያስተምሩ ‹‹ ሜጀር ካዴት አንቶኒዮ›› እያሉ ይጠሩኝ ነበር። ለአለቆቼ መስሎ ከታያቸው እኔ ከምንም አልቆጠርኩትም ከዚህም የበለጠውን ፈተና አልፌ አለሁ።





* * *

ብዙ ሐሳብ ዘንግቻለሁ። ለጊዜው በጽሑፍ ለማስቀረት ጊዜው ስላልፈቀደልኝ ብዙው ድርጊት እንደተረሣ ቀረ ። በዚህ መካከል ልረሳው የማልፈቅደው ነገር ቢኖር አንድ ጉዳይ ብቻ ነው። የናፈቀችኝን አገሬን ንጉሠ ነገሥቴንና ቤተሰቦቼን አይቻለሁ። በሀገሬ ብዙ ችግር ቢደርስብኝም ከምንም አልቆጥረውም። የማልረሳው ጉዳይ ደግሞ ያልኩት ይህ ነው፤ የኢጣልያን ሀገር በግፍ አቃጥለሃል ሀብቱን ዘርፈሃል (እናንተው ፋሺስት ሀገሬን አላቃጠለም)? ተብዬ ፴፪ ዓመት እንድታሠር ሲፈረድብኝ በእንግሊዝ መንግሥት አማካይነት በገንዘብ እንድመለስ አደረገልኝ። ይህን አልዘነጋውም።

የማልዘነጋው ደግሞ መንግሥቴ የጦር ታክቲክ እንድማር ገነት ት/ቤት ሲሰደኝ ቤተ ሰቦቼ በችግር ላይ ነበሩ፤ እንግሊዞች የከፈሉልኝን ገንዘብ እንድመልስላቸው በሕግ ጠየቁኝ ። ለጊዜው የምከፍለው ገንዘብ አጣሁኝ።

እኔ በውደድር ነበርኩ። ልጆቼ ኢዮብና እጅጋየሁ አብዲሳ ከሌሎች ቤተሰቦቼ ጋር ይሠቃዩ ነበርና በእውነት ለምን ተፈጠርኩ? እስከማለት ደረስኩ ኮርሱ በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም ተፈጸመ። ከ ፩፻፶ እጩ ተወዳዳሪዎች እኔ ፺ኛ ሆንኩ ። ከግርማዊነታቸው የምስክር ወረቀት ተቀበልኩ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ዋናው ዓላማዬ ሀገሬን መውደድ ንጉሠ ነገሥቴን ማፍቀር ወገኖቼን ማገልገል እንጂ « ለምን እንዲህ አደረጉኝ» ብዬ አላውቅም። በቆራጥ መንፈስ የተመሠጥኩ ድኅ በሙናኔ ስኮራ በድንገት በሚፈጸምብኝ አድራጎት አልበሳጭም። ይሁን እንጂ እንግሊዞችም ሳይቀሩ ብዙ ብዙ ነገር ነገሩኝ። አልተቆጣሁም ። ወደ ፫ኛ እግረኛ ክፍለ ጦር እንድሄድ ተወስኖብኝ ሳለ እንደገና ወደ ፲፩ኛ እግረኛ ሻለቃ አዲስ አበባ ተደለደልኩ።

በዚህ ሰዓት የሻለቃው ሕክምና መኰንን ሆንኩ፤ በዚህ ቦታ ፫ ወራት እንደ ሠራሁ በሻለቃው ጠ/ጦር ሠፈር የ፬ ሻምበል አዛዥ ሆንኩ። ከ፲፱፻፵፩-፵፫ ዓ.ም ደግሞ ፪፻፹፩ ወታደሮች ሹማምንትና ባለሌላ ማዕርግ የሚገኙበት የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ጠቅላላ የመሣሪያና የጥይት ዴፖ ማከማቻ ግምጃ ቤትና የአዲስ አበባ ዙሪያ ምሽግ ሹም የዘብ ተነጣይ ሻምበል ዋና አዛዥ ሆኜ ሠራሁ።

በዚህ ቦታ ፮ ዓመት ከ ፲፬ ቀን ያለ ዕረፍት ሠራሁ። ቀጥሎም በ፩ኛ እግረኛ ክፍለ ጦር የንብረት ሻምበል አዛዥ ሆኜ ክፍሉን በአዲስ ሕግ በደንብ እንዳቋቀቁም ታዝዤ ዓመት ከሠራሁ በኋላ እንደገና የመሣሪያ ግምጃ ቤት ኦርዲናስ ሥራ ሻምበልና የክፍለ ጦሩን ግምጃ ቤት ሥራ ብቻ እንዳቋቁም ታዘዝሁ።





ሥራውን ተረከብኩ። አንድ ዓመት ከ፮ ወር እንደቆየሁ ወደ ፩ኛ ብሬጌድ ለ፳ኛ ሻለቃ ረዳት መኰንንነት እንድሠራ ታዘዝሁ።

ከዚህ ቀጥዬ ከተባበሩት መንግሥታት ጦር ጓደኞች ከኢ.ን.ነ.መ ባለሥልጣኖች የተሰጠኚቸው የምስክር ወረቀቶችና የኒሻኖች ዐይነት በሚቀጥለው ተራ ቁጥር ለአንባቢዎች አበረክታለሁ።

ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተተረጐመ

የጦር ጓደኞች ዋና ኮሚሲዮን

አ.ፖ 394

ወደ አገራቸው የተሰደዱት እንዲመለሱ በተለይ የቆመ ኮሚሲዮን

ደ.ተ: ኤል 10.6 ኤ ዲ/ኤል ኤም ቴሌ 489081

አክሶት 239 የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፵፮ ዓ.ም

ለክቡር የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የካይሮ ሚኒስቴር እንዲያውቁትም አዲስ አበባ

፩ ይህንን ደብዳቤ የያዘ አብዲሳ አጋ የሆለታ የጦር ትምህርት ቤት ተማሪ የነበረው ከ ፲፱፻፴፮ ዓ.ም ከየካቲት 12 ቀን አደጋ ቀን ጀምሮ የፖለቲካ እሥረኛ ሆኖ በኢትዮጵያም በኢጣልያን አገርም ታስሮ ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

፪ በፋሺስቶች መውደቂያ ጊዜ ኢጣልያኖች እርቅ ስለፈለጉ ስለ አቶ አብዲሳ አጋ ከታሠረበት ትሬያ ከሚባለው እምልጦ ከእንግሊዝ ፣ ከዩጎዝላቭያ ከሶቶ አፍሪካ ከሌሎች አርበኞች ተደባልቶ ከጀርመን ጋር ይታገል ነበር።

የኢትዮጵያ አርበኞች አምስት ዓመት ሙሉ ሰንደቅ ዓላማቸውን በማፍቀር ከኢጣልያን ጭቆና ሲታገሉ የኢትዮጵያን ወንዶች ልጆች ስም ከፍ እንዳደረጉ ይህ አብዲሳ አጋ በድፍረት በመሥራቱና የኢትዮጵያ ወንድ ልጅ በመሆኑ የአገሩን ስም ከፍ ለማድረግ በቃ።

የአርበኞች ሹማምንቶችና ዋናም የጦር ሠራዊት ሹም ሰር ሃሮልድ አሌክሳንድር የሰጡት የምስክር ወረቀቶች በእሱ እጅ ይገኛሉ።

ማኅተም ፊርማ

የጦር ጋደኞች ዋና መሥሪያ ቤት ሜ.ጀ. ሃርመን

ሮም ዋና አዛዥና ሹም





አዲስ አበባ ሰኔ 28 ቀን 1939 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት

የጦር ሚኒስቴር

ቁጥር 334319 ተጨ.ማሪ መ/1983

ምክንያት።

ለንጉሠ ነገሥት የጦር ሠራዊት ጠቅላይ መምሪያ።

አዲስ አበባ

አብዲሳ አጋ የሚባል በጠላት ወረራ ዘመን በጠላት እጅ ታሥሮ በዚያው በአርበኝነት ሥራ በመሥራት በጅግንነት ያገለገለ ስለሆነ በጦር ሠራዊት ውስጥ በመቶ አለቃ ማዕርግ ተደልድሎ እንዲሠራ ስለተፈቀደ ይህ ትእዛዝ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በተባለው ማዕርግ ተደልድሎ ደመወዙን እንዲያገኝና ወደፊት ወደ ጦር ትምህርት ቤት እንዲላክ ይሁን።

ፊርማ ራስ አበበ አረጋይ።

ቁጥር 98092

አንኮና ኢጣሊአ



t.me/OLDBOOKSPDF

## የአርበኞች የምስክር ወረቀት::

በተባበሩት ነገሥታት ጦር ጓደኞች ስም ሆኜ አብዲሳ አጋ አንቶኒዮን አመሰግነዋለሁ:: በተባበሩት መንግሥታቶች ስም አብዲሳ አጋ በየጦሩ ሜዳ ከአርበኞች ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ስለ አገሩና በንጉሠ ነገሥቱ ስም ከጠላት ጋር ስለታገለና የጠላትን ፖለቲካ በመስበሩና ስለወጋ የጠላትን ሥራና አገር ስለአበላሸና ለጦር ሠራዊታችን ዋጋ ያለውን እንፎርማሲዮን ስለ ሰጠ:: ከፍ ባለ ምስጋና እናመሰግነዋለን :: አርበኞች በድፍረታቸው በሚያስደንቅ ሥራቸው ነፃነት ታገለዋል:: ስለዚህ የዓለም መንግሥታት በሞላ ማወቅ ይገባናል:: ይህንን የመሰለ የምስክር ወረቀት የያዙት አርበኞች ስለ ነጻነታቸውና ስለ አገራቸው ነጻነት ስለታገሉ ከፍ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል::

ፊርማ

1) ጄኔራል ማንፎልድ •

የአርበኞች ዋና ኮንትሮል::

ፊርማ

ጄኔራል ሃርልድ ፊልድ ማርሻል አሌክሳንደር የኢጣልያንን አገር የወጋ ጦር የተባበሩት መንግሥታት ጦር ሠራዊት ዋና አዛዥ::

መሪ::





2) ሜጀር ካባሬላሎድ ተጠባባቂ

ኮንትሮል ምክትል

3) ማንተም

የተባበሩት መንግሥታት የጦር ሠራዊት

* * *

ክሮም ዋና ከተማ በስተምሥራቅ በኩል ክሮም በግምት 085 ኪሎ ሜትር በሚሆን አንድ አነስተኛ ቀበሌ ሺሊና የተባለች ቦታ አለች:: የዚህች ቦታ አቀማመጥ ለዚች አገር ውበት ያላት ለምለም ቦታ ሁና ከተማዋ የገጠር መንደር ናት ::አንድ ትልቅ ፏፏቴ ውኃ በከተማዋ ዳር ያልፋል :: በአገሩ ላይ ብዙ አትክልት በያይነቱ አለበት:: በዚህች አነስተኛ ከተማ ውስጥ የኢጣሊያኖች ኖት ገንዘብ ይታተምበታል:: አንድ ትልቅ የልዩ ልዩ ወረቀቶች ፋብሪካ አለበት:: በዚህች ከተማ ነዋሪ ሕዝብ በግምት ፳ሺ ይሆናል:: እንኳንስ ሰዎቹና ድንጋዩና እንጨቱ ፋሽስትና ናዚስት ነው:: ሕዝቡ በሙሉ በተለይ በፋሺስት መሪዎችና በሞሶሊኒ ያመልካል፣ ከከተማው ውጪ ለመሄድ መንገዱ በጣም ምቹ ነው:: የፋሺስት ባለሥልጣኖች መሪዎች የእረፍት ጊዜያቸውን በዚች ባልታወቀች መንደር ያሳልፋሉ:: ከሕዝቡ እንዲጠናሁት ብዙ ጊዜ በዚህ ቦታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ንጉሣቸውም ሳይቀር ስብሰባ ያደርጋል የውጭ አገር ሰው አይደርስበትም ይባላል፡፡ ከከተማው ውጭ የሚገኙትን ሕዝቦች በደንብ አይቻቸዋለሁና የሞሶሊኒን ሥዕል የክርስቶስ ነው ሲሉ ያመልኩበታል፡፡በአገሩ የሥጋ ደዌ በሽተኛ (አካለ ጎዶሎ) ይበዛል ፡፡ እንዳየሁት ኑሯቸው ከሥልጠነው ዘመን ጋር ያልተስተካከለ ነው፡፡ ሴቱም ወንዱም ግልድም ይታጠቃሉ፡፡ የውሃ እንስራ በራሳቸው ላይ ይሸከማሉ፡፡የእጅ ባትሪ በጨለማ ያዩ እንደሆነ በጣም ይፈራሉ፡፡ ሴቶቹ በጣም ቁንጅና አላቸው ፡፡ ጽዳትና ትምህርት ያንሰቸዋል፡፡ ከዚህ አገር ሕዝብ ዋና ሀብታቸው የወይራ ዘይትና የወይን ጠጅ ነው፡፡ እርሻ በፈረስ ጉልበት ይታረሳል፡፡ በአገሩ ትላልቅ የእንጨት ዛፍ ይበዛዋል፡፡ ያንን አገር ስዞር በእውነት ተማሪ ቤትና ሆስፒታል አላየሁም፡፡ ከከተማይቱ ውጭ ተማሪ ቤት ሆስፒታል ቤተክርስቲያን አይገኝም፡፡ የዚህ አገር ሕዝብ በእውነቱ በጣም የሚገርሙ ፍጥረቶች ናቸው፡፡ መልካቸው ኢጣልያን ሆኖ ከሮም 145 ኪሎ ሜትር ሲገኙ ከከተማው ውጭ የሆኑት የኢጣልያን ቋንቋ አያውቁም፡፡ጥቁር ሰው ሲያዩ እንደሌሎቹ ኢጣልያኖች መደንበርና ማፈዝ አያውቁም፡፡እኔን ደጋግሞ የሚገርመኝ ስለ ኢትዮጵያውያን ኑሮ የጻፉትን አንዳንድ ጽሑፍ ስመለከትና የኤቢሲኖን ኑሮ ደረጃ ሳስታውሰው ነው፡፡







የሻምበል አብዲሣ አጋ በሌሊት ጨለማ በጥይት ውጋጉን የኢትዮጵያን ወሰን ሲያስከብር በዚህ ዐይነት ቆራጥነት ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF



የሻምበል አብዲሣ አጋ በሌሊት ጨለማ በጥይት ውጋገን
የኢትዮጵያን ወሰን ሲያስከብር በዚህ ዐይነት ቆራጥነት ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

በአርበኝነት ጉዞያት በኔ እጅ የተማረኩት የጠላት የጦር ሹማምንቶች፡፡

| ስምና ማዕርግ | የጦር ሜዳ ስም |
|---|---|
| 1) ኮሎኔል ትሩቤት አዶ | ቪአ ኑራ |
| 2) የመ/አለቃ ትሩንቤት አለዶ | ኮሊሻኖ |
| 3) የሻምበል ባሻ ቱሩንቤት ጉእዶ | ›› |
| 4) የሻለቃ ጉሊርሞ ማሪኦ | ›› |
| 5) ሻምበል ጂሮላሞ | ኡያኖ |
| 6) የመ/አለቃ ሳርዳኞ አዳሞ | ትሬአ |
| 7) ማርሻሎ ባሎምባሪን ፊስታ | ›› |
| 8) ሻምበል ኤርኮ አለዶ | ›› |
| 9) ማርሻሎ ችስቴል ኤኔርኮ | ›› |
| 10) የ፶ አለቃ ካባሬል ሴኒኤአና | ›› |
| 11)የ፶ አለቃ ሉኬት አሪኖ | ›› |
| 12)ሻለቃ ቪቶ ማሳሮ | ›› |





| | |
|---|---|
| 13)የመ/አለቃ ሳንቲ ኡቬርቶ | ›› |
| 14)የመ/አለቃ ሳልባቶሬ ኡጎ | ›› |
| 15)የመቶ አለቃ ቢአንክ ፍራንክ | ›› |
| 16)ሻምበል ማሪኖ ሊኦኔ | ሳንቤቶ |
| 17)ኮሎኔል ፋርቱናቶ | ›› |
| 18)ሌ/ኮሎኔል ዛፖኔ አሪጐ | ›› |
| 19)ሻለቃ ነቤሊ | ›› |
| 20)ካራቢኔሬ ኮንፎርቴ አርቦ | ›› |
| 21)ካራቢኔሬ አታቪኦ አቢሶ | ›› |
| 22)ኮሎኔል ጋኤታኖ | ›› |
| 23)ሻለቃ ካቺአት | ›› |
| 24)ሻለቃ አንቶኔል ሳንቤቶ | ›› |
| 25)የመ/አለቃ ባቼሎ ማሪና ጂሊአ ሳርአ | ማቴልካ |
| 26)ሻምበል ኒኮላ ጀባኒ | ማቴልካ |



t.me/OLDBOOKSPDF

| | |
|---|---|
| 27)ባንታዮኒ የባንክ ሹም | ›› |
| 28)የባንክ ሹም ዋና ጽሐፊ ጂኖ ኒኮላ | ›› |
| 29)ሻምበል ባሻ ኬአባ የባንክ ዘበኛ | ›› |
| 30)ሻምበል ፔኔኖ የባንክ ዘበኛ | ›› |
| 31)ጃኪሌ ሮማኖ | ካስቴላ ሳንቤትሮ |
| 32)ሻምበል ጃኮሞ ጉርቢኒ | ክጃኖ |
| 33)ጂአንካሬል አኢታ | ፋርንታሊ |
| 34)ሮሳ ዲቤትሮ | ›› |
| 35)ዶዶኖ ዶባኒ | ›› |
| 36)አርዴልእ አኖ | ›› |
| 37)ኤሸሮሚላንሲ | ችንጉሊ |
| 38)ማቺሊን አምራቶ | ›› |
| 39)አሲጃኖ ካዛሊ | ›› |
| 40)አምስት የጀርመን ወታደሮች | ኪጃኖ |







ሻምበል አብዲሣ አጋ በጦር መሥመር ከወታደሮቻቸው ጋር ሆነው ጠላትን ሲያጠቁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF



ሻምበል አብዲሣ አጋ በጦር መሥመር ከወታደሮቻቸው ጋር ሆነው ጠላትን ሲያጠቁ።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተመለከቱት ሰዎች ማለት መኰንኖች በሚገባ መማሪያ ይዘው በጦር ሜዳ የተማረኩት ሲሆን ጥቂቶቹ ለአንድ አንድ መሥሪያ ቤት ኃላፊ ሆነው ተማርከው ሕግ የተፈጸመባቸው ሲሆን ለምሳሌ በጦር ሜዳ የወደቁትንና ተማርከው ዕለቱን የሚገደሉትን አልጻፍኩም፡፡

እንዲሁም ባይገደሉም ተማርከው ዕለቱን የሚለቀቁትን ወይም የሚአመልጡትን ለመጻፍ አልቻልኩም፡፡

ስለዚህ በ42 ተራ ቁጥር የተመለከቱትን መኰንኖች ስምና የተማረኩበት የጦር ሜዳ ማስታወሻ ለደራሲዎች መስጠት የቻልኩበት ዋና ቁም ነገሩ ለደራሲዎች ሥራና ድካም እንደሚረዳ በማወቅ ነው፡፡ ስለ እነዚህ ሁኔታ በሰፊው ለማስረዳት ዝግጁ ነኝ፡፡

ነገር ግን እነዚህ መኰንኖች ሆኑ ሲቪሎች ፈጽሞ የወታደርን ስም የሚያጠፉ ናቸው፡፡ የመጨረሻዎቹ የኢጣልያኖችን ወታደሮች አስቀያሚና አሳፋሪ ናቸው፡፡ በያዙት መማሪያ ሳይሠሩበት ተማርከው የተገደሉ ናቸው፡፡





## የሴቶች ምርኮኞች፡፡

1) ሲኞሪና ሊና ጆቫኒ የራዲዮ ሠራተኛ ሳንሳ ባሪኖ
2) ›› እና ጋስባሪን ›› ›› ››
3) ›› ጆግኒና እንጀሎ ›› ›› ››
4) ›› ቡሩና ቡሩኖ ›› ›› ››
5) ›› ማሪአ ቲትኖ ›› ›› ››
6) ›› ፒፕኖ ካስቴሎ ›› ›› ››

* * *

አገሬ እንደ ደረስኩ ከብዙ በጥቂቱ ከወገኖቼ ከኢትዮጵያውያኖች ከበጎ አድራጊዎች የገንዘብ እርዳታ የሰጡኝን በጥቂቱ በክቡር ብላታ ዲሬሳ አመንቴና በአቶ አላና ናትናኤል የተደረገልኝን የገንዘብ እርዳታ አስታውሳለሁ፡፡

1) አቶ ዲሬሳ ዳንኬ
2) ወ/የሺ. እመቤት ዲሬሳ
3) አቶ አላና ናትናኤል



t.me/OLDBOOKSPDF

4) ›› ገቢሳ አያሙቻ

5) ›› ይርጋ ወ/ማርያም

6) ›› ደስታ ሮሮ

7) ›› ገብረ መስቀል ዋሲሁን

8) ›› ባዩ ገብረየስ

9) ›› በረከት ገብረ ሥላሴ

10)›› ሠይፉ ገብረ ዮሐንስ

11)›› ካሌሌ ጅምበሩ

12)›› ነጋሪ ሰማ

13)›› ሰሚ ቢርብርሳ

14) የተክበሩ ኃይሌ ቤሬ

15) የተክበሩ ተፈራ እስጢፋኖስ

16) ወይዘሪት ሣራ አያና

17) አቶ ገብረ ሥላሴ ወርቅነህ





18) ›› ተስፋ እዝጊ ሐውኪ

19) ›› ገብርኤል ኤድሞንድ

20) ክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም

21)አቶ ገብረ ሚካኤል ፍሥሐዬ

22)አቶ ብርሃነ ሥላሴ እብሳ

23)ክቡር አቶ ይልማ ዲሬሳ

24)አቶ ገብረ ወልድ ዋየሳ

25)›› ታሲሳ ይብሳ

26)›› ደሴ ካሣሁን

27)ሻለቃ ኃይሉ ማርያም

28) አቶ ደሬሳ ነጋቴ

29)›› ይስሐቅ ግደይ

30)›› ሳንድረስ ዘሪሁን

31)ባላታ ደሬሳ አመኑቴ



t.me/OLDBOOKSPDF

32)አቶ ዓለማየሁ ቅጣታ

33)›› አርአያ ኃይሌ

34) ›› ገብረ ማርያም ተስፋዬ

35) ›› ብርሃኑ ወርቅነህ

36) ወይዘሮ ቀለመ ወርቅ

37) አቶ አህመድ አበራ

38) ›› ምስጋና ሐውኪ

39) ›› ገብረ ማርያም አመንቴ

40)ወይዘሮ ጉዕማሽ

41)አቶ ጆርጅ ትረጅ

42)ወይዘሮ ማሕሌት አካሉ

43)›› ማርያም ነወረ

44)አቶ አርአያ አበበ

45) አቶ በየነ ቢያድግልኝ





46) ›› ነጋሪ ሙሉቱ

47) ›› ሣሙኤል ዋየሳ

48) ወይዘሮ ማርያም ተሻስ

49) አቶ ዮሴፍ አሰቦ

50) ›› አድምቄ

51)›› ዘመድ ወ/ገብርኤል

52) ›› ገለታ ብሩ

53) ›› ፈለቀ ይርጋ፥

ለነዚህ በጎ አድራጊዎች ከልባዊ ምስጋና በስተቀር ምንም አላደረግኩም።

* * *

ስለኔ ብዙ ሰዎች ብዙ አስተያየት ያቀርባሉ። አብዲሳ ለምን ወደ ኋላ ቀረ?በጋብቻ ወይም በሌላ ጉዳይ ዘመድ መፍጠር አይገባውም? ይሉኛል ። ሌሎች ደግሞ ለሌሎች አውርተውብኝ ሌሎች ሲነግሩኝ እንዲህ ይሉኝ ነበር ። « በ1929 ዓ.ም ኢጣልያ ፋሺስት ኢትዮጵያን ሲወራት በጦርነት ቆስሎ ሲማረክ የሄደው ሚስቱን ይዞ



t.me/OLDBOOKSPDF

ነው። በዚያም ሰዓት 15 ዓመቱ ነው››። የመጨረሻዎቹ ደግሞ እንዲህ ሲሉኝ እሰማለሁ። ‹‹ በጦርነቱ ጊዜ ከአርበኝነት ሲመለስ የነጭ ሚስት ነበራቸው››።

ያም ሆነ ይህ ሐሜቱ በሙሉ ውሸት ነው። ብደሰት ባልደሰት አልጨነቅም። ግን የሚሰነዘርብኝም ሐሜት የኔን መኖር ከማይፈልጉ ሰዎች እንጂ ከጨዋዎቹ የሀገሬ ዜጎች አይደለም ። የእኛን የኢትዮጵያውያንን ጨዋነት ለጨዋው ለሀገሬ ሕዝብ ላስረዳ አልፈልግም።

አገራችን ቅድስት ነች። በላይዋ ላይ የሰፈሩት ዜጎች ቅዱሳን ናቸው ። ሙሉ በሙሉ ‹‹ ናቸው›› ብዬ ባልናገርም መሆን አለብን እላለሁ። ‹‹ ጽድቅ በምድር›› እንደሚባለው ከኔ ጀምሮ ሌላውም ዜጋ ለሀገሩ ለንጉሡ ነገሥቱና ለወገኑ ከዕሙንነት የነጠረ የሥራ ውጤት ማሳየት አለበት ። እኛ ሠርተን ምሳሌ ካልሆን ማን ሊሆንልን ይችላል?።

